# የሉቃስ ወንጌል ጥናት

## ምዕራፍ፡ 1-10
## ኢየሱስ፡- ‹‹ና፤ ተከተለኝ›› አለ፡፡

# የሉቃስ ወንጌል ጥናት

**ምንጭ:-**

1. **አፕልኬሽን የተሰኘ መጽሐፍ ቅዱስ ጥናት መጽሐፍ** (THE APPLICATION BIBLE STUDY)
2. 1995 Intervarsity Christian Fellowship of the USA, WEB SITE FOR Daily Devotions
3. *ሥራ ለበዛላቸው ሴቶች የሚሰጥ መጽሐፍ ቅዱስ ጥናት* (BIBLE STUDY FOR BUSY WOMEN)
4. **በጃኪ አንደርሰን** (Jackie Anderson) **ተጽፎ በጳውሎስ ኮይቴ ተተረጎመ።**

## ከዚህ በታች ያለውን ለቡድንህ አባለት አንብብና ተወያዩ።

## ለጥናት የሚጠቅሙ መመሪያዎችና መጽሐፍ ቅዱስን ከሕይወት ጋር ማዛመድ፡

መጽሐፍ ቅዱስን ከሕይወታችን ጋር ለማዛመድ ስንሞክር ብዙ ጊዜ ያስቸግረናል። አንዳንድ ጊዜ በተሳሳተ መንገድ ከሕይወታችን ጋር ለማዛመድ እንሞክራለን። በመጀመሪያ በመጽሐፍ ቅዱስ ዘመን የነበሩ ሰዎች ሁኔታ ምን እንደሚመስል መረዳት ያስፈልጋል። ብዙ ጊዜአቶች አልፈዋል። በዚያን ጊዜ የነበረው ባሕልና ወግ በእኛ ዘመን ካለው ይለያል። ለምሳሌ:- በማቴ፡14፡29 ላይ ጴጥሮስ በውሃ ላይ እንደተራመደ ይናገራል። ይህ ማለት እኛ ዛሬ እንደ ጴጥሮስ በውሃ ላይ መራመድ አለብን ማለት ነው?

ብዙ ታሪኮች በዚያን ጊዜ ለነበሩ ለየት ላሉ ሁኔታዎችና ለአንዳንድ ሰዎች ብቻ እንደሆኑ መረዳት አለብን። ይሁን እንጂ እግዚአብሔር በቃሉ አማካይነት ራሱንና ፈቃዱን እንደሚገልጥ አምናለሁ። በጥንቃቄ ከተመለከትን እግዚአብሔር ለሕይወታችን ታላቅ መመሪያና ትምህርት ሊያስተምረን ይችላል። ይህ መመሪያ ለእኛ እና በመጽሐፍ ቅዱስ ላሉ ሰዎች ትርጉም አለው። መጽሐፍ ቅዱስን የመተርጎምና ከሕይወታችን ጋር የማዛመድ ሂደት ጥንቃቄ የተሞላበት ማጥኛ ዘዴ ነው እንጂ የራሳችንን ግምትና ስሜት መሠረት በማድረግ የተሳሳተ ትርጉም የምንሰጥበት አይደለም።

እኛ መጠቀም የምንችላቸው መመሪያዎች ከዚህ በታች  ተቀምጠውልናል፡

1. በመጀመሪያው ዘመን ለነበሩ ሰዎች መጽሐፉ ምን ለማስተማር እንደፈለገ በጥንቃቄ ተመልከት።
2. በእኛ ጊዜና በእነርሱ ጊዜ መካከል ያሉ ልዩነቶች ምንድናቸው? በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያሉ ሰዎች ሁኔታ ልዩ የሚያደርገው ምንድነው?
3. የክፍሉ ትርጉም የሚሰጠውን መመሪያ ለማግኘት ሞክር። ምናልባት ይህ ከሁሉም ሊከብድ ይችላል። መመሪያው በጥቅሱ ውስጥ መታየት አለበት። ክፍሉ የሚሰጠው መመሪያ ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚሻገር መሆን አለበት እንጂ በአንድ ጊዜ ብቻ የሚወሰን መሆን የለበትም። ደግሞ ከሌሎች የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ጋር የሚጋጭ መሆን የለበትም። በጊዜው ለነበሩ ሰዎችም ለእኛም የሚስማማ መሆን አለበት።

**የሉቃስን ወንጌል ስታጠና እነዚህን መመሪያዎች አንብብ፤ክለሳም አድርግ።**

# የሉቃስ ወንጌል፡ ምዕ፡1-10

## የትምርት ዝርዝር

1. የሉቃስ ዕቅድ_______________________ ሉቃ፡1፡1-4
2. ጅማሬ ___________________________ ሉቃ፡1፡5-25
3. ማሪያም____________________________ ሉቃ፡1፡26-45
4. የምሥራቹ ቃል______________________ ሉቃ፡2፡1-20
5. ሁለት አረጋዊያን_______________________ ሉቃ፡2፡21-40
6. የሕብረትና የፀሎት ጊዜ
7. ዮሐንስ________________________________ ሉቃ፡3፡1-20
8. ናዝሬት_________________________________ ሉቃ፡4፡16-30
9. ተልዕኮ__________________________________ ሉቃ፡4፡31-44
10. ለቡድን የተደረገ ጥሪ_______________________ ሉቃ፡5፡1-11
11. የፀሎት ጊዜ_____________________________ ሉቃ፡5፡17-35
12. ደቀመዝሙርነት_____________________________ ሉቃ፡6፡12-16
13. የሕብረትና የፀሎት ጊዜ
14. መባረክና መሸለም____________________________ ሉቃ፡6፡17-36
15. ልዩ መሆን___________________________________ ሉቃ፡6፡43-49
16. ወታደር_____________________________________ ሉቃ፡7፡1-10
17. ርህራሄ______________________________________ ሉቃ፡7፡11-17
18. አንዲት ሴት______________________________________ ሉቃ፡7፡36-50
19. ሴቶች_____________________________ ሉቃ፡8፡1-3 የሕብረትና የፀሎት ጊዜ
20. አፈር______________________________________ ሉቃ፡8፡4-15
21. አጋንንቶች__________________________________ ሉቃ፡8፡26-39
22. እምነት_________________________________ __ሉቃ፡8፡40-56
23. ደቀመዛሙርትን መላክ_________________________ ሉቃ፡9፡1-6 እና ቁ.40
24. እንጀራ____________________________________ ሉቃ፡9፡12-17
25. ዋጋ መክፈል_______________________________ ሉቃ፡9፡23-26 እና ቁ.57-62
26. ሰባዎቹን መላክ______________________________ሉቃ፡10፡1-24
27. ባልንጀራ_________________________________ ሉቃ፡10፡25-37
28. ማሪያምና ማርታ_____________________________ ሉቃ፡10፡38-42
29. የሕብረትና የፀሎት ጊዜ

መግቢያ፡- ስለ ኢየሱስ የበለጠውን ማወቅ ትፈልጋለህ? ሥራው ሐኪም የሆነ ከአህዛብ ወገን ወደ ጌታ የመጣው ሉቃስ ይህን የኢየሱስን ታሪክ ይጽፋል፡፡ እርሱ የሐዋሪያው ጳውሎስ የቅርብ ወዳጅ ሲሆን ብዙ የጥንት ክርስቲያኖችም ጋር ሕብረት ያደረገ ሰው ነበር፡፡ ምናልባት ሉቃስ ለሌሎች ሐዋሪያትም ቃለ መጠይቅ ሳያደርግ አይቀርም፡፡ የኢየሱስ እናት ከሆነችው ማሪያም ጋር እንደተነጋገረ በጊዜው የነበረው ባሕል ያስተምራል፡፡ ሉቃስ ስለ ኢየሱስ ሕይወት በጥልቀት የተማረ ሰው ነበር፡፡ አንተም የሉቃስን ወንጌል ስታጠና በዚህ ወንጌል ብቻ የሚገኙ ስለ ሰው ልጅ የሚያወሩ እውኔታዎችን በጥልቀት ትማራለህ፡፡

እያንዳንዱ ሰው በሕይወቱ የሚከተለው አንድ ሰው ይኖረዋል፡፡ አንተ የአንድን አስተማሪ ወይም የኳደኛ ፈለግ ልትከተል ትችላለህ፡፡ እኛ ሁል ጊዜ እንደ አንድ ሰው ለመሆን ስንፈልግ የዚያን ሰው ፈለግ እንከተላለን፡፡ ኢየሱስ ወንዶችና ሴቶች እርሱን እንዲከተሉት ጠራቸው፡፡ እርሱ ወደ ሰማይ ሲሄድ የእግዚአብሔርን መንግሥት ሥራ ያስቀጥሉ ዘንድ ተተኪ ደቀመዛሙርትን ፈለገ፡፡ ኢየሱስን መከተል ማለት ምን ማለት እንደሆነ እንዲገባችሁ ይህ የወንጌል መጽሐፍ ይረዳችኋል፡፡

ይህ የጥናት መመሪያ ለየት ያለ የአጠናን ዘዴ ይጠቀማል፡፡ ይህም ማለት፡- መጀመሪያ የመጽሐፍ ቅዱሱን እውነት ለራስህ በጥንቃቄ ትመለከተዋለህ፡፡ ከዚያም በመንፈስ ቅዱስ እርዳታ አማካኝነት የክፍሉን ዋና ሀሳብ ታገኛለህ፡፡ ታማኝ ሆነህ ብዙ ካነበብክ ቃሉን ከሕይወትህ ጋር እንዲታዛምድ መንፈስ ቅዱስ እንዲረዳህ ለመንፈስ ቅዱስ በር ትከፍታለህ፡፡
በእያንዳንዱ ሳምንት መጽሐፍ ቅዱስ ከመነበቡ በፊት አንድ ሰው አጭር ታሪክ ከመጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል፡፡ ይህን ማድረግ የክፍሉን ሀሳብ በደንብ እንድትረዳና አዳዲስ ነገሮችን እንድታይ ይረዳሃል፡፡

## ትምህርት-1

ሉቃ፡1፡1-4 ከዚህ በታች የቀረበው ለየት ያለ ትርጉም ነው፡፡
ቁ.1 በኛ ዘንድ ስለ ተፈጸመው ነገር ብዙዎች ታሪክን በየተራው ለማዘጋጀት ሞክረዋል፡፡
ቁ.2. እነዚህ ሰዎች ከመጀመሪያው እግዚአብሔር ተስፋውን ይፈጽም ዘንድ ለእኛ ያደረገውን በዓይን ያዩትና የቃሉ አገልጋዮች የሆኑትን ደቀመዛሙርት ሪፖርት እንደ ምንጭ ተጠቅመዋል፡፡
ቁ.3. ይህንን ታሪክ ከመጀመሪያው ጀምሮ በጥንቃቄ መርምሬአለሁ፡፡ የከበርህ ቴዎፍሎስ ሆይ በጥንቃቄ ሁሉን ከመጀመሪያው ተከትዬ በየተራው ልጽፍልህ መልካም ሆኖ ታየኝ፤
ቁ.4. ይህም የተማርኸውን ቃል እርግጡን እንድታውቅ ነው፡፡

| |
|---|
| ምልከታ፡- ምልከታ ማለት መጽሐፍ ቅዱስ የሚለውን ሀሳብ ብዙ ጊዜ ደግሞ ደጋግሞ በጥንቃቄ ማንበብ ማለት ነው፡፡ የአንድን ክፍል ዋና ሀሳብ ከመወሰን በፊት ደግሞ ደጋግሞ ማንበብ ተገቢ ነው፡፡<br>በአንድ ታሪክ ውስጥ መነሳት ያለባቸው ነገሮች ከዚህ በታች ቀርበዋል፡- |

ቁልፍ ቃላት፤- በአንድ ታሪክ ውስጥ የተደጋገሙ ቃላት ቁልፍ ቃላት ናቸው፡፡
እነዚህም፡-
ሰዎች
ቦታዎች
ጊዜያት
ክስተቶች
ለምልከታው ጠቃሚ የሆኑ ጥያቄዎች፡- ምን? ለምን? መቼ? የት? ማን? እንዴት?

**ምልከታ**፡- እነዚህን አራት ቁጥሮች እንደገና አንብብ፡፡ ሌሎች የዚህን ክፍል ትርጉም በቀላሉ እንዲያውቁ የክፍሉን ሀሳብ በራስህ አባባል አስቀምጥ፡፡

**ጥያቄዎች**፡

1. ሉቃስ ከአህዛብ ወገን ጌታን የተቀበለ ሐኪም ሲሆን ከአህዛብ ወገን ለሆነው ቴዎፍሎስ ይጽፋል፡፡ ሉቃስ ይህንን ወንጌል የጻፈው ለምንድነው?
2. ሉቃስ ታሪኩን በትክክል ለመጻፍ ቃለ መጠይቅ ያደረገው ለማነው? በመግቢያ ላይ የተጻፈውን ተመልከት፡፡
3. ሉቃስ የኢየሱስን ታሪክ ያዘጋጀው እንዴት ነው?
4. ቁ.2ን እንደገና አንብብ፡፡ ስለ እግዚአብሔር የምትማረው ምንድነው?
5. ሉቃስ ይህንን መጽሐፍ የጻፈበትን ዓላማ ከተማርክ በኋላ ከዚህ ወንጌል ማየት የምትችለው ጭብጥ ምንድነው?
6. አንዳንድ ሰዎች ኢየሱስ ፍጹም ሰው መሆኑን አያምኑም፡፡ እውነተኛ የኢየሱስን ታሪክ ማወቅ ለእምነትህ የሚሰጠው ጥንካሬ ምንድነው?

**ማጠቃለያ**፡- ሉቃስ የኢየሱስን ወንጌል በጊዜ ቅደም ተከተል ይናገራል፡፡ ይህም ማለት የተከሰቱ ነገሮችን እንደየቅደም ተከተላቸው ያስቀምጣል ማለት ነው፡፡ ነገሮችን በቅደም ተከተላቸው በማስቀመጥ የታወቀው የሉቃስ ወንጌል ብቻ ነው፡፡ ሉቃስ ይህ ታሪክ እውነተኛ የኢየሱስ ታሪክ መሆኑን ሊያሳየን ፈልጎ ታሪኩ በተፈጸመበት ጊዜ፣ በሰዎች ስምና የተፈጸሙባቸው ቦታዎች ላይ ትኩረት ያደርጋል፡፡ እግዚአብሔር በሆኑ ነገሮች ሁሉ ላይ የበላይ ተቆጣጣሪ እንደሆነ ሉቃስ ያስተምረናል፡፡

## ትምህርት- 2

**መግቢያውን አንብብ፡-** ሉቃስ የኢየሱስን ወንጌል በጊዜ ቅደም ተከተል ይናገራል፡፡ ይህም ማለት የተከሰቱ ነገሮችን እንደየቅደም ተከተላቸው ያስቀምጣል ማለት ነው፡፡ ነገሮችን በቅደም ተከተላቸው በማስቀመጥ የታወቀው የሉቃስ ወንጌል ብቻ ነው፡፡ ሉቃስ ይህ ታሪክ እውነተኛ የኢየሱስ ታሪክ መሆኑን ሊያሳየን ፈልጎ ታሪኩ በተፈጸመበት ጊዜ፣ በሰዎች ስምና የተፈጸሙባቸው ቦታዎች ላይ ትኩረት ያደርጋል፡፡ እግዚአብሔር በሆኑ ነገሮች ሁሉ ላይ የበላይ ተቆጣጣሪ እንደሆነ ሉቃስ ያስተምረናል፡፡ ይህ እውነት በዮሐንስ ወንጌል ላይ ተገልጧል፡፡ ወደ ሃያ ሺህ የሚያህሉ ካህናት በእሥራኤል ይኖሩ ስለ ነበረ ተራ በተራ በቤተመቅደስ ያገለግሉ ነበር፡፡ ወደ አሥር ሺህ የሚያህሉ ካህናት በዘካሪያስ ቡድን ውስጥ ነበሩ፡፡ እነዚህ አሥር ሺህ ካህናት እያንዳንዱ በየጧቱ ወደ

ቤተመቅደስ እየገቡ ዕጣን ያጥኑ ነበር። እግዚአብሔር ዘካሪያስን የሚመርጥበት ትክክለኛ የምርጫ ጊዜ ያውቅ ነበር። በእግዚአብሔር ጊዜ ዘካሪያስ ወደ መቅደስ ገባ፤ ዮሐንስም ተወለደ።

አሁን የቡድኑ መሪ በሉቃ፡1፡ 5-25 ያለውን ታሪክ ይናገራል። ይህን ለማድረግ ተዘጋጅ፤ደግሞ ቀጣዩን ታሪክ ከሉቃ፡1፡26-38 በሚቀጥለው ሳምንት የሚናገረውን አንድ ሰው ወክል።
ሉቃ፡1፡1-25 አንብብ።
አሁን እነዚህን ክፍሎች በጥንቃቄ ተመልከት።

ለምልከታ የሚጠቅሙ ጥያቄዎች፡

1. ከቁ.1-25 ባለው ክፍል የሆነው ዋናው ጉዳይ ምንድነው?
2. ስለ ጊዜ የሚጠቁም ነገር ምንድነው? ለምሳሌ በቁ.5 ‹‹ዘመን›› ይላል። ከእነዚህ ዘመን ጠቋሚ ነገሮች የምትማረው ምንድነው?
3. ስለ ዘካሪያስና ኤልሳቤጥ ምን ትማራለህ? የእነርሱ ጠንካራ ጎን ምን ነበር?
4. ኤልሳቤጥ በተወለደችበት ባህል መሠረት አንዲት ሴት ሐጢአት ከሰራች መካን ሆና ትቀራለች የሚባል አመለካከት ነበር።መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ዘካሪያስና ኤልሳቤት ምን ይላል? እሷ ለምን መካን ሆነች ብለህ ታስባለህ?
5. ስለ ዮሐንስ ምን ትማራለህ? መልኣኩ ገብርኤል በተናገረው መሠረት በሕይወቱ የነበረው ዓላማ ምን ነበር?
6. ቁ.16-17 እንደገና አንብብ። ስለ ልብ መለወጥ ከዚህ ክፍል የምትማረውን ተወያይ።
7. ልብህ እንዴት ነው? በሕይወትህ ለለውጥ ዝግጁ ነህ?
8. አንተስ እንደ ዮሐንስ እንዴት የእግዚአብሔርን መንገድ የሚጠርግ መልእክተኛ መሆን ትችላለህ?

***<u>ማጠቃለያ</u>***፡- ዮሐንስ ማለት ‹‹እግዚአብሔር ቸር›› ማለት ነው። እግዚአብሔር ለዮሐንስ የራሱን ስም ሰጠው። እግዚአብሔር ቸር በመሆኑ ለእኛ የሰጠውን ደህንነት ስናስብ ዮሐንስ የተላከበትን ዓላማ የበለጠ መረዳት እንችላለን። እግዚአብሔር ዮሐንስን የኢየሱስን መንገድ የሚጠርግ መልእክተኛ አድርጎ ላከው። ዮሐንስ ድንጋይ ልብ ሁሉ ለኢየሱስ ይለውጥ ነበር።

## ትምህርት-3

***<u>መግቢያውን አንብብ</u>***፡- ሉቃስ የኢየሱስን ታሪክ ይናገራል። በዘካሪያስ፣በኤልሳቤጥና በዮሐንስ ይጀምራል። ዛሬ ስለ ዮሐንስ የበለጠውን እንማራለን ግን አስቀድመን ስለ ማሪያም ታሪክና ስለ መልዓኩ እንማራለን። ታሪኩ ከእግዚአብሔር ቃል እንደሚከተለው ቀርቧል።

ታሪኩን ከሉቃ፡1፡26-45 በቃል ተናገር።
ሉቃ፡1፡26-56 አንብብ።

**ምልከታ፡**

የሚከተሉት ጥያቄዎች ክፍሉን ጠለቅ ብለህ እንድትመለከት ይረዱሃል፡፡

1. ስለ ማሪያም የሚገልጹ ጥቅሶችን በሙሉ ተመልከት፡፡ ከዚህ የምትማረው ምንድነው?
2. ስለ ማሪያምና ከእግዚአብሔር ጋር ስላላት ግንኙነት የምትማረው ምንድነው? በውስጧ ያላት አመለካከት ምንድነው?
3. ስለ ኢየሱስ ወይም ስለ ሕፃኑ የሚያሳዩትን ቃላት ፈልግ፡፡ ስለ እርሱ የምትማረው ምንድነው?
4. ቁ.32 እና 33 እንደገና አንብብ፡፡ በነገሥታት ላይ ትኩረት የሚያደርጉ ቃላት ፈልግ፡፡ ኢየሱስ ዘላለማዊ ንጉሥ መሆኑ ዛሬ ለእኛ የሚሰጠው ትርጉም ምንድነው?
5. ከድንግል ስለ መወለድ ይህ ታሪክ የሚያስተምረን ምንድው? ይህ ለማመን አስፈላጊ ነው?

ስለ ዘካሪያስ የቀረውን ታሪክ ከሉቃ፡1፡57-80 አንብብ፡፡

1. በዚህ ክፍል የተፈጸመው ዋናው ክስተት ወይም ጉዳይ ምንድነው?
2. በቁ.68-75 የዘካሪያስን ፀሎት እንደገና በጥንቃቄ አንብብ፡፡ ከዚህ የምትማረው ምንድነው?
3. ስለ ዮሐንስ ዓላማ ሌላ የምትማረው ነገር ምንድነው?ቁ.76-79 እንደገና አንብብ፡፡
4. በቁ.76-79 ዘካሪያስ ልጁን በእጁ ይዞ ሲፀልይ የተሰማው ስሜት ምንድነው?
5. ከዚህ ከመጀመሪያው ምዕራፍ ስለ እግዚአብሔር የተማርከው ምንድነው?

**ከሕይወት ጋር ማዛመድ**

6. ቁ.38 እና 45 እንደገና አንብብ፡፡ ከዚህ የምትማረው ምንድው? ይህንን በተለየ መንገድ ከሕይወትህ ጋር እንዴት ልታዛምድ ትችላለህ?

**ማጠቃለያ**፡ እግዚአብሔር መስሑን ወይም ንጉሥን ሊልክ ቃል ገብቷል፡፡ የዳዊት መንግሥት የዘላለም መንግሥት እንደሚሆን እግዚአብሔር ለዳዊት ተናግሮ ነበር፡፡ ኢየሱስ በመምጣቱ ያንን ተስፋ ፈጸመው፡፡ ስለዚህ እግዚአብሔር የተናገረውን ተስፋ ቃል እንደሚፈጽም ማመን ትችላለህ፡፡ ለማሪያምና ኤልሳቤጥ ልጅ መውለድ የሚቻል አልመሰላቸውም፡፡ ነገር ግን ሃይል ሁሉ የእግዚአብሔር ነው፡፡ እግዚአብሔር ፈቃዱን ለመፈጸም ድሆችን፣ወጣቶችን፣አዛውንቶችን፣ሴቶችና ወንዶችን ምርጫው ያደርጋል፡፡ በእግዚአብሔር ላይ ካለን እምነት አንደኛው ደረጃ እግዚአብሔር ሁሉን ቻይ መሆኑን ማመን ነው፡፡ ዘካሪያስና ማሪያም ሁለቱም እግዚአብሔር ስለ ሚያደርገው ነገር ሁሉ እርሱን እንዳመሰገኑ ልብ በል፡፡

## ትምህርት-4

**መግቢያውን አንብብ፡-** ይህ ለክርስቲያኖች አዲስ ታሪክ አይደለም፡፡ ታሪኩን ቀድሞ ስለምታውቅ ‹‹ስሰማው ይሰለቸኛል›› ብለህ ልታስብ ትችላለህ፡፡ ቢሆንም በፊት ያልተለማመድከውን ነገር አሁን ልትለማመድ ስለምትችል በጥልቀት መርምር፡፡ ይህንን በአዲስ መልክ ለማጥናት ሞክር፡፡ ታሪኩን ስታጠና ራስህን በማሪያም፣በእረኞቹ ወይም

በታሪኩ ውስጥ ካለው ሌላ ሰው ቦታ አስቀምጥና ምን ይሰማቸው እንደነበር ለመረዳት ሞክር፡፡

በሉቃ፡2፡1-20 ያለውን ታሪክ በቃልህ ተናገር፡፡

ታሪኩን አንብብ፡፡

ለምልከታ የሚረዱ ጥያቄዎች፡

1. ከቁ.1-4 ድረስ ባለው ሥፍራ ላይ ያለውን ታሪካዊ እውኔታ ተመልከት፡፡ በዚህ ክፍል ሉቃስ ስለ ሮም መንግሥት፣ስለ አገዛዙ የመሳሰሉ ነገሮችን በጥንቃቄ የሚናገረው ለምንድነው? ዮሴፍ ወደ ዳዊት ከተማ የሄደበትን ምክንያት ሉቃስ በጥንቃቄ ሊነግረን የፈለገው ለምንድነው?
2. ኢየሱስ በቤተልሔም መወለዱ አስፈላጊ የሆነው ለምንድነው?
3. ንግሡ ተወለደ! የአይሁድ ሰዎች ለብዙ ዘመናት ይህንን ነገር ይጠባበቁ ነበር፡፡ እረኞች ዝቅተኛ የሕብረተስብ ክፍል ተደርገው ይወሰዱ ነበር፡፡ ታዲያ የኢየሱስን መወለድ ዜና አብሳሪዎች እረኞች እንዲሆኑ እግዚአብሔር ለምን መረጣቸው?
4. በመልዓኩ የተነገረው የምሥራቹ ቃል ምንድነው? ቁ.11 እንደገና አንብብ፡፡ በዚህ ክፍል ኢየሱስ እንዴት ነው የተገለጸው? በሮም አገዛዝ ሥር ላሉ እረኞች ይህ ምን ማለት ነው?
5. ራስህን በታሪኩ ቦታ አስቀምጥ፡፡ እንደ እረኛ የሚሰማህ ስሜት ምንድነው?
6. ቁ.17 እንደገና አንብብ፡፡ የእረኞች ሥራ ምንድነው? ለዚህ ውጤቱ ምንድነው?
7. በዚህ ታሪክ ለማሪያምና ለዮሴፍ የተሰማቸው ጥልቅ ስሜት ምንድነው?
8. በዚህ ታሪክ እግዚአብሔር አንተን የሚያስተምረው ምንድነው?

**ማጠቃለያ**፡- የሉቃስ ወንጌል በጊዜው ስለ ነበረው የሮም ታሪክ የሚነግረን ብቸኛው ወንጌል ነው፡፡ አንባቢዎቹ ደግሞ አብዛኛውን ጊዜ የግሪክ ሰዎችና የሮም ሰዎች ሲሆኑ በጊዜው በነበረው ፖለቲካ ተመስጠው ነበር፡፡ እግዚአብሔር የታሪክ ተቆጣጣሪ ነው፡፡ እንዲሁም ማሪያምና ዮሴፍ ለሕዝብ ቆጠራ ወደ ቤተልሔም እንዲመጡ አስቀድሞ ቆጠራው እንዲደረግ የወሰነ አምላክ ነው፡፡ የኢየሱስ መወለድ ብዙዎችን ያስገረመና ታላቅ ደስታን የፈጠረ ጉዳይ ነበር፡፡ እነዚህ ሰዎች የዮሐንስንና የኢየሱስን አገልግሎት እንዲፈልጉ እግዚአብሔር እያዘጋጃቸው ነው፡፡

## ትምህርት-5

**የመክፈቻ ጥያቄ፡-** የሕይወትህ መጨረሻ ሲደርስ ምን መምሰል ትፈልጋለህ ሠርተህ ለመፈጸም የምትፈልገው ነገር ምንድነው ምናልባት ይህን ነገር ብዙ ጊዜ አላሰብክም ይሆናል፡፡ ነገር ግን ጥቂት ጊዜ ውሰድና አስብበት፡፡

በዚህ ታሪክ ዕድሜአቸውን በመልካም የጨረሱ ሁለት ሰዎችን እንመለከታለን፡፡ በሃይልና ትርጉም ያለውን ሕይወት መኖር ምን ማለት እንደሆነ እነዚህ ሰዎች ያወቁ ይመስላል፡፡ እስቲ ስለ ኢየሱስ የነበራቸውን ‹‹ምስክርነት›› እንመልከት፡፡

ታሪኩን ስማና እግዚአብሔር እንዲጠቀምህ ራስህን ለእግዚአብሔር አዘጋጅ።

ታሪኩን ከሉቃ፡2፡21-40 በቃልህ ተናገር።

ሉቃ፡2፡21-40 አንብብ።

ምልከታ፡- ምልከታ ማለት መጽሐፍ ቅዱስ የሚለውን ሀሳብ ለመረዳት ብዙ ጊዜ ደግሞ ደጋግሞ በጥንቃቄ ማንበብ ማለት እንጂ አንተ በራስህ ሀሳብ የምትተረጉመው እንዳይደለ አስታውስ።

1. በእነዚህ ክፍሎች የሆነው ዋናው ጉዳይ ምንድነው?
2. በሉቃ፡2፡1-21 ያለው ክፍል ስለ ኢየሱስ መወለድና ስለ ግርዛቱ ይናገራል። አሁን ኢየሱስ በቤተመቅደስ በጌታ ፊት የሚቆምበት ጊዜ ደረሰ። ሕጉ በቁ.22-24 እንዴት ነው የተገለጸው? ዘሌ፡12፡6-8 የዚህ የመንጻት ስነስርዓት መጀመሪያ እንደሆነ ብሉይ ኪዳን ይናገራል። በዘሌዋዊያን መጽሐፍና በሉቃ፡2፡24 ላይ የማሪያምና የዮሴፍ እኮኖሚ ምን ደረጃ ላይ እንዳለ ፍንጭ እናገኛለን። የኢኮኖሚ ደረጃው ምን ላይ ነበር?
3. በታሪኩ ውስጥ ያሉትን ሰዎች በጥንቃቄ መመልከት ወሳኝ ነው። እነዚህን ቁልፍ ሰዎችን በመመልከት የምትማረው ምንድነው? (ማሪያም፣ስሞኦንና ሐና::)
4. ስምዖንና ሐናን አነጻጽር። እነርሱን አንድ የሚያደርጋቸው ምንድነው?
5. ስምዖን ኢየሱስን ባየው ጊዜ ምን ተሰማው ብለህ ታስባለህ?
6. በቤተመቅደስ ውስጥ እንደነ ስምዖን ወይም ሐና ያሉ ሰዎችን ንግግር ከሚሰሙ ሰዎች እንደ አንዱ ብትሆን ምን ይመስልህ ነበር?
7. በሉቃስ ወንጌል መንፈስ ቅዱስ ትልቅ ቦታ አለው። ስለ መንፈስ ቅዱስ የሚያወሩ ክፍሎችን ተመልከት። ስለ መንፈስ ቅዱስ የሚያወሩ ጥቅሶችን እንደገና ማንበብ ትችላለህ። ከእነዚህ ጥቅሶች የምትማረው ምንድነው?
8. የስምዖንን ትንብት በቁ.33-35 እንደገና አንብብ። ስለ ኢየሱስ የምትማረው ምንድነው? የኢየሱስ የመጨረሻው ሕይወት ውጤት በእሥራኤልና በማሪያም ላይ ምን እንደሚሆን ነው የተነገረው?

**ከሕይወት ጋር ማዛመድ**

1. በቁ.34 መሠረት ሰዎች ኢየሱስን በደስታ ይቀበሉታል፤ አሊያም ይገፉታል። ከራስህ የሕይወት ልምምድ በመነሣት ስለዚህ ጉዳይ ከቡድንህ አባላት ጋር ተወያይ።
2. ነፍስን የሚያሳዝን ነገር እንኳን ቢመጣ ማሪያም ኢየሱስ እንዲጠቀማት ፈቃደኛ ነበረች። በእውነተኛ ሕይወትህ የሚገጥምህን ተግዳሮትም ሆነ ድል ለቡድንህ አባላት አካፍል።
3. በቁ.38 ሐና ኢየሱስን እንዳየች ለምላሽዋ ያደረገቻቸው ሁለት ነገሮች ምንድናቸው? ይህ በቁ.17 እና 20 ላይ እረኞቹ ከሰጡት ምላሽ ጋር እንዴት ይመሳሰላል? እነዚህ ልንከተላቸው የሚገቡ ለእኛ የተቀመጡ ምሳሌዎች ናቸው:: የኢየሱስን ወንጌል ልትመሰክርላቸው የምታስባቸውን ሰዎች ስም ለቡድንህ አባላት ተናገር። ወንጌሉን ለመመስከር አጋጣሚዎችን ሁሉ እግዚአብሔር እንዲሰጥህ ፀልይ።

ማጠቃለያ፡- ሉቃስ ለግሪክ አማኞች ጽፏል። በቁ.32 ላይ ከአሕዛብ ወገን የሆነውን ስምዖንን ጠቅሶ ኢየሱስ ለዓለም በሙሉ ብርሃን እንደሆነ ይናገራል። በዓለም ላይ ያለው ሕዝብ በሙሉ ወንጌልን ሰምቶ የመዳን ዕድል ከእግዚአብሔር ተሰጥቷል። ስለዚህ አስደናቂ ጉዳይ ክብር ለእግዚአብሔር ይሁን።

ቁ.39 ከሌሎች ወንጌላት ክፍሎች ጋር ሲነጻጸር ግራ ሊያጋባ ይችላል። በማቴ፡2 መሠረት የማሪያም ቤተሰብ ወደ ናዝሬት ከመሄዳቸው በፊት ወደ ግብፅ እንደሄዱ እናውቃለን። ይህ ሉቃስ በታሪኩ ውስጥ አንዳንድ ነገሮችን እንዳላካተተ ያሳያል።

## ትምህርት-6

**መግቢያውን አንብብ፡-** የሉቃስ ወንጌል በእውነተኛ ሰዎች ታሪክና በእውነተኛ ቦታዎች የተሞላ ነው። ምልከታ ማለት እነዚህ ታሪኮች ለሕይወታችን ምን እንደሚያስተምሩ ለማወቅ የሚረዳን የመጀመሪያው ደረጃ እንደሆነ አስታውስ። ቀጥሎ ደግሞ እግዚአብሔር ለታሪኮቹ የሰጠውን ትርጉም እንመረምራለን። ከዚያም በኋላ መንፈስ ቅዱስን በመስማት በሕይወታችን ላይ ለውጥ እንዲመጣ እንሻለን። እኛ ቀድሞ ከተለማመድናቸው ታሪኮች ውስጥ ታላቁን መዝገብ (ሀብት) እንዴት ማግኘት እንችላለን? ልክ በመዝ፡1 ላይ እንዳለው ሰው ቃሉን ለማሰላሰል ጊዜ መውሰድ እንችላለን። የሚከተውን ዘዴ እኛም መጠቀም እንችላለን፡-

**አንድን ታሪክ ለማጥናት የሚረዱ አራት የጥያቄ ዘዴዎች**

1. **በታሪኩ ላይ በቀጥታ የምመለከተው ምንድነው?** ለምሳሌ፡- ማን? የት? መቼ? ምን ሆነ? በክፍሉ ላይ ያሉ ሰዎች አመለካከት ምንድነው? መማር ያለብኝ በጊዜው የነበሩ ልማዶች ምንድናቸው? አስፈላጊ የሆኑ ቁልፍ ቃላት የትኞቹ ናቸው?
2. **የክፍሉ ትርጉም ምንድነው?** እነዚህ ሰዎች ለምን ተቀመጡ? ይህ ታሪክ በዚህ ጊዜ ለምን ሆነ? እነዚህ ነገሮች (ጉዳዮች) የሆኑት ለምንድነው? እነዚህ አመለካከቶች ለምን ፈለቁ? እነዚህ ልማዶች ለምን ይዘውተራሉ? እነዚህ ቃላት ለምን ተቀመጡ?
3. **ይህ ክፍል ለእኔ የሚሰጠው ትርጉም ምንድነው?** በዚህ ክፍል ለእኔ የተገባው ተስፋ ቃል ወይም የተሰጠኝ ትዕዛዝ አለ? ልከተላቸው ወይም ልሸሻቸው የተቀመጡ ምሳሌዎች አሉ?
4. **ይህንን ታሪክ ካጠናሁ በኋላ የእኔ ሕይወት እንዴት መለወጥ አለበት?**

ለሉቃስ ወንጌል ጥናት በሙሉ እነዚህን ዘዴዎች እንጠቀማለን። ዛሬ ጊዜ ወስዳችሁ አንዳችሁ ለአንዳችሁ ፀልዩ፤ሕብረትም አድርጉ።

## ትምህርት-7

***መግቢያውን አንብብ፡-*** *የሉቃስ ወንጌል የተጻፈው በአንደኛው ክፍለ ዘመን ነበር፡፡ ይህ ጊዜ የእሥራኤል ሕዝብ በአስጨናቂው ሮም አገዛዝ ሥር የነበረበትና የራሳቸው የውስጥ ችግሮች የነበሩበት ጊዜ ነበር፡፡ በዚህ ጊዜ በሕይወቱ ብዙ ሰዎችን የቀየረው አንድ ሰው ብቅ አለ፡፡ ይህ ሰው እሳትን የተላበሰ ሰው ሲሆን ስለ እሳት በብዙ መንገድ ይናገር ነበር፡፡ አንዳንድ ሰዎች ‹‹ይህ ሰው መስሑ ሊሆን ይችላል›› ይላሉ፡፡ ግን አይደለም፡፡ ይሁን እንጂ ይህ ሰው በክርስትና ታሪክ ዓይነተኛ ሚና የነበረው ሰው ነበር፡፡ ይህም ሰው ዮሐንስ ነበር፡፡ ታሪኩ ከእግዚአብሔር ቃል እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡*

*ታሪኩን ከሉቃ፡*3፡1-20 *ተናገር፡፡*
*ታሪኩን አንብብ፡፡*

**ምልከታ**፡- *በታሪኩ ላይ በቀጥታ የምለከተው ነገር ምንድው?*

1. *በታሪኩ ላይ የተጠቀሰው ማነው? ታሪኩ መቼ ሆነ? የት ተፈጸመ? ዋና ዋና ጉዳዮች ምንድናቸው? በጊዜው የነበሩ አመለካከቶች ምንድናቸው? ስለ ጥምቀት ልማድ እኔ የማውቀው ምንድነው? በክፍሉ ላይ የተጠቀሱ ቁልፍ ቃላት ምንድናቸው?*
2. *በቁ.*15 *መሠረት የሕዝቡ አመለካከት ምን ነበር? ከቁ.*15-17 *ስለ ዮሐንስ የምትማረው ምንድነው?*
3. *ስለ እውነተኛ ንስሐ ዮሐንስ ጎላ አድርጎ የሚናገረው ምንድነው?*
4. *ከቁ.*10-14 *እንደገና አንብብ፡፡ ስለ እነዚህ ሰዎች የምታገኘው ምንድነው? የዕለት ኑሮአቸው ምን ይመስላል?*

**የክፍሉ ትርጉም ምንድነው?**

1. *ታሪክ እንደሚናገረው ሄሮድስና በታሪኩ ውስጥ የተጠቀሱ ሌሎች ሰዎች ምግባረ ብልሹ ሰዎች ነበሩ፡፡ የሥልጣናቸው ምንጭ ምንድነው? ይህ ዮሐንስ ከነበረው ስልጣን ጋር ስናነጻጽረው ምን ይመስላል?*
2. *በቁ.*4-6 *ላይ የዮሐንስ አገልግሎት ይበልጡን እንዲገባን ሉቃስ ከኢሳያስ መጽሐፍ ይጠቅሳል፡፡ ስለ እርሱ የተገለጸውን ነገር በጥንቃቄ ተመልከት፡፡ (ይህ የመካከለኛው ምስራቅ ንጉሥና የተከታዮቹ ስዕላዊ መግለጫ ነው፡፡ በዚያን ጊዜ አንድ ገዢ ወደ መንገድ ሲሄድ አሽከሩ ወይም መልዕክተኛው ቀድሞ ወደ ፊት እንዲሄድ ይደረጋል፡፡ ይህ መልዕክተኛ ንጉሡ በሚሄድበት አካባቢ ያሉ ሰዎች በነቂስ ወጥተው በምድረ በዳ መንገዱን እንዲያዘጋጁለት ያስጠነቅቃቸዋል፡፡ በመንገድ ላይ ጉድጓዶች ሁሉ ይደፈናሉ፤ወጣ ገባው ሁሉ ይደለደላል፤ጠማማው መንገድ ሁሉ ይቃናል፤ሸካራውም መንገድ ትክክል ይሆናል።) ዮሐንስ ‹‹ንጉሥ›› ለሆነው ኢየሱስ ምን በማድረግ ነው መልዕክተኛ የሆነው? ጠማማውን ማቅናትና ሸካራውን መንገድ ትክክል ማድረግ ማለት ለዮሐንስ ምን ማለት ነበር? ይህን ንስሐ ከመግባት ጋር የሚያገናኘው ምንድነው?*
3. *ንስሐ መግባት ማለት ምን ማለት ነው?*
4. *ቁ.*7-9 *ብዙ ሰዎች በዮሐንስ እጅ ለመጠመቅ እንደመጡ ይናገራል፡፡ ዮሐንስ በእነርሱ ላይ ጠበቅ ያደረገው ለምንድነው? እነርሱ፡- ‹‹አብርሃም አባት አለኝ፤*

ስለዚህ ችግር የለም›› እንዳሉ በዚህ ዘመን እኛ እንደነሱ የምንናገረው ነገር ምንድነው? ዮሐንስ ይህን አስተሳሰባቸውን የታገለው እንዴት ነበር?

5. በቁ.15-17 ላይ ዮሐንስ ስለ ኢየሱስ ግልጽ አድርጎ የሚናገረው ነገር ምንድነው? ስለ መስሑ በተገለጸው ነገር ላይ አስገራሚ የሆነው ምንድነው?
6. የኢየሱስ ጥምቀት ከዮሐንስ ጥምቀት የሚለየው በምንድነው?
7. በቁ.18 ላይ የዮሐንስ ስብከት ስለ ምሥራቹ ቃል ነው:: ይህ ቃል መጥቶ በእሳት ስለሚያጠምቀው ፈራጁ (ኢየሱስ) ቃል ሊሆን የሚችለው እንዴት ነው?

**ይህ ለእኔ የሚሰጠው ትርጉም ምንድነው?**

1. በቁ.10 ሕዝቡ፡- ‹‹ምን እናድርግ? ›› አሉ፡፡ ዛሬ በእኛ ዘመን በተግባር መግለጽ የምንችለው ንስሐ ምን ዓይነት ነው?
2. ጠማማው የቀና መንገድ እንደሚሆንና እንዲሁም ሸካራው መንገድ ትክክል እንደሚሆን መጥምቁ ዮሐንስ ተናገሯል፡፡ ዛሬ በሕይወትህ ‹‹ጠማማ›› ወይም ‹‹ሸካራ›› የሆነው ሥፍራ የትኛው ነው?

**ይህንን ታሪክ ከተማርኩ በኋላ ሕይወቴ እንዴት መለወጥ አለበት?**

በዚህ በሚቀጥለው ሳምንት በተግባር የምታደርገውን ነገር ለቡድንህ አባላት ግለጽ፡፡ ታዲያ ያደረከውን ነገር በቀጣዩ ሕብረት ጊዜ ለቡድንህ አባላት ለማካፈል ሞክር፡፡

**ማጠቃለያ**፡- የዮሐንስ ጥምቀት ሰዎችን ከፊት ለሚጠብቃቸው ነገር የሚያዘጋጅ ብቻ ነበር፡፡ የኢየሱስ ጥምቀት ግን እውነተኛ፣ቋሚና መንፈስ ቅዱስ በዚያ በመኖሩ ሃይለኛ ትርጉም ያለው ጥምቀት ነው፡፡ ይህ ጥምቀት እግዚአብሔር ከእኛ ጋር እንዳለና በእኛ ውስጥ እንደሚኖር የሚያሳይ ነው፡፡ ንስሐ መግባት ማለት ከሐጢአት ጎዳና ወደ እግዚአብሔር ተመልሶ በፍጹም ልብ ለእግዚአብሔር መታዘዝ ማለት ነው፡፡ ሐጢአት ማለት በእግዚአብሔር ላይ አለመታመንና በራስ ጎዳና መጓዝ ማለት ነው፡፡ ዮሐንስ ሕዝቡን ባጠመቀ ጊዜ ሕዝቡ ሕይወታቸውን በሙሉ ለእግዚአብሔር ማዘጋጀታቸውን የሚያሳይ ምልክት ነው፡፡

## ትምህርት-8

**የባለፈውን ትምህርት ከጠናህ በኋላ የሆነው አዲስ ነገር ምንድነው?**

**መግቢያውን አንብብ፡-** በዚህ ጥናት ውስጥ ስለ መጽሐፍ ቅዱስ ለኢየሱስ ያለውን አመለካከት እናያለን፡፡ በዚህ ጊዜ ለሕዝቡ የነበረው የብሉይ ኪዳን መጽሐፍ ነበር፡፡ ኢየሱስ ስለ ራሱ ለመመስከር መጽሐፍ ቅዱስን እንደሥልጣኑ ቃል እንዴት እንደተጠቀመ እናያለን፡፡ ኢየሱስ ሕዝቡን ያስገረመውን አዲስ ትርጉም ሲሰጥ እንመለከታለን፡፡
ኢየሱስ ከአዳም ዘር መምጣቱንና ሰው መሆኑን ለማሳየት ሉቃስ የኢየሱስን የዘር ሐረግ ይደረድራል፡፡ ኢየሱስ ከዳዊት ዘር ሲሆን ለዳዊት መንግስት የተተነበየውን ትንቢት ኢየሱስ በመምጣቱ ፈጸመው፡፡ ሌላው ከታሪኩ የምንማረው ኢየሱስ በዮሐንስ እጅ እንደተጠመቀና መንፈስ ቅዱስ በእርግብ አምሳል በእርሱ ላይ መውረዱን ነው፡፡ ኢየሱስ

ወደ ምድረ በዳ ሄዶ በሰይጣን ሲፈተን 30 ዓመቱ ነበር፡፡ በመጽሐፍ ውስጥ ያለውን እውነት በመጠቀስ ሰይጣንን አሸነፈው፡፡ ይህ ሁሉ አገልግሎቱን በገሃዱ ለመጀመር ያዘጋጀው ነበር፡፡ የዛሬው ታሪክ በሉቃ፡4፡16-30 ላይ ነው፡፡

በሉቃ፡4፡16-30 ያለውን ታሪክ በቃል ተናገር፡፡

አሁን ታሪኩን አንብብ፡፡

**በታሪኩ ውስጥ በቀጥታ የሚመለከተው ምንድነው?**

1. በታሪኩ ውስጥ የምታየውን እውኔታ በሙሉ ተናገር፡- በታሪኩ ውስጥ የተገለጸው ማነው? በታሪኩ ውስጥ የሆነው ምንድነው? ታሪኩ የተፈጸመው በየትኛው ሥፍራ ነው?
2. ስለ ናዝሬት ጠቃሚ የሆነው ምን ነበር?
3. በክፍሉ ውስጥ የታዩ አመለካከቶችና ምላሾች ምን ነበሩ?
4. እኔ መማር ያለብኝ በጊዜው የነበረው ልማድ ምንድነው? *ምኩራብ የአይሁድ ሰዎች የሚሰበሰቡበት ትንሽ ቤት ነበር፡፡ በጊዜው በነበረው ወግ መሠረት በምኩራብ ውስጥ መደበኛ ሰባኪ አልነበረም፡፡ በዚህ ፈንታ በምኩራቡ ውስጥ ከተሰበሰቡ ሰዎች የተወሰኑቱ መጽሐፍ ቅዱስን ካነበቡ በኋላ ውይይት ማድረግ ነበር፡፡ አንድ በጣም አስፈላጊ ነው የሚሉት ሰው ከውጭ ተጋብዞ መጽሐፉን ያነብላቸውና አስተያየቱን እንዲሰጥ ይደረግ ነበር፡፡* ኢየሱስ የተጠቀመው የትኛው የመጸሐፍ ቅዱስ ክፍል ነው?

**የክፍሉ ትርጉም ምንድነው?**

1. ኢየሱስ ኢሳ፡61፡1-2 ይጠቅሳል፡፡ እርሱ በአገልግሎቱ መጀመሪያ ላይ ይህንን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ለምን የጠቀሰ ይመስላሃል?
2. በዚህ መጽሐፍ ላይ ስለ ተጠቀሱ አራት ቡድኖች ተወያዩ፡፡ ስለ እነዚህ ቡድኖች መልካም ዜና የሆነው ምንድነው?
3. ይህ በጊዜው ለነበሩ ሰዎችም ሆነ ዛሬ ላለንበት ዘመን የሚሰጠው ትርጉም ምንድው?
4. ይህንን የመጽሐፍ ክፍል ኢየሱስ በራሱ እንዴት ተግባራዊ ያደርጋል? እርሱ ሊያደርግ ያለው ምን ነበር?
5. በቁ.18-19 ላይ ኢየሱስ ስለራሱ ጥሪና አገልግሎት ይገልጻል፡፡ የእርሱ ትኩረት በማን ላይ ነው?

**ክፍሉ ለእኔ የሚሰጠው ትርጉም ምንድነው?**

1. ሰዎች በጣም የተቆጡት ለምንድነው? እዚህ አንድ ፍንጭ አለ፡- በዚያን ጊዜ አይሁድ ራሳቸውን ለእግዚአብሔር የተለዩ ሰዎች አድርገው ይቆጥሩ ነበር፡፡ በጣም የሚገርመው እግዚአብሔር በአይሁድ ፋንታ አሕዛብን እንዴት እንደወደዳቸውና እንደመረጣቸው ኢየሱስ ከብሉይ ኪዳን ሁለት ታሪኮችን ይናገራል፡፡
2. ሕዝቡ ኢየሱስን ያመሰግናሉ፤ነገር ግን ኢየሱስ በእነርሱ ላይ ጠንከር ያለ ንግግር አድርጓል፡፡ እርሱ ልባቸውን ያያል፡፡ ይህ እኛ ለኢየሱስ ስለምንሰጠው ምላሽ ምን ያስተምረናል?

3. እኔ ልከተል የምችለው ምሳሌ አለ?

ይህንን ታሪክ ከተማርኩ በኋላ ሕይወቴ እንዴት መለወጥ አለበት?

1. ይህንን ማጠቃለያ ሀሳብ አንብብና በዚህ ሳምንት ልትከተለው የምትችለው የኢየሱስ ምሳሌ ምን እንደሆነ ለቡድንህ አባላት አካፍል፡፡

ማጠቃለያ፡-

- ኢየሱስ የስልጣኑን ቃል በክፍተኛ ሁኔታ ተጠቅሟል፡፡
- እርሱ ይህንን የተጠቀመው ሰይጣንን ለማሸነፍ ነው፡፡
- እርሱ ማን እንደሆነ ለማሳየት ተጠቅሟል፡፡
- ሕዝቡንም ለመገሰጽ ተጠቅሟል፡፡
- ስለ አገልግሎት ለመግለጽ ቃሉን ተጠቅሟል፡፡

## ትምህርት-9

**መግቢያ**፡- በናዝሬት ከተማ የነበሩ የሃይማኖት መሪዎች እግዚአብሔር ለኢየሱስ ያስቀመጠውን ዕቅድ ኢየሱስ ሲናገር ሰሙና ተቆጡ፡፡ እንዲያውም ልገድሉት ሞከሩ፡፡ ኢየሱስ ሄዶ ተልዕኮውን መፈጸም ጀመረ፡፡

በሉቃ፡4፡31-44 ያለውን ታሪክ ተናገር፡፡

ታሪኩን አንብብ፡፡

**በዚህ ክፍል በቀጥታ የምመለከተው ምንድነው?** በክፍሉ ውስጥ የተጠቀሰው ማነው? ታሪኩ የተፈጸመው የት ነው? መቼ ተፈጸመ? በቦታው የሆነው ምንድነው? በክፍሉ ውስጥ የነበሩ ሰዎች አመለካከት ምን ነበር? እኔ መማር ያለብኝ በጊዜው የነበረው ልማድ ምን ነበር? ቀኑ ሰንበት ስለነበረ በቀን ምንም ሥራ መሥራት ስለማይቻል በመሸ ጊዜ ሰዎች አንድ የታመመ ሰው ወደ ኢየሱስ አመጡ፡፡

**የክፍሉ ትርጉም ምንድነው?** እነዚህ ሰዎች እዚህ ቦታ ለምን ተጠቀሱ? በክፍሉ ለተከሰቱ ነገሮች ምክንያት ምንድነው? በክፍሉ የነበሩ አመለካከቶች ምክንያት ምንድነው? ስለ ኢየሱስ አገልግሎት የምንማረው ምንድነው?

**ክፍሉ ለእኔ የሚሰጠው ትርጉም ምንድነው?** እኔ ልከተለው ወይም ልሸሸው የምገባኝ ምሳሌ አለ?

ይህንን ታሪክ ከተማርኩ በኋላ ሕይወቴ እንዴት መለወጥ አለበት?
ኢየሱስ፡- ‹‹ለሌሎች ከተሞች ስለ እግዚአብሔር መንግስት መመስከር አለብኝ፤ ምክንያቱም የተላኩት ለዚህ ነውና›› አለ፡፡

አንተስ ጥሪ አለህ? እዚህ ያለኸው ለምን እንደሆነ ታውቃለህ? እግዚአብሔር እንዲልክህ ትፀልያለህ?

## ትምህርት-10

በሕይወትህ በራስ መተማመንን የፈጠረልህ ክፍል የትኛው ነው? ነገሮችን በራስህ (ያለማንም እርዳታ) በደንብ ማከናወን የምትችለው በየትኛው የሕይወትህ ክፍል ነው?

በዚህ ታሪክ አንድ በዓሣ ማጥመድ ሥራ የታወቀ ሰው እንመለከታለን፡፡ ይህ ሰው ነገሮችን በራሱ የሚያከናውን ቢሆንም ኢየሱስን ሲያገኝ ስለ ሥራውና ስለ እግዚአብሔር አንድ አስደናቂ ነገር የተማረ ሰው ነበር፡፡

ከሉቃ፡5፡1-11 ያለውን ታሪክ ተናገር፡፡

ታሪኩን አንብብ፡፡
**በክፍሉ በቀጥታ የምመለከተው ምንድነው?** በክፍሉ ውስጥ የተጠቀሱ ሰዎች እነማን ናቸው? (ጴጥሮስ፣ ያዕቆብና ዮሐንስ ለአንድ ዓመት ኢየሱስን አውቀዋል ግን የእርሱ ደቀመዝሙር አልሆኑም፡፡) ታሪኩ የሆነው የት ነው? መቼ ሆነ? በክፍሉ ውስጥ የሆነው ምንድነው? በሰዎች ዘንድ የነበሩ አመለካከቶች ምንድናቸው? እኔ መማር ያለብኝ በሕዝቡ ዘንድ የነበሩ ልማዶች ምንድናቸው? *ዓሣ ለማጥመድ ወሳኝ ጊዜ ምሽት ሲሆን ጥልቀት የሌላቸው የውሃ ክፍሎች ይመቻሉ፡፡*

**የክፍሉ ትርጉም ምንድነው?** እነዚህ ሰዎች ለምን ተጠቀሱ? ኢየሱስ ወደ ጀልባው ለምን ገባ? በቁ.4 ላይ ኢየሱስ ስለ ተናገረው ነገር ጴጥሮስ ምን ተሰማው? እነዚህ አመለካከቶች ለምን በሰዎች ዘንድ ተነሡ? የዓሣው ቁጥር ጠቃሚ የሆነው ለምንድነው? የጴጥሮስ አመለካከት የተቀየረው እንዴት ነው? እነዚህ ሰዎች ሁሉን ነገር ትተው ኢየሱስን ለመከተል የወሰኑት ለምንድነው? ኢየሱስ አገልግሎቱን ብቻውን ለማድረግ ሀሳብ ነበረው?

**የክፍሉ ሀሳብ ለእኔ የሚሰጠው ትርጉም ምንድነው?** ኢየሱስን ለመከተል የሚያስከፍለኝ ዋጋ አለ? በዚህ ታሪክ ውስጥ ለመከተል ወይም ለመሸሽ ምሳሌ የሚሆነኝ ነገር አለ?

**ይህንን ታሪክ ከተማርኩ በኋላ ሕይወቴ እንዴት መለወጥ አለበት?**
ኢየሱስን መከተል ማለት በትክክል ምን ማለት ነው? ኢየሱስን የበለጠውን እንዳትከተል እንቅፋት የሚሆንህ ነገር አለ?

**ማጠቃለያ**፡- ኢየሱስ ዓሣ አጥማጁን የራሱ ተከታይ አደረገው፡፡ ኢየሱስ የእግዚአብሔርን መንግሥት ለማስፋት ተልዕኮ ስለ ነበረው ሰዎች ከእርሱ ጋር እንዲሠሩ መረጣቸው፡፡ በ1ቆሮ፡1፡26-31 ላይ እግዚአብሔር የዓለምን ደካማ ሰዎችን እንደመረጠ እንማራለን፡፡ እግዚአብሔር የእኛን የትምህርት ደረጃና ብቃታችንን አይመለከትም፡፡ ኢየሱስን

ለመከተል መታዘዝ ብቻ ይበቃል። እኛ ራሳችንን ለእግዚአብሔር ከፈቀድን እርሱ እኛን ፍሬ የምናፈራ ደቀመዛሙርት ሊያደርገን ይችላል።

## ትምህርት-11

የኢየሱስ አገልግሎት እየበዛ ሄደ። የኢየሱስ ዜና በአገር ሁሉ እየተስፋፋ በመሄዱ ብዙ ሕዝብም ሊሰሙትና ከደዌአቸው ሊፈወሱ ይሰበሰቡ ነበር። ይሁን እንጂ የሃይማኖት መሪዎች ኢየሱስን ይተቹት ነበር። ይህ ሁሉ ሲሆን ኢየሱስ ዘወትር ወደ ምድረ በዳ ፈቀቅ ብሎ መፀለዩን አላቋረጠም ነበር።
ታሪኩ ከሉቃ፡5 እንደሚከተለው ቀርቧል።

ከሉቃ፡5፡17-35 ታሪኩን አንብብ።
ታሪኩን አንብብ።

**በታሪኩ ውስጥ በቀጥታ የሚመለከተው ምንድነው?** በዚህ ክፍል የተፈጸሙ ሁለት ዋና ዋና ታሪኮች ምንድናቸው? የሃይማኖት መሪዎች የሚተቹት ምን ነበር? ኢየሱስ ለእነርሱ የሰጠው ምላሽ ምን ነበር?

**እኔ መማር ያለብኝ በጊዜ የነበሩ ልማዶች ምንድናቸው?** *ማቴዎስ ቀረጥ ሰብሳቢ በመሆኑ ከአይሁድ የተጠላና የተገለለ ሰው ነበር።*

**የክፍሉ ትርጉም ምንድነው**? ስለ ኢየሱስ የምትማረው ምንድነው? ስለ አገልግሎቱ የምትማረው ምንድነው? የሃይማኖት መሪዎች በትችት የተሞላ አመለካከት የነበራቸው ለምንድነው?

**ክፍሉ ለእኔ የሚሰጠው ትርጉም ምንድነው?** በሕይወቴ ልተገብረው የምችለው ትዕዛዝ ወይም የተገባልኝ ተስፋ ቃል ምንድነው? ለመከተል ወይም ለመሸሽ የሚገባኝ ምሳሌ አለ?

**ይህንን ታሪክ ከተማርኩ በኋላ ሕይወቴ እንዴት መለወጥ አለበት?**

**ማጠቃለያ**፡- ሉቃ፡5፡16 በቃልህ ተናገር (ነገር ግን ኢየሱስ ወደ ምድረ በዳ ፈቀቅ ብሎ ይፀልይ ነበር።) ኢየሱስ ሲፀልይ ሁሌ ለአይሁድ መሪዎች ትችት ምላሽ ለመስጠት ሃይል ያገኝ ነበር። ደቀመዛሙርቱን በጥበብ ይመርጥ ነበር። ከፀሎቱ በኋላ በአገልግሎቱ ላይ ያተኩር ነበር። አንተም የኢየሱስ ተከታይ ከሆንክ ተመሣሣይ ልምምዶችና ተግዳሮቶች ሊያጋጥሙህ ይችላሉ።

## ትምህርት-12

**መግቢያውን አንብብ፡-** ኢየሱስ ጠላቶቹን በጣም ስላስቆጣቸው እንዴት እንደሚገድሉት ይማከሩ ጀመር፡፡ ሌሎች ከደዌአቸው ሊፈወሱ ስለሚፈልጉ ኢየሱስን ይከተሉ ነበር፡፡ ኢየሱስ ተልዕኮ ስለነበረው ያንን ተልዕኮ ከግብ የሚያደርሱለትን ቡድን ማጠናከሩን ቀጠለ፡፡ ታሪኩ ከሉቃ፡6፡12-16 ቀርቧል፡፡
ታሪኩን በቃል ተናገር፡፡
ታሪኩን አንብብ፡፡

**በታሪኩ ውስጥ በቀጥታ የምመለከተው ምንድነው?** ኢየሱስ አሥራ ሁለቱን ከመምረጡ በፊት ያደረገው ምንድነው? ታሪኩ የሆነው የት ነበር? ታሪኩ የሆነው መቼ ነበር? በታሪኩ ውስጥ ያሉ አሥራ ሁለቱ እነማን ናቸው? ስለ እነዚህ ሰዎች የምታውቀው ምንድነው?

**የክፍሉ ትርጉም ምንድነው?** ኢየሱስ እነዚህን ሰዎች የመረጠው ለምንድነው? እነርሱ በዚህ ጊዜ የተመረጡበት ምክንያት ምንድነው?

**ክፍሉ ለእኔ የሚሰጠው ትርጉም ምንድነው?** አንድን ሰው አቅደህ ደቀመዝሙር ለማድረግ መርጠሃል? ደቀመዝሙርነት ማለት ኢየሱስን ለመከተል፣ለእርሱ ለመታዘዝና የእግዚአብሔርን መንግሥት ለማስፋት የድርሻን ለመወጣት መወሰን ማለት ነው:: ደቀመዝሙርነት ሕብረት በማድረግና አንዱ ሌላውን ወደ ክርስቶስ ፍጹም ሙላት እንዲያድግ በመርዳት ላይ የተመሠረተ ነው፡፡ ስለ ደቀመዝሙርነት ያለህን ልምድ ለቡድንህ አባላት አካፍል፡፡ አንተ የደቀመዝሙር ስልጠና ወስደሃል?

**ይህንን ታሪክ ከተማርኩ በኋላ ሕይወቴ እንዴት መለወጥ አለበት?** ኢየሱስ ማንኛውንም ውሳኔ ከመውሰዱ በፊት ይፀልይ ነበር፡፡ ስለዚህ ደቀመዝሙር ለማድረግ የምትችለውን ሰው ከመምረጥህ በፊት ፀልይ፡፡ የዚህን ሰው ስም ጠርተህ ፀልይ፡፡ ወይም አንተን ደቀመዝሙር ለማድረግ የሚችል ሰው እግዚአብሔር እንዲሰጥህ ፀልይ፡፡

## ትምህርት-13

## የሕብረትና የፀሎት ቀን

በዚህ በሕብረትና በፀሎት ቀን አንዳችሁ ለአንዳችሁ ፀልዩ፡፡ በዚህ ጊዜ አንድን አባል ስለ ሕይወቱ፣ ስላለፈው ታሪኩና በሕይወቱ ምን እንደሚያስደስተው እርስ በርሳችሁ ተጠያየቁ፡፡

## ትምህርት-14

***የቡድንህን አባለት፡-*** *የእሁድ ቀን እንዴት እንደሚያሳልፉ ጠይቅ፡፡ እረፍት በማድረግ ነው ወይስ በመሥራት?*

***መግቢያውን አንብብ፡-*** ኢየሱስ በሰንበት ቀን በመወሱ የሃይማኖት መሪዎችን አስቆጣቸው፡፡ በሰንበት መልካም ሥራ መሥራትና የታመሙትን መንከባከብ እንደሚቻል አስተማራቸው፡፡ ከዛ በኂላ አሥራ ሁለቱን መርጦ ማስተማር ጀመረ፡፡ ኢየሱስ የሚናገረውን ሕይወት መኖር በእግዚአብሔር ሃይል ካልሆነ ከባድ ነው፡፡

በሉቃ፡6፡17-36 ያለውን ታሪክ በቃልህ ተናገር፡፡
ታሪኩን አንብብ፡፡

**በታሪኩ ውስጥ በቀጥታ የምመለከተው ምንድነው?** ኢየሱስ የሚያስተምረውን ማንን ነው? የት ነው የሚያስተምረው? በታሪኩ ውስጥ ያሉ ቁልፍ ቃላት የትኞቹ ናቸው? ‹‹ብፁዓን›› (የተባረከ) እና ‹‹ወዮላችሁ›› የሚሉትን ቃላት በጥንቃቄ ተመልከት፡፡ ከዚህ ምን ትማራለህ?
የተራቡና የጠገቡ፣ ድሆችና ባለጠጎች እነዚህንና ሌሎች ተቃራኒ ሀሳብ ያላቸውን ቃላት ፈልግ፡፡
‹‹ሽልማት›› የሚለውን ቃል ተመልከት፡፡ ከዚህ የምትማረው ምንድነው? ኢየሱስ እኛ እንድናደርግ የሚነግረን ከባዱ ነገር ምንድነው?

**የክፍሉ ትርጉም ምንድነው?** እግዚአብሔር እነዚህን ሰዎች የሚሸልመው ለምን ይመስልሃል? እኛ ይቅር ባዮች፣ለጋሾችና ሌሎችን የምንወድ ሰዎች እንድንሆን ኢየሱስ የሚነገረን ለምንድነው? ቁ.32-34 እንደገና ተመልከት፡፡ እግዚአብሔር የሚያስተምረውን ለመረዳት ሐጢአተኞችንና የእግዚአብሔርን ልጆች አነጻጽር፡፡

**ክፍሉን ለመረዳት የሚጠቅሙ ነገሮች፡** ኢየሱስ የደቀመዛሙርቱን አዲስ ሕይወት ለማስተማር ማነጻጸሪያዎችን ይጠቀማል፡፡ እኛ ከዓለም የተለየን ሰዎች እንድንሆን እርሱ ይፈልጋል፡፡ ዓለሙን የሚከተል ሰው ራስ ወዳድና በቁጣ የተሞላ ነው፡፡ ነገር ግን የኢየሱስ ተከታይ እንደ እግዚአብሔር ሀሳብ ሩህሩህ፣ለጋሽና ለጠማማም እንኳን ሳይቀር ይቅር የሚል ነው፡፡ የሚገርመው ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጆች ልዩ መሆናቸውን ለማሳየት ቀኝ ጉንጭን ለሚመታ ግራ ጉንጭ ማሳየት እስከሚገባ ድረስ ጠንካራ ምሳሌ ሲጠቀም እናያለን፡፡

**ክፍሉ ለእኔ የሚሰጠው ትርጉም ምንድነው?** ኢየሱስ ለደቀመዛሙርቱ እየተናገረ ነው፡፡ ያለ መንፈስ ቅዱስ እርዳታ እነዚህን ትዕዛዛት መተግበር አንችልም፡፡ እኛ ኢየሱስን የምንከተል ሰዎች ከሆንን ለእኛ የተገባው ተስፋ ቃል ምንድነው? እኔ መከተል ወይም መሸሽ ያለብኝ ምሳሌ አለ?

**ይህንን ታሪክ ከተማርኩ በኂላ ሕይወቴ እንዴት መለወጥ አለበት?** በዚህ ሳምንት ልታደርገው ያቀድከውን አንድ ነገር ለቡድንህ አባላት አካፍል፡፡

## ትምህርት-15

**መግቢያውን አንብብ፡-** ኢየሱስ ተከታዩቹ በዓለም ላይ ካሉ ሰዎች የተለዩ እንዲሆኑ ይፈልጋል። እኛ ጠላቶቻችንን እንድንወድ፣ መልካም ሥራ እንድንሠራና ሌሎችን ይቅር የምንል ሰዎች እንድንሆን ኢየሱስ ያስተምረናል። በሌሎችም ላይ እንዳንፈርድ ያስጠነቅቀናል። ይህ ማለት አንድ ሰው ሲሳሳት እያየን ዝም እንድንል አይደለም። ነገር ሌሎችን ድካም ብቻ እያየን ጊዜ ከማጥፋት የራሳችንንም ድካም መመልከት አለብን። ቀጣዩን ታሪክ ስንማር ስለዚህ ጉዳይ አስብ።

በሉቃ፡6፡43-49 ያለውን ታሪኩን ተናገር።
ታሪኩን ተናገር።

**በታሪኩ ውስጥ በቀጥታ የምመለከተው ምንድነው?** ኢየሱስ የሚናገረው ለማን ነው? (ቁ.20 እና 42 እንደገና ተመልከት።) ስለ መልካምና ክፉ ሰዎች የተቀመጠው መመሪያ ምንድነው? ልብና አፍ የተያያዙ ስለ መሆናቸው የምትማረው ምንድነው?

**የክፍሉ ትርጉም ምንድነው?** የአንዳንድ ሰዎች ሕይወት ሲበላሽ የአንዳንዱ ጠንካራ ሆኖ የሚቀጥለው ለምንድነው? ኢየሱስ ሌሎችን ስለሚፈርዱ ግብዞች ካስተማረ በኋላ ስለ ፍሬና ስለ ቤቶች የሚያስተምረው ለምንድነው? እነዚህን የሚያገናኘው ምንድነው?

**ክፍሉ ለእኔ የሚሰጠው ትርጉም ምንድነው?** ሰው በልቡ የሞላውን በአፉና በባሕሪው ያሳያል። እውነተኛ እምነታችን በየቀን ኑሮአችን ላይ እንዴት ተጽዕኖ ሊያመጣ እንደሚችል ከቡድንህ አባላት ጋር ተወያይ። መናዘዝ ያለብኝ ሐጢአት አለ?

**ይህንን ታሪክ ከተማርኩ በኋላ ሕይወቴ እንዴት መለወጥ አለበት?**
ቁ. 46 በቃልህ ተናገር፡- ‹‹ ስለ ምን ጌታ ሆይ፣ጌታ ሆይ ትሉኛላችሁ? የምለምነውንም አታደርጉም?››

የተሰወሩ ሐጢአቶችን እግዚአብሔር እንዲያሳይህ ፀልይ።

ከዚህ ታሪክ የተነሣ በዚህ ሳምንት ልታደርግ ያለኸውን ለቡድንህ አባላት ተናገር።

## ትምህርት-16

እምነት ብዙ ጊዜ የምንሰማው ቃል ነው። አንተ እምነት ለሚለው ቃል ምን ዓይነት ትርጉም ልትሰጥ ትችላለህ?

**መግቢያውን አንብብ፡-** በዚህ ጥናት እምነት የሚለውን ቃል ለየት ባለ መልክ እንመለከታለን። ከኢየሱስ ተግባራዊ እርዳታ የፈለገውን አንድ የሮማ ወታደር እንመለከታለን። ኢየሱስ በገሊላ ከተማ አጠገብ በሚትገኘው ቅፍርናሆም ከተማ ነበረ።

ይህ ቦታ የት እንደሚገኝ ለማወቅ ከፈለግህ በዚህ ጥናት መጨረሻ ላይ በሚገኘው ካርታ ላይ መመልከት ትችላለህ፡፡

በሉቃ፡7፡1-10 ላይ ያለውን ታሪክ ተናገር፡፡
ታሪኩን አንብብ፡፡

**በታሪኩ ውስጥ በቀጥታ የምመለከተው ምንድነው?** በታሪኩ ውስጥ ያሉትን የተለያዩ ሰዎች ስም ጥቀስ፡፡ የመቶ አለቃው ወደ ኢየሱስ እንዴት ነው የቀረበው? የአይሁድ ሽማግሌዎች የነበራቸው አመለካከት ምንድነው? ከዚያ በኋላ የሆነው ምንድነው? እኔ መማር ያለብኝ በጊዜው የነበሩ ልማዶች ምንድናቸው? ይህ የመቶ አለቃ የሮማ ወታደር ሲሆን በመቶ ሰዎች ላይ ሥልጣን ነበረው፡፡ ሰዎች አብዛኛውን ጊዜ በአካባቢያቸው ስለ ሰፈሩ ወታደሮች ያላቸው አመለካከት ምንድነው? ለምሳሌ ኢትዮጵያዊያን ለጣሊያን ወታደሮች የነበራቸው አመለካከት ምን ነበር? የመቶ አለቃው ከአይሁድ ሕዝብ ጋር የነበረው ግንኙነት ምን ነበር? ወይም አይሁድ እንዴት ተቀበሉት?

**የክፍሉ ትርጉም ምንድነው?** ኢየሱስ ከመሪዎችና ከሽማግሌዎች ጋር የሄደው ለምንድነው? የመቶ አለቃው ከኢየሱስ እርዳታ የጠየቀው ለምን ይመስልሃል? የመቶ አለቃው በኢየሱስ ላይ እውነተኛ እምነት እንደነበረው ያሳየው እንዴት ነው? ስለ እውነተኛ እምነት የምትማረው ምንድነው?

**ክፍሉ ለእኔ የሚሰጠው ትርጉም ምንድነው?** ስለ ኢየሱስና እርሱ ለሕዝቡ ስላለው ርህራሄ የምትማረው ምንድነው? እኔ እንድከተለው ወይም እንድሸሸው ምሳሌ የሚሆነኝ ነገር አለ?

**ይህንን ታሪክ ከተማርኩ በኋላ ሕይወቴ እንዴት መለወጥ አለበት?**
በዚህ ሳምንት ኢየሱስ ምን እንዲያደርግልህ ነው የምታምነው? ይህንን እምነት በተግባርና በአስተሳሰብ እንዴት ማሳየት ትችላለህ?

***ማጠቃለያ***፡- ይህንን ታሪክ በሉቃ፡8፡22-25 ባለው ኢየሱስ ማዕበሉን ፀጥ ካደረገው ታሪክ ጋር ማነጻጸር ትችላለህ፡፡ ኢየሱስ ደቀመዛሙርቱን፡- ‹‹እምነታችሁ የት ነው? ›› አላቸው፡፡ እነዚህ ደቀመዛሙርት የመቶ ዓለቃው እምነት አልነበራቸውም፡፡ የኢየሱስን ማንነትና በዓለም ላይ ስላለው ስልጣን ገና በመረዳት ሂደት ላይ ናቸው፡፡ አንተስ በየትኛው ደረጃ ላይ ነህ?

## ትምህርት-17

በሕይወትህ የሰው ማጽናናት ያስፈለገህበት ጊዜ የትኛው ነው?

***መግቢያውን አንብብ፡-*** ኢየሱስን ለመከተል ከወሰንክ የምትከተለው ማን እንደሆነ ማወቅ አለብህ፡፡ እርሱ በዚህ ዓለም ሲኖር በችግርና በመከራ ያሳለፈበትን ባሕሪውን በትክክል ማየት አለብህ፡፡ እርሱ በዙሪያው ለነበረው ሕዝብ ሲሰጥ የነበረውን ምላሽ ማጥናት አለብህ፡፡ የዛረው ታሪክ አጭር ነው ግን በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ ስለዚህ ታሪክ ጊዜ ወስደህ አስብበት፡፡

በሉቃ፡7፡11-17 ያለውን ታሪክ በቃል ተናገር፡፡

ታሪኩን አንብብ፡፡

**በክፍሉ ውስጥ በቀጥታ የምመለከተው ምንድነው?** በዚህ ክፍል የነበሩ ሁለት ዓይነት ሰዎች የትኞቹ ናቸው? ታሪኩ የሆነው የት ነው? ናይን የሚትባለው ትንሽ የመንደር ከተማ ነበረች፡፡ ኢየሱስ በሕዝቡ መካከል ያየው የመጀመሪያው ሰው ማን ነበር? ለዚህች ሴት ኢየሱስ የሰጠው ምላሽ ምን ነበር? ቀጥሎ ኢየሱስ ያደረገው ምን ነበር?

እኔ መማር ያለብኝ በጊዜው የነበሩ ልማዶች ምንድናቸው? ለአይሁድ ሴት የነበራት ታላቁ ደስታ ልጅ ማግኘት ነበር፡፡ ይህች ሴት ባልዋንና ልጇን በሞት ያጣች ስለነበረች የሚንከባከባት ሰው አልነበራትም፡፡ የድህነት ኑሮ ትኖራለች፡፡ እንዲሁም የልጇ በለጋነት መሞቱ የሐጢአት ቅጣት ተደርጎ ይወሰድ ነበር፡፡ ከዚህም የተነሣ ይህች ሴት በእፍረትና ራሷን እንደ ጥፋተኛ አድርጋ ትኖር ነበር፡፡ በከተማው የነበሩ ምናልባትም 500 የሚያህሉ ሕዝብ ይህችን ሴትና ልጇን ይከተሉ ነበር፡፡ ከኢየሱስ ጋር የነበረው ሕዝብ ቁጥር ብዙ ሊሆን ይችላል፡፡ ከዚህም የተነሣ ሕዝቡ በትንሽ መንገድ ይሰበሰቡና በጊዜው የነበረውን ሁኔታ ያጨናንቁ ነበር፡፡ በሙሴ ሕግ መሠረት የሞተን ሰው መንካት መርከስ ነው፡፡ ብዙውን ጊዜ ሰው ከእንደዚህ ዓይነት ችግር ይሸሻል፡፡

**የክፍሉ ትርጉም ምንድነው?** ብዙ ሕዝብ ከኢየሱስ ጋር ስላለ ኢየሱስ ይህንን አጋጣሚ ተጠቅሞ ሃይሉን ለማሳየትና ለማስተማር ፈለገ፡፡ ይሁን እንጂ ታሪኩ፡ ‹‹ጌታ እርሷን አየ›› ይላል፡፡ ዛሬም ጌታ እያንዳንዱን ሰው የሚያይ ዓይን አለው፡፡ ኢየሱስ መበለቷን አታልቅሺ ያላት ለምንድነው? ኢየሱስ የሞተውን ሰው ቀስ ብሎ ሄዶ ያስነሣው ለምንድነው? ሕዝቡ በመገረም ላይ ሳሉ ኢየሱስ ትኩረቱን በሴቷ ላይ በማድረግ ልጁን ወደ እናቱ አመጣ፡፡ ለኢየሱስ ስለነበረው ርህራሄ የምንማረው ምንድነው?

**ክፍሉ ለእኔ የሚሰጠው ትርጉም ምንድነው?** አንድ ሰው ርህራሄ እንዳለው ወይም እንደሌለው እንዴት ማወቅ ትችላለህ? በሌሎች ላይ ያለውን መውደድ ለማሳየት ዋጋ ስለ መክፈል ዛሬ የተማርከው ምንድነው?

**ይህንን ታሪክ ስለተማርኩ ሕይወቴ እንዴት መለወጥ አለበት?**
ከዚህ በታች ያለውን ‹‹ፍቅር በመካከላችን ተመላለሰ›› የሚለውን የፓውል ሚሌር (Paul Miller) አንብብ፡-

> *ኢየሱስ እንዴት መውደድ እንዳለብን አሳይቶናል፡- በመጀመሪያ ማየት፣ስሜቱን መጋራትና ከዚያም መርዳት፡፡ ለአንድ ሰው እርዳታ ብንሰጥ ነገር ግን የዚያን ሰው ችግር ካላየንና ስሜቱን ካልተጋራን ፍቅራችን ቀዝቃዛ ነው የሚሆነው፡፡ አንድን ችግረኛ ብናይና ስሜቱን ብንጋራ ነገር ግን ለችግረኛው የሚያስፈልገውን እርዳታ ባንሰጥ ፍቅራችን እርካሽ ነው የሚሆነው፡፡ ፍቅር ሁለቱንም ያደርጋል፡፡*

ሰዎችን እጎዳ ይሆናል ብለህ ሸሽተህ ታውቃለህ? ምናልባት አንድን ሰው ብትወድ ያ ሰው ለራሱ ሊጠቀመኝ ይችላል ወይም አንድ ነገር አጣ ይሆናል የሚል ስጋት አለህ? በሕይወትህ ተለውጠህ የኢየሱስን ምሳሌ እንዴት መከተል ትችላለህ?

***ማጠቃለያ***፡- የዚህች መበለት ስሜት ለኢየሱስ ተሰማው፡፡ ኢየሱስ ወደ ልቧ ገባ፡፡ ራሱን በእርሷ ቦታ አደረገ፡፡ እኼ ነው ርህራሄ ማለት!! ሕዝቡ እንኳን ሲያመሰግኑት እርሱ ግን ዓይኑን ከእርሷ ላይ አላነሳም ነበር፡፡ ሌሎችን መውደድ ማለት ጊዜአችንን በመስጠት፣ በገንዘባችን በመርዳት መሆን እንዳለበት ኢየሱስ አሳይቶናል፡፡ በዚያን ጊዜ በሌላው ላይ ትኩረት የሚያደርግ አገልጋይ እንሆናለን፡፡

## ትምህርት-18

ስለ እምነት መማራችንን እንቀጥላለን፡፡ መጥምቁ ዮሐንስ በእሥር ቤት በነበረ ጊዜ ስለ ኢየሱስ መጠራጠር ጀመረ፡፡ ኢየሱስ ለዮሐንስ ራርቶ በቃሉ ያበረታታው ነበር፡፡ እኛ ሁላችንም በእምነታችን እያደግን እንዳለን ኢየሱስ ይገባዋል፡፡ ስለ አንዲት ሴትና ስለ እምነቷ የሚያጠነጥን ታሪክ ከዚህ በታች ቀርቧል፡፡ ኢየሱስ ለዚህች ሴት ያሳየውን ርህራሄ እንደገና አድምጥ፡፡

ከሉቃ፡7፡36-50 ያለውን ታሪክ ተናገር፡፡
ታሪኩን አንብብ፡፡

**በክፍሉ ውስጥ በቀጥታ የምመለከተው ምንድነው?** ኢየሱስ ያለው የት ነው? በታሪኩ ውስጥ ያለው ማነው? ሴትዮዋ የተገለጸችው እንዴት ነው? ሥራዋ ምንድነው? ከዚህ በኋላ የሆነው ምንድነው? በእነዚህ ሰዎች ውስጥ የነበሩ አመለካከቶችና ስሜቶች ምንድናቸው? እኔ መማር ያለብኝ በጊዜው የነበሩ ልማዶች ምንድናቸው? በዚያን ጊዜ ወንዶች በሴቶች ላይ የነበራቸው አመለካከት ምን ነበር? አስፈላጊ የሆኑ ቁልፍ ቃላት የትኞቹ ናቸው?

**የክፍሉ ትርጉም ምንድነው?** ይህች ሴት እምነቷን ያሳየችው እንዴት ነው? ስምዖን ስለ ኢየሱስ ምን ተሰማው? በቁ.40-43 ያለው ታሪክ የሚያስተምረው ትምህርት ምንድነው? በዚህ ክፍል ክፉኛ ሐጢአተኛ ማነው? ሴትዮዋ ናት ወይስ ስምዖን? ለምን?

**ክፍሉ ለእኔ የሚሰጠው ትርጉም ምንድነው?** ወደ ኢየሱስ ስለመምጣት የምንማረው ምንድነው? ሐጢአታቸው ከተሰረየላቸው ሰዎች ሕይወት ኢየሱስ የሚፈልገው ምላሽ ምንድነው? በታሪኩ ውስጥ ካሉ ሰዎች የትኛውን ትመስላለህ? ለምን?

**ይህንን ታሪክ ከተማርኩ በኋላ ሕይወቴ እንዴት መለወጥ አለበት?**
አንድ ሰው ለእውነተኛ እምነት የሚወስዳቸው ደረጃዎች ምንድናቸው? ይህች ሴት ለኢየሱስ የነበራት ፍቅር ምን ይመስላል? በዚህ ሳምንት ለእግዚአብሔር ያለህን ፍቅር እንዴት ትገልጻለህ?

***ማጠቃለያ***፡- ይህች ሴት በፍጹም ንሥሐ ወደ ኢየሱስ የተመለሰች፣ለኢየሱስ ጥልቅ ፍቅር የነበራትና ኢየሱስ ላደረገላት ነገር የሚታመሰግን ሴት ናት፡፡ ኢየሱስ እንደሚወድህ እንዳታምን የሚከለክልህ ነገር ምንድነው? ሐጢአት ነው ወይስ ትዕቢት? ኢየሱስ ሊቀበልህ ዝግጁ ነው፡፡

## ትምህርት-19

***መግቢያውን አንብብ፡-*** ኢየሱስ 12 ደቀመዛሙርትና ሌሎች ተከታዮች ነበሩት፡፡ እነርሱም አንድ ላይ የሚውሉ፣ በሕብረት የሚበሉ፣ በአንድነት የሚፀልዩና የሚያገለግሉ ነበሩ፡፡ የዛሬው ታሪክ ቀጥሎ ቀርቧል፡፡

በሉቃ፡8፡1-3 ያለውን ታሪክ ተናገር፡፡
ታሪኩን አንብብ፡፡

**ከዚህ በታች ባሉ ጥያቄዎች ላይ ከቡድንህ አባለት ጋር ውይይት አድርግ፡፡**

1. ኢየሱስን ስለተከተሉ ሴቶች የምትማረው ምንድነው?
2. በአይሁድ ባሕል መሠረት ወንድ አስተማሪዎች ሴቶችን አያስተምሩም ነበር፡፡ ኢየሱስ ይህችን ሴት ከደቀመዛሙርቱ ጋር እንድትቆይ በማድረጉ ደቀመዛሙርቱን ሊያስተምር የፈለገው ምንድነው?
3. ደቀመዝሙር ስለ ማድረግ ከኢየሱስ ዘዴ የምትማረው ምንድነው?

ዛሬ አንዳችሁ ለአንዳችሁ ፀልዩ፤ሕብረትም አድርጉ፡፡ በሕብረት ስትፀልዩ አንድ የቡድን አባል የፀሎት ርዕስ ቢሰጥ በጎኑ ያለው ሰው ሊፀልይለት ይችላል፡፡ እያንዳንዱ የቡድን አባል የራሱን የፀሎት ርዕስ እንዲያካፍልና እያንዳንዱ ሰው በአጠገቡ ላለው ሰው እንዲፀልይ አድርግ፡፡

## ትምህርት-20

***መግቢያውን አንብብ፡-*** ኢየሱስ አብዛኛውን ጊዜ በምሳሌ ያስተምር ነበር፡፡ ምሳሌ ማለት በሰዎች የየቀን አኗኗር ጋር የተያያዙትን፡- አፈር፣ዘር፣ብርሃን፣ዛፎች ወይም ሰዎችን በመጠቀም የሰማያዊውን እውነት ማስተማሪያ መንገድ ነው፡፡ ምሳሌዎች የአንድን ሰው አስተሳሰብ ለመቀየር የሚጠቅሙ ቀላል ታሪኮች ናቸው፡፡ በኢየሱስ ዘመን የነበሩ የሃይማኖት መሪዎች የእነዚህን ቀላል ታሪኮች ትርጉም መረዳት አቃታቸው፡፡ በኢየሱስ እምነት ስላልነበራቸው የእግዚአብሔር ማንነት ሊረዱ አልቻሉም፡፡ ዛሬ የምሳሌዎቹ መልዕክት እንዳያመልጣችሁ፡፡

በሉቃ፡8፡4-15 ያለውን ታሪክ በቃል ተናገር፡፡
ታሪኩን አንብብ፡፡

ኢየሱስ የሚያስተምረው ማንን ነበር?
ኢየሱስ በምሳሌ የሚያስተምረው ለምንድነው?
ኢየሱስ በምሳሌዎቹ የሚሰጠው ትርጉም ምንድነው?
እነዚህ ምሳሌዎች ከእግዚአብሔር ቃል ጋር የሚገናኙት እንዴት ነው? ለመጽሐፍ ቅዱስ ምላሽ ለመስጠት የተማርካቸው የተለያዩ መንገዶች ምንድናቸው?

በዚህ ክፍል ቁልፍ ቃላት ማመንና እምነት የሚሉት ናቸው። እነዚህን ቃላት ፈልግና ውይይት አድርግ። የሚሰማ ጆሮ ያለው ይስማ ማለት ምን ማለት ነው? የልብህ አፈር ምንድነው? እንዴት ታውቃለህ?

**ይህንን ታሪክ ስለተማርኩ ሕይወቴ እንዴት መለወጥ አለበት?**
ኢየሱስን ስለ መከተል የተማርከው ምንድነው?

## ትምህርት-21

***መግቢያውን አንብብ፡-*** ኢየሱስና ደቀመዛሙርቱ በገሊላ አልፈው ሄዱ። ባሕሩን ተሻግረው ወደ አሕዛብ ክልል ገቡ። ይህ ቦታ አሥሩ ከተሞች የሚል ስያሜ አለው። አሕዛብ ለገቢ ምንጫቸው አሳማ ያረቡ ነበር። ታሪኩ ከእግዚአብሔር ቃል እንደሚከተለው ቀርቧል።

በሉቃ፡8፡26-39 ያለውን ታሪክ በቃል ተናገር።
ታሪኩን አንብብ

1. **በክፍሉ ውስጥ በቀጥታ የሚመለከተው ምንድነው?** ማን? የት? መቼ? ምን ሆነ? በክፍሉ ውስጥ ያሉ አመለካከቶች ምንድናቸው? እኔ መማር ያለብኝ በጊዜው የነበሩ ልማዶች ምንድናቸው? ክፍለ ጦር ማለት ከ3000-6000 ያህል ሠራዊትን የሚይዝ ነበር።
2. **የክፍሉ ትርጉም ምንድነው?**
   ሀ. እነዚህ ሰዎች በዚህ ክፍል ለምን ተገለጹ?
   ለ. የከተማው ሕዝብ ኢየሱስን ያልተቀበለው ለምንድነው?
   ሐ. ኢየሱስ እነዚህን አጋንንቶች ያላጠፋው ለምንድነው?
   መ. ኢየሱስ ሰውዬውን ወደ ቤቱ የላከው ለምንድነው?
3. **ክፍሉ ለእኔ የሚሰጠው ትርጉም ምንድነው?**
   ሀ. እግዚአብሔር ዛሬ በዓለም ላይ ያለውን ክፋት በሙሉ የማያጠፋው ለምንድነው?
   ለ. አሳማዎቹ (እሪያዎቹ) ቢጠፉ የሕዝቡ ኢኮኖሚ ይጎዳ ነበር። ነፃ የወጣው ሰውና ኢየሱስ ሳይሆን ያሳሰባቸው ገንዘባቸው ብቻ ነበር። ገንዘብን በተመለከተ ኢየሱስ የሚያስተምረን ምንድነው?

**ይህንን ታሪክ ስለተማርኩ ሕይወቴ እንዴት መለወጥ አለበት?**
ኢየሱስን ስለመከተል ዛሬ የተማርከው ምንድነው?

# ትምህርት-22

***መግቢያውን አንብብ፡-*** ዛሬ በሁለት ሰዎች እምነት ላይ ትኩረት የሚያደርጉ ሁለት ታሪኮች እናያለን፡፡ እነዚህም፡-ለታመመችው ልጁ እርዳታን የሚፈልገው አንድ ገዥና ከእርኩሰቷ ልድትድን የምትፈልግ አንዲት ሴት ናቸው፡፡ ኢየሱስ ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ በሚዘዋወርበት ጊዜ በመንገድ ላይ እየቆመ እርዳታን ፈልገው ወደ እርሱ የሚመጡትን ይረዳቸው ነበር፡፡ ይህንን ታሪክና ስለ እምነት የተነገረውን ትምህርት ስማ፡፡

በሉቃ፡8፡40-56 ያለውን ታሪክ በቃል ተናገር፡፡
ታሪኩን ተናገር፡፡

***በክፍሉ ውስጥ በቀጥታ የምመለከተው ምንድነው?*** ማን? የት? መቼ? ምን ሆነ? በክፍሉ በጊዜው የነበሩ አመለካከቶች ምንድናቸው? በክፍሉ ውስጥ ያሉ ቁልፍ ቃላት ምንድናቸው?

1. እኔ መማር ያለብኝ በጊዜው የነበሩ ልማዶች ምንድናቸው? ምኩራብ ማለት አይሁድ የሚያመልኩበት ቦታ ነው፡፡ የምኩራቡ መሪ አምልኮን በበላይነት ይቆጣጠራል፡፡ ለአንድ የምኩራብ መሪ በሰው እግር ላይ መውደቅ ያልተለመደ ተግባር ነው፡፡ ስለዚህ ገዥና ለእርሱ ስለነበረው አመለካከት የምትማረው ምንድነው?
2. በአይሁድ ሕግ መሠረት ደም የሚፈሳትን ሴት መንካት ያረክሳል፡፡ በዘሌ፡15 ላይ እንደሚናገረው የአይሁድ ወንዶች ለአምልኮ ወደ ምኩራብ መግባት ይችሉ ዘንድ ሴቶችን መንካት ይቅርና በዓይናቸው እንኳን አያዩአቸውም፡፡
3. በገዢውና በሴትዬዋ ላይ ኢየሱስ የነበረው አመለካከት ምን ነበር?

***የክፍሉ ትርጉም ምንድነው?*** ይህች ሴት በስሜቷ፣በሥጋዋና በገንዘቧ የተጨነቀችው እንዴት ነው? ኢየሱስ ‹‹ማነው የነካኝ?›› ብሎ የጠየቀው ለምንድነው? ከዚህች ሴትዬዋና ከእምነቷ የምትማረው ምንድነው? ኢየሱስ ኢያይሮስን አትፍራ ያለው ለምንድነው?

***ክፍሉ ለእኔ የሚሰጠው ትርጉም ምንድነው?*** ሕይወት ውጣ ወርድ የሞላባት ናት፡፡ ሰዎች በሕመም ይሰቃያሉ፣ ልጆቻቸውንም በሞት ያጣሉ፡፡ በእነዚህ ታሪኮ ላይ እኛ በምንፈራቸው ነገሮች ላይ ኢየሱስ ሃይል እንዳለው እናያለን፡፡ ኢየሱስ ከእኛ እምነትን ይፈልጋል፡፡ እምነታችንን በእርሱ ላይ እንድንጥል ይፈልጋል፡፡ ታዲያ ይህ ማለት ኢየሱስ ሁል ጊዜ ከበሽታችንና ከሞት ነፃ ያወጣናል ማለት ነው? ራዕይ፡21፡4 አንብብ፡፡ ምንም እንኳ ኢየሱስ ከሚደርስብን መከራ ነፃ ባያወጣንም በእርሱ መታመን የሚያስፈልገው ለምንድነው? ኢየሱስ ሕዝቡ ተአምራትን አይቶ ሳይሆን እንዲሁ እንዲከተሉት ይፈልጋል፡፡ ጤናማ መንፈስ እንዲኖራቸው ይፈልጋል፡፡ ዛሬ ስለ ኢየሱስ የተማርከው ምንድነው?

***ይህንን ታሪክ ስለተማርኩ ሕይወቴ እንዴት መለወጥ አለበት?***
በሕይወትህ እየደረሰብህ ያለ መከራ ምንድነው? ለዚህ ምን ማድረግ አለብህ?

**አሁን ቆም ብለህ አስብ:**
ኢየሱስ ኢያይሮስ የተባለ አንድ የትልቅ ሰው ሴት ልጅ ሊፈውስ እየሄደ ነው። ይህች ትንሽ ልጅ ሞታ ነበር። እርሱ እየሄደ በመንገድ ላይ ሳለ ብዙ ሕዝብ ይጋፉት ነበር። ***በጣም የሚገርመው ምንም እንኳ ኢየሱስ አንድ አንገብጋቢ ተልዕኮ ከፊቱ ቢጠብቀውም ለዚህች ሴት ሲል ቆመ***፡ ለኢየሱስ ይህች ሴትና ችግሯ ከሌላው ነገር ሁሉ ይልቅ በጣም አስፈላጊ ነበሩ። በዛች ሰዓት የኢየሱስን ትኩረት ሙሉ በሙሉ የሳበችው እርሷ ነበረች። ይህች ከሰው የተገለለች፤ማንም ግድ የማይላትና የማይፈልጋት ሴት እግዚአብሔር ደረሰላት፤ ምክንያቱም እምነቷ እንደ ልጅ እምነት ነበር።

## ትምህርት-23

***ታሪኮችን ከሕይወትህ ጋር ማዛመድ እንድትችል በመጽሐፉ መጀመሪያ አካባቢ የተቀመጡትን መመሪያዎች እንደገና ከልስ። ይህ ታሪክ አንዳንድ ጊዜ ከሁሉም ወንጌላዊያን ሕይወት ጋር ይዛመዳል። ይህ ማዛመድ ትክክል ነው ትላለህ? የዚህን ታሪክ ዋና ነጥብ ለማግኘት በጥንቃቄ ማንበብና መፀለይ አለብህ።***

**መግቢያውን አንብብ፡- የዛሬው *ታሪክ* ኢየሱስ በደቀመዛሙርቱ ላይ የነበረውን *መሪነት* ሰፋ ባለ መልክ ያሳያል። እርሱ የእግዚአብሔርን መንግስት ለመመሥረት ዕቅድ እንደነበረው *ታስታውሳለህ*። ይህንን ብቻውን አይደለም የሚያደርገው። *አሥራ* ሁለቱን በሥራው ይተባበሩ ዘንድ አሰለጠናቸው። በእግዚአብሔር መንግሥት *ሥራ* ውስጥ የአንተን ድርሻ እግዚአብሔር እንዲያሳይ ፀልይ። *ታሪኩ* ከዚህ በታች ቀርቧል።**

በሉቃ፡9፡1-6 እና ቁ.10 *ያለውን ታሪክ* በቃል ተናገር።
*ታሪኩን* አንብብ።

**በክፍሉ ውስጥ በቀጥታ የምመለከተው ምንድነው?**

1. ኢየሱስ በአንድነት የሰበሰበው ማነው? ኢየሱስ 12ቱን ወዴት ላከ? ለ12ቱ የተሰጣቸው ትዕዛዝ ምንድነው? ከዚያ በኋላ ምን ሆነ? እነዚህ ሐዋሪያት ሥራቸውን ይወጡ ዘንድ ኢየሱስ ምን ሰጣቸው?
2. የሃይልና የስልጣን ትርጉም ምንድነው?
3. እኔ መማር ያለብኝ በጊዜው የነበሩ ልማዶች ምንድናቸው? ከእግር አቧራ ማራገፍ ኢየሱስን ይጠሉ ከነበሩ አይሁድ መለየትን ያሳያል። ይህ የሚያሳየው ሐዋሪያት ሕዝቡ ስለሚሰጡት ምላሽ ግንዛቤ አልነበራቸውም ማለት ነው።
4. 12ቱ የነበሩበት ሁኔታ ምን እንደሚመስል በጥንቃቄ መርምር። ዛሬ በሐዋሪያት ታሪክ የተፈጸመው ድንቅ ነገር ምንድነው?
5. እነዚህ 12ቱ ሐዋሪያት በሥራቸው እምነት የጣሉት በማን ላይ ነው?

**የክፍሉ ትርጉም ምንድነው?** ስለ ኢየሱስ አመራር ዘዴ የምትማረው ምንድነው? እርሱ እነዚህን 12ቱን የላከው ለምንድነው ኢየሱስ እነርሱን በዚህ ጊዜ ሊልክ የፈለገው ለምንድነው? ኢየሱስ መንግሥቱን ለማስፋት መስበክንና መፈወስን ጎን ለጎን

የተጠቀመው ለምንድነው? ደቀመዛሙርቱ ከአንድ ከተማ ወደ ሌላ ከተማ ሲዘዋወሩ በሌሎች ላይ እንዲደገፉ ትዕዛዝ የሰጠው ለምንድነው?

**ክፍሉ ለእኔ የሚሰጠው ትርጉም ምንድነው?** በቤትህ ወይም በቡድን መጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ጊዜ እንደ ኢየሱስ ጥሩ መሪ መሆን የምትችለው እንዴት ነው?

***ይህንን ታሪክ ስለተማርኩ ሕይወቴ እንዴት መለወጥ አለበት?***

***<u>ቆም ብለህ አስብ፡</u>***
*ይህ የሐዋሪያቱ የመጀመሪያ አጭር የተልዕኮ ሥራ ሲሆን ተልዕኮውም ደቀመዛሙርትን ማፍራት ነው፡፡ ኢየሱስ ምሳሌ በመሆን ብዙ ካስተማራቸው በኂላ 12ቱ በራሳቸው እንዲያገለግሉ ላካቸው፡፡ በውጤቱም ብዙ ሠራተኞች በእግዚአብሔር መንግሥት ማገልገል ጀመሩ፡፡ በሄዱበት መንደር ሁሉ እነርሱን በተቀበሉ ሰዎች ቤት ማረፍ ጀመሩ፡፡ በሄዱባቸው ቤቶች በእንግድነት የሚቆዩት ለጥቂት ጊዜ እንጂ ለተቀበሏቸው ቤተሰቦች ሸክም ሊሆኑ አይደሉም፡፡ ተልዕኮአቸውን ሲጨርሱ ወዲያው ወደ ኢየሱስ ይመለሱ ነበር፡፡ በእግዚአብሔር መንግሥት የሚያገለግሉ ሰዎች እግዚአብሔር የሚያስፈልጋቸውን ሁሉ እንዲሰጣቸው በእርሱ ይታመኑ ነበር፡፡ አገልጋዮች እርዳታ በሚያስፈልጋቸው ጊዜ የእግዚአብሔር ልጆች በሚችሉት ቢረዱ መልካም ነው፡፡ አገልጋዮችም በሚያገኙት መጠን መኖር አለባቸው፡፡*

## ትምህርት-24

***መግቢያውን አንብብ፡-*** *ኢየሱስ ዓለም አቀፋዊ መሪ ነው፡፡ የኢየሱስ ዕቅድ የደቀመዛሙርቱን መንፈሳዊ ሕይወት ማሳደግ ነው፡፡ ኢየሱስ ይህን ያደረገው ፍጹም የሆነ የትምህርት ዝግጅት በማድረግ አይደለም፡፡ ኢየሱስ ሁኔታዎችን በማገናዘብ እርዳታ ለሚያስፈልጋቸው ሰዎችም እርዳታ እየሰጠ በማስተማሩ ቀጠለ፡፡ የዛሬውን ታሪክ ስማና ስለ ኢየሱስ አመራር አስብ፡፡*

በሉቃ፡9፡12-17 ላይ *ያለውን ታሪክ በቃል ተናገር፡፡*
*ታሪኩን አንብብ፡፡*

***በክፍሉ ውስጥ በቀጥታ የምመለከተው ምንድነው?*** *ማን? የት? መቼ? ምን ሆነ? በታሪኩ ውስጥ የተንጸባረቁ አመለካከቶች ምንድናቸው? እኔ መማር ያለብኝ በጊዜው የነበሩ ልማዶች ምንድናቸው?*
***የክፍሉ ትርጉም ምንድነው?*** *ኢየሱስ የ12ቱ ዓለም አቀፋዊ መሪ ነው፡፡ በዚያ ቀን 12ቱ የተማሩት ምንድነው? እነዚህ ደቀመዛሙርት በተልዕኮው እንዲሳተፉ ኢየሱስ እንዴት ረዳቸው? ሕዝቡ ምግቡን በልተው ሲጨርሱ የተረፉ 12ቱ መሶቦች ምን ያመለክታሉ? ቁ.17 ተመልከት፡፡*

***ክፍሉ ለእኔ የሚሰጠው ትርጉም ምንድነው?*** *ደቀመዝሙር ለማድረግ ግዴታ መማሪያ ክፍል አያስፈለግም፡፡ ስለ ኢየሱስ የማስተማር ዘዴ ከዚህ ታሪክ የምንማረው ምንድነው?*

ዮሐ፡6፡6 አንብብ። በዮሐንስ ወንጌል ከዚህ ታሪክ ጋር የሚመሳሰለው የትኛው ነው? ከዚህ የምትማረው ምንድነው?
**ይህንን ታሪክ ስለተማርኩ ሕይወቴ እንዴት መለወጥ አለበት?**

**ቆም ብለህ አስብ፡-** ደቀመዛሙርቱ ያገለግሉ ዘንድ ኢየሱስ ዕድል ሰጣቸው። አንድ ሰው ዝም ብሎ የሚመለከት ከሆነ ተመልካች ብቻ ይሆናል። አገልግሎት የደቀመዝሙርን መንፈሳዊ ሕይወት ያሳድጋል። ሌሎች እንዲያገለግሉ እንዴት መርዳት እንችላለን?

## ትምህርት-25

**መግቢያውን አንብብ፡-** እኔ የእግር ኳስ አሰልጣኝ እንደሆንኩ አስብ። አንድ አዲስ ክለብ ማደራጀት እፈልጋለሁ። አንተ በእኔ እግር ኳስ ቡድን ውስጥ መግባት ከፈለክ የሚከተለውን ማድረግ ይጠበቅብሃል። ራስህን ክደህ በማለዳ መነሳት አለብህ። ጠንክረህ መሥራት አለብህ። በእኔ ክለብ ውስጥ መሆን ትፈልጋለህ? ሌሎች ነገሮችም አሉ፡- ሰዎች ስለ አንተ ሊዋሹ ይችላሉ። እንዲሁም ሊያሙህ ይችላሉ። ቤትህን ልታጣ ትችላለህ። ልትታሰር ትችላለህ። አልፎም ልትሞት ሁሉ ትችላለህ። አሁንስ በእኔ ክለብ ውስጥ መሆን ትፈልጋለህ? ኢየሱስ ደቀመዛሙርቱን የሚጠይቀውን ጥያቄ መረዳት እንድንችል ይህ ያግዘናል። ታሪኩ ከመጽሐፍ ቅዱስ እንደሚከተለው ቀርቧል፡-

በሉቃ፡9፡23-26 እና ቁ.57-62 ያለውን ታሪክ አንብብ።

**በክፍሉ ውስጥ በቀጥታ የምመለከተው ምንድነው?** ማን? የት? መቼ? ምን ሆነ? በክፍሉ ውስጥ የተንጸባረቁ አመለካከቶች ምንድናቸው? በክፍሉ ውስጥ ያሉ ቁልፍ ቃላት ምንድናቸው?

**የክፍሉ ትርጉም ምንድነው?** ማቴ፡5፡11-12 አንብብ። አንድ ሰው በኢየሱስ ቡድን ውስጥ ለመሆን የፈለገው ለምንድነው?
ደቀመዝሙር ለመሆን ዋጋ መክፈል ማለት ምን ማለት ነው? እኛ ደቀመዝሙር ባንሆን ልናጣ የምንችለው ምንድነው? ኢየሱስን መከተል እምቢ ብል በፍጹም መለማመድ የማልችለው ምንድነው?

ሰዎች ደቀመዝሙር ላለመሆን የሚሰጡት ሰበብ ምንድነው?
**ክፍሉ ለእኔ የሚሰጠው ትርጉም ምንድነው?** ክርስቲያን ሆነህ ደቀመዝሙር ላለመሆን ትችላለህ? እግዚአብሔር ሳልከተል በእርግጥ ደስተኛ መሆን እችላለሁ?

**ታሪኩን ስለተማርኩ ሕይወቴ እንዴት መለወጥ አለበት?**

# ትምህርት-26

***መግቢያውን አንብብ፡-*** ኢየሱስ ከገሊላ ወደ ኢየሩሳሌም እየሄደ በመንገድ ላይ ሳለ ስለ እግዚአብሔር መንግሥትና ስለ እውነተኛ ደቀመዝሙርነት አስተማረ። እርሱን ሊከተሉ ለፈለጉት የወንጌል ተልዕኮ በመስጠት ይልካቸው ነበር።

በሉቃ፡10፡1-24 ያለውን ታሪክ በቃል ተናገር።
ታሪኩን አንብብ።

**በክፍሉ ውስጥ በቀጥታ የሚመለከተው ምንድነው?** ስለ 70ዎቹና ስለተሰጣቸው ተልዕኮ የምትማረው ምንድነው? የተልዕኮው ዓላማ ምን ነበር? እንዴት መዘጋጀት ነበረባቸው? መልዕክታቸውስ ምን ነበር? ያስፈለጋቸውን ነገር እንዴት ያገኙ ነበር? በክፍሉ ውስጥ የሆነው ምንድነው? በክፍሉ ውስጥ የተንጸባረቁ አመለካከቶች ምንድናቸው? ኢየሱስ 70 ሰዎችን የመረጠው ለምንድነው?

**የክፍሉ ትርጉም ምንድነው?** በቁ.3 ላይ ኢየሱስ ለበጎችና ተኩላዎች የሰጠው ትርጉም ምንድነው? በቁ.9 እና 11 የእግዚአብሔር መንግሥት ማለት ምን ማለት ነው? የእግዚአብሔር መንግሥት የቀረበው እንዴት ነው? ደቀመዛሙርቱ በመመለሳቸው ያስደሰታቸው ምንድነው? ኢየሱስ ይዘው ለመጡት ሪፖርት የሰጠው ምላሽ ምንድነው?

**(ማስታወሻ፡- የእግዚአብሔር መንግሥት በሰዎች ሕይወት የሚሆን የእግዚአብሔር አገዛዝ ነው።)**

**ክፍሉ ለእኔ የሚሰጠው ትርጉም ምንድነው?** መስካሪ ለመሆን ስትፈልግ የሚሰማህ ስሜት ምንድነው? ለአንድ ደቀመዝሙር የደስታው ምንጭ መሆን ያለበት ምንድነው? ለምን?

**ይህንን ታሪክ ስለተማርኩ ሕይወቴ እንዴት መለወጥ አለበት?**

<u>**ቆም ብለህ አስብ**</u>፡- ዓለም አቀፋዊ የደቀመዝሙር መሪ ደቀመዛሙርትን ከመማሪያ ክፍል አውጥቶ ወደ ተግባራዊ የሕይወት ኑሮ ይመራቸዋል። በዚህ ታሪክ ኢየሱስ ለተከታዮቹ ሃላፊነት ሰጣቸው። እንዲያገለግሉና ስለ አገልግሎታቸው ሪፖርት እንዲያቀርቡ ዕድል ሰጣቸው። አንተ ደቀመዝሙር ለምታደርጋቸው ሰዎች ይህንን እንዴት ምሳሌ በመሆን ማሳየት ትችላለህ? አንተ ዓለም አቀፋዊ መሪ ነህ?

# ትምህርት-27

***መግቢያውን አንብብ፡-*** የደጉ ሳምራዊ ታሪክ ለብዙዎች አዲስ አይደለም። ኢየሱስ ስለ እግዚአብሔር መንግሥት ለተሰበሰበው ሕዝብ ይናገር ነበር። ዘላለማዊ ሕይወት አለኝ ማለት ብቻ በራሱ በቂ አይደለም። እግዚአብሔር እርሱን የሚከተሉ፣እርሱን የሚታዘዙና

እርሱ እኛን እንደወደደ ሌሎችን የምንወዱ ሰዎች መንግሥት ይፈልጋል። ከመጽሐፍ ቅዱስ የዛሬውን ታሪክ ስማና በማታውቃቸው ሰዎች ላይ ስላለህ ባሕሪ ራስህን ጠይቅ።

በሉቃ፡10፡25-37 ያለውን ታሪክ በቃል ተናገር።
ታሪኩን አንብብ።

**አራቱ የጥያቄ መንገዶች፡**

1. **በክፍሉ ውስጥ በቀጥታ የምመለከተው ምንድነው?** ይህ ምሳሌ ስለሆነ ኢየሱስ ምሳሌውን የተናገረበትን ምክንያት ፈልግ። ኢየሱስ ሊያስተላልፍ የፈለገውን ነጥብ መርምር። ማን? የት? መቼ? ምን ሆነ? በክፍሉ ውስጥ የተንጸባረቁ አመለካከቶች ምንድናቸው? እኔ መማር ያለብኝ በጊዜው የነበሩ ልማዶች ምንድናቸው? በክፍሉ ውስጥ ያሉ ቁልፍ ቃላት የትኞቹ ናቸው?
2. **የክፍሉ ትርጉም ምንድነው?** እነዚህ ሰዎች በዚህ ክፍል ለምን ተጠቀሱ? እነዚህ ሰዎች በዚህ ጊዜ ሊጠቀሱ ያስፈለገበት ምንክንያት ምንድነው? እነዚህ ክስተቶች በዚህ ክፍል የሆኑት ለምንድነው? በክፍሉ ውስጥ ያሉ አመለካከቶች ለምን ተንጸባረቁ? በጊዜው የነበሩ ልማዶች ለምን አስፈለጉ? በክፍሉ ውስጥ ያሉ ቁልፍ ቃላት ለምን አስፈለጉ?
3. **ክፍሉ ለእኔ የሚሰጠው ትርጉም ምንድነው?** በክፍሉ ውስጥ የተገቡ ተስፋ ቃሎች ወይም ትዕዛዛት አሉ? እኔ መከተል ያለብኝ ወይም መሸሽ የሚገባኝ ምሳሌ አለ?
4. **ይህንን ታሪክ ስለተማርኩ ሕይወቴ እንዴት መለወጥ አለበት?**

## ትምህርት-28

**እያንዳንዱን የቡድን አባል ጠይቅ፡-** በዚህ ዓመት ደስ እንዲያሰኝህ ልታደርገው የምትፈልገው ነገር ምንድነው?

**መግቢያውን አንብብ፡-** እኛ ሁላችንም በቤተሰቦቻን፣በሥራችን፣በቤተክርስቲያናችን ጉዳይ ልንወጠር እንችላለን። እግዚአብሔርን በብዙ መንገድ ልናገለግል እንችላለን። ነገር ግን የዛሬው ታሪክ የሚናገረው በጣም አስፈላጊው ነገር ከእግዚአብሔር ጋር የጠበቀ ግንኙነት እንድናደርግ ነው።

በሉቃ፡10፡38-42 ያለውን ታሪክ በቃል ተናገር።
ታሪኩን አንብብ።

**በክፍሉ ውስጥ በቀጥታ የምመለከተው ምንድነው?** ስለ ማሪያምና ስለ ማርታ የምትማረው ምንድነው? ሥራቸው ምን ነበር? ይህ የሆነው መቼና የት ነበር? ከዛ በኋላ የሆነው ነገር ምንድነው? በክፍሉ የተንጸባረቁ አመለካከቶች ምንድናቸው? እኔ መማር ያለብኝ በጊዜው የነበሩ ልማዶች ምንድናቸው? (በዚያን ጊዜ ወንዶች በሚያስተምሩበት ቦታ ሴቶች መቀመጥና መገኘት አይችሉም ነበር።) በክፍሉ ያሉ ቁልፍ ቃላት የትኞቹ ናቸው?

**የክፍሉ ትርጉም ምንድነው?** ኢየሱስ ወደዚህ ቤት ሲገባ የወሰነው ለምንድነው? ኢየሱስ ማርታን ያልደገፈው ለምንድነው? በኢየሱስ ንግግር መሠረት በጣም አስፈላጊው ነገር ምንድነው? አንተስ ይህንን አስፈላጊውን ነገር እንዴት ማግኘት ትችላለህ?

**ክፍሉ ለእኔ የሚሰጠው ትርጉም ምንድነው?** እኔ መከተል ያለብኝ መልካም ምሳሌ ወይም መሸሽ ያለብኝ ምሳሌ አለ? ከእነዚህ ሁለቱ ሴቶች የትኛዋን ትመስላለህ? ለምን? አንድ ደቀመዝሙር ግንኙነቱን ከእግዚአብሔር ቃል ጋር እንዴት ይመሰርታል? ዮሐ፡8፡ 31-32 አንብብ፡፡

ይህንን ታሪክ ስለተማርኩ ሕይወቴ እንዴት መለወጥ አለበት?

## ትምህርት-29

በክፍል አንድ ጥናት ይህ የመጨረሻው ሳምንት ነው፡፡ ፈቃደኛ ከሆንክ ክፍል ሁለትን መቀጠል ትችላለህ፡፡ በሉቃስ ወንጌል ያሉትን የኢየሱስ ምሳሌዎች እንዴት ማጥናት እንደምትችል በሁለተኛው ክፍል ትማራለህ፡፡

በዚህ ሳምንት እስካሁን ድረስ የተማርካቸውን ዋና ዋና ነጥቦችን ከልስ፡፡ የኢየሱስ ደቀመዝሙር ለመሆን የተማርካቸው ትምህርቶች ሕይወትህን ምን ያህል ለወጡ

አንዳችሁ ለአንዳችሁ ለመፀለይና ሕብረት ለማድረግ ጊዜ ውሰዱ፡፡

# የሉቃስ ወንጌል ጥናት
# ምዕራፍ፡11-

**ምንጭ፡**

1. አፕልኬሽን ስታዲ ባይብል (Application Study Bible) የተሰኘ መጽሐፍ
2. መጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ሥራ ለበዛላቸው ሴቶች (BIBLE STUDY FOR BUSY WOMEN) የሚል በ Ethel Herr የተጻፈ መጽሐፍ
3. በጃኪ አንደርሰን (Jackie Anderson) ተጽፎ በጳውሎስ ኮይቴ የተተረጎመ

***ይህንን ለቡድንህ አባላት አንብብና ተወያዩ፡፡***
***የጥናት መመሪያዎችና መጽሐፍ ቅዱስን ከሕይወት ጋር ማዛመድ፡***

*መጽሐፍ ቅዱስን ከሕይወታችን ጋር ለማዛመድ ስንሞክር አብዛኛውን ጊዜ ያስቸግረናል፡፡ አንዳንድ ጊዜ በተሳሳተ መንገድ መጽሐፍ ቅዱስን ከሕይወታችን ጋር እናዛምዳለን፡፡ በመጀመሪያ ዘመን ለነበሩ ሰዎች መጽሐፍ ቅዱስ ለምን እንደተጻፈ አስቀድመን መረዳት አለብን፡፡ አሁን እኛ ያለንበት ዘመን እነርሱ ከነበሩበት ዘመን በጣም የራቀ ነው፡፡ እነርሱ የነበሩበት ባሕልና ወግ (ልማድ) ከእኛ ጊዜ የተለየ ነው፡፡ ለምሳሌ፡- በማቴ፡14፡29 ላይ ጴጥሮስ በውሃ ላይ እንደተራመደ ይናገራል፡፡ ይህ ማለት እኛም ዛሬ በውሃ ላይ መራመድ እንችላለን ማለት ነው?*

በሉቃስ ወንጌል የመጀመሪያዎቹን 10 ምዕራፎች ስናጠና ብዙ ታሪኮችን አግኝተናል፡፡ አሁን በምዕራፍ 11 ኢየሱስ የተናገራቸውን ምሳሌዎች እናገኛለን፡፡ ምሳሌዎች ስለ እውነተኛ ሰዎች ሕይወት የሚናገሩ አይደሉም፡፡ ኢየሱስ እነዚህን ምሳሌዎች የተጠቀመው መንፈሳዊ እውነት ለማስተማር ነው፡፡

**ምሳሌ ለየት ያለ መልክ ያለው ጽሑፍ ነው፡፡**

ኢየሱስ ብዙ ምሳሌዎችን የተጠቀመው ለምንድነው? እርሱ አስተማሪ ስለሆነ ተማሪዎቹ መንፈሳዊ እውነትን እንዲረዱ ይረዳቸዋል፡፡ ለዚህም እነርሱ የሚያውቁትን ነገር እንደ፡- አፈር፣በቆሎ እና በግ የመሳሰሉትን በመጠቀም ጀመረ፡፡

- ኢየሱስ እነዚህን ታሪኮች ለሁለት ዓላማ ነው የተናገረው፡፡ እነርሱም፡- እኛ እንዴት መኖር እንደሚገባንና እግዚአብሔር ማን እንደሆነ ለማሳየት ነው፡፡
- ምሳሌ በየዕለቱ የምናየውን ነገር በመጠቀም መንፈሳዊ እውነት ማስተማሪያ መንገድ ነው፡፡

ኢቴል ሄር (Ethel Herr) የተባለች ፀሐፊ ስለ ምሳሌ የሚከተለውን ብላለች፡- ‹‹ በግሪኩ ቃል ምሳሌ የሚጠቀመው ሁለት ነገሮችን ጎን ለጎን በማስቀመጥ ለማነጻጸር ዓላማ ነው፡፡ ኢየሱስ ሳንቲም የጠፋባትን ሴት በአንድ በኩል በማስቀመጥ በሌላ በኩል እግዚአብሔር አብ ለሚጠፉ ነፍሳት ምን ያህል እንደሚያስብ ያነጻጽራል፡፡ ስለዚህ ምሳሌ ሁለት የትርጉም ደረጃ አለው፡፡

እኛ የምሳሌዎች ትርጉም በትክክል ምን እንደሆነ ማጥናት እንችላለን፡፡ ምሳሌዎች እንዴት ማጥናት እንደምንችል ‹‹መጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ሥራ ለበዛላቸው ሴቶች›› ከተባለ ከኢቴል ሄር መጽሐፍ የተወሰዱ መመሪያዎች ከዚህ በታች ቀርበዋል፡፡

1. አብዛኛውን ጊዜ ምሳሌ አንድ ዋና ነጥብ የያዘ ሲሆን በውስጡ ያሉ ተጨማሪ ነገሮች እኛ ዋናውን መልዕክት እንድንረዳ ይረዱናል፡፡ ስለዚህ ተጨማሪ ነገሮችን ለመተርጎም መሞከር የለብንም፡፡
2. በሉቃስ ወንጌል ያለውን ምሳሌ አንብብ፡፡ ደግሞም በሌሎች ወንጌላት ስለዚህ ምሳሌ የተነገረውን ተመልከት፡፡
3. ኢየሱስ ምሳሌውን የተናገረበትን አውድ (context) አስብ፡፡ ኢየሱስ አንድን ምሳሌ እንዲናገር ያደረገው ምንድነው? ኢየሱስ ምሳሌውን በመጠቀም ለተጠየቀው ጥያቄ ምላሽ እየሰጠ ነው? በጊዜው እርሱ ሊያስተምር የፈለገው ምንድነው? ትምህርቱ ለማነው? እኛ መረዳት የሚገባን ልማድ አለ? ኢየሱስ በምሳሌው ትርጉም እየሰጠ ነው?
4. ከሁሉም የሚበልጠው ትርጉም በጊዜው ለነበሩ ሰዎች ምሳሌው ምን ትምህርት እንደሰጠ መረዳት ነው፡፡ ቀላሉን ምሳሌ ውስብስብ አታድርገው፡፡ እኛ የምንሰጠውን ትርጉም ሰዎች መረዳት ካልቻሉ ዋናውን ነጥብ ስተናል ማለት ነው፡፡
5. ከመጽሐፍ ቅዱስ ውጭ ማግኘት የማትችለውን እውነት ከሌላ ቦታ አትፈልግ፡፡
6. የክፍሉን ዋና ነጥብ ፈልግ፡፡ ወይም በታሪኩ ላይ ስለተጠቀሱ ሰዎች የሚያወራ ዋና ነጥብ ምን እንደሆነ ለማግኘት ሞክር፡፡ ለምሳሌ በሉቃ፡15 ላይ ስለ ጠፋው ልጅ በሚናገረው ታሪክ ሦስት ዓይነት ሰዎችን እናገኛለን፡፡ እነርሱም፡- ሁለቱ ልጆችና አባት ናቸው፡፡
7. ይህንን እውነት ከሕይወትህ፣ከአመለካከትህና ከሁኔታዎችህ ጋር አዛምድ፡፡

ይህን ስለ ምሳሌዎች የተሠራውን የመልመጃ ወረቀት እንጠቀማለን፡፡ ይህንን ወረቀት ኮፒ ለቡድንህ አባላት ልትሰጥ ትችላለህ፡፡

**<u>የምሳሌ መልመጃ</u>**

**የምዕራፉ ክፍልና የምሳሌው ስም---------------------------------------**

**ምሳሌው የተነገረበት አውድ፡**

ምሳሌው የተነገረው በምን ወቅት ነው?
በምሳሌው ዙሪያ ያሉ ሌሎች ትምህርቶች ምንድናቸው?
ኢየሱስ የሚናገረው ለማን ነው?
በጊዜው የነበሩ ልማዶች ምንድናቸው?
ኢየሱስ ለምሳሌው የሰጠው ትርጉም ካለ (አብዛኛውን ጊዜ ኢየሱስ ለምሳሌው ትርጉም ሲሰጥ አንመለከትም፡፡)

**የምሳሌው ዋና ነጥብ:**

**ስለ እግዚአብሔር የተሰጠ ትምህርት:**

**ስለ ሰው የተሰጠ ትምህርት:**

**እኔ እንዴት መኖር አለብኝ:**

**ራስህን ለመስጠት ፀልይ:**

## ትምህርት-1

**መግቢያውን አንብብ፡-** የዛሬው ምሳሌ ስለ ፀሎት ነው፡፡ መጀመሪያ ኢየሱስ ይፀልይ ነበር፡፡ በኋላም ደቀመዛሙርቱ ኢየሱስ ስለ ፀሎት እንዲያስተምራቸው ጠየቁት፡፡ እንዴት መፀለይ እንደሚገባቸው ኢየሱስ መንገድ አሳያቸው፡፡ ኢየሱስ በጣም የታወቀ ፀሎት አስተማራቸው፡፡ ከዚያም ሁለት ምሳሌዎችን ነገራቸው፡፡ በጌታችን ፀሎት ውስጥ ያሉ ቃላትና እርሱ በሰጠው ምሳሌ ውስጥ ያሉ ተመሳሳይ ቃላት ፈልግ፡፡

በሉቃ፡11፡5-13 ያለውን ምሳሌ ተናገር፡፡
ሉቃ፡11፡1-13 ያለውን ክፍል አንብብ፡፡

ይህን የምሳሌ መልመጃ ወረቀት ለውይይት ተጠቀም፡፡

<u>**የምሳሌ መልመጃ**</u>

**የመጽሐፉ ክፍልና የምሳሌው ስም**-----------------------------------------------------
**ምሳሌው የተነገረበት አውድ፡**

ምሳሌው የተነገረው በምን ወቅት ነው?
በምሳሌው ዙሪያ ያሉ ሌሎች ትምህርቶች ምንድናቸው?
ኢየሱስ የሚናገረው ለማን ነው?
በጊዜው የነበሩ ልማዶች ምንድናቸው?
ኢየሱስ ለምሳሌው የሰጠው ትርጉም ካለ (አብዛኛውን ጊዜ ኢየሱስ ለምሳሌው ትርጉም ሲሰጥ አንመለከትም፡፡)

**የምሳሌው ዋና ነጥብ**:
**ስለ እግዚአብሔር የተሰጠ ትምህርት**:
**ስለ ሰው የተሰጠ ትምህርት**:
**እኔ እንዴት መኖር አለብኝ**:
**ራስህን ለመስጠት ፀልይ**:

**ማብራሪያ፡-**

**ጠይቁ፣ፈልጉ፣አንኳኩ**

እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት ሶስቱ ቁልፍ ቃላት በጣም ወሳኝ ናቸው፡፡ በእርግጥ የመሰላል መወጣጫን ማሰብ ትችላለህ፡፡ አንድ ቦታ ለመውጣት መሰላል ትጠቀማለህ፡፡ በመንገድ ላይ ማቆም የለብህም፡፡ አንዳንድ ደረጃ እየረገጥክ መውጣቱን ትቀጥላለህ፡፡ እንደዚሁም በክርስትና ሕይወታችን እግዚአብሔርን መጠየቅ፣መፈለግና መዝጊያውን ማንኳኳት የሚቆም ሳይሆን ቀጣይ እንደሆነ እንማራለን፡፡ እግዚአብሔርን በትዕግስት እንጠብቀዋለን፡፡ በመጀመሪያ በፀሎት እግዚአብሔርን **ጠይቅ**፡፡ ምክንያቱም እግዚአብሔር ከአንተ ጋር የግል ግንኙነት ለማድረግ ይፈልጋልና፡፡ ለፀሎትህ ምላሽ እስከምታገኝ እግዚአብሔርን **ፈልግ**፡፡ እኛ በትዕግስት የምንጠብቅ ሰዎች እንድንሆን እግዚአብሔር ይፈልጋል፡፡ ምክንያቱም በእግዚአብሔር የምንታመን ሰዎች ስለሆንን፡፡ በመጨረሻም ደጁን **ለማንኳኳት** ምንም መጠራጠር የለብህም፡፡ ለእግዚአብሔር መታዘዛችንንና በእግዚአብሔር ላይ ያለንን እምነታችን ለማሳየት በአቋማችን የፀናን

ሰዎች እንድንሆን እግዚአብሔር ይፈልጋል፡፡ እግዚአብሔር ታላቅ አምላክ ስለሆነ በራሱ ጊዜና እንደ ፈቃዱ ለምንጠይቀው ጥያቄ መልስ ይሰጣል፡፡

## ትምህርት-2

***መግቢያውን አንብብ*፡-** በሕዝቡ መካከል አንዳንድ ሰዎች ኢየሱስን አልወደዱም፡፡ ምንም እንኳ ኢየሱስ ያደረገውን ተአምራትና ፈውሱን ቢያዩም ንስሐ ለመግባትና ኢየሱስን ለመከተል አልፈለጉም፡፡ አንተስ የቱ ጋ ነህ? በሕዝቡ መካከል ነህ? የኢየሱስ ደቀመዝሙር (ተከታይ) ነህ? አርሱን ለማወቅ ጉጉት አለህ? የዛሬውን ምሳሌ ስትማር ስለ እነዚህ ነገሮች አስብ፡፡

በሉቃ፡11፡14-28 ያለውን ታሪክ በቃል ተናገር፡፡
ታሪኩን አንብብ፡፡
የምሳሌውን መልመጃ በመጠቀም ተወያዩ፡፡

<u>የምሳሌ መልመጃ</u>

**የመጽሐፉ ክፍልና የምሳሌው ስም-----------------------------------------------------**
**ምሳሌው የተነገረበት አውድ፡**
ምሳሌው የተነገረው በምን ወቅት ነው?
በምሳሌው ዙሪያ ያሉ ሌሎች ትምህርቶች ምንድናቸው?
ኢየሱስ የሚናገረው ለማን ነው?
በጊዜው የነበሩ ልማዶች ምንድናቸው?
ኢየሱስ ለምሳሌው የሰጠው ትርጉም ካለ (አብዛኛውን ጊዜ ኢየሱስ ለምሳሌው ትርጉም ሲሰጥ አንመለከትም፡፡)
**የምሳሌው ዋና ነጥብ:**
**ስለ እግዚአብሔር የተሰጠ ትምህርት:**
**ስለ ሰው የተሰጠ ትምህርት:**
**እኔ እንዴት መኖር አለብኝ:**
**ራስህን ለመስጠት ፀልይ:**

**ውይይት፡-** የእግዚአብሔር መንግሥት በሕዝቡ መካከል እንደሆነች ኢየሱስ በግልጽ ለሕዝቡ ተናግሯል፡፡ እርሱን በሚከተሉትና እርሱን በማይከተሉት መካከል ያለውን ልዩነት ያስቀምጣል፡፡ እርሱን ለማይከተሉት ኢየሱስ የሚሰጠው ማስጠንቀቂያ ምንድነው? በቁ.28 መሠረት በእውነት ከኢየሱስ ጋር ያለው ማነው?

## ትምህርት-3

**መግቢያውን አንብብ፡-** የሕዝቡ ቁጥር እየጨመረ የኢየሱስ ትምህርት በጣም እየጠነከረ ሄደ። ሕዝቡ የሚወስዱት ውሳኔ ወይም ራሳቸውን ለእግዚአብሔር አሳልፌው አለመስጠታቸው ዋጋ እንደሚያስከፍላቸው ኢየሱስ ያስጠነቅቃቸው ነበር።

በሉቃ፡11፡29-36 ያለውን ታሪክ በቃል ተናገር።
ታሪኩን አንብብ።

የምሳሌውን መልመጃ በመጠቀም ተወያዩ።

**<u>የምሳሌ መልመጃ</u>**

**የመጽሐፉ ክፍልና የምሳሌው ስም-------------------------------------------------------**
**ምሳሌው የተነገረበት አውድ፡**

ምሳሌው የተነገረው በምን ወቅት ነው?
በምሳሌው ዙሪያ ያሉ ሌሎች ትምህርቶች ምንድናቸው?
ኢየሱስ የሚናገረው ለማን ነው?
በጊዜው የነበሩ ልማዶች ምንድናቸው?
ኢየሱስ ለምሳሌው የሰጠው ትርጉም ካለ (አብዛኛውን ጊዜ ኢየሱስ ለምሳሌው ትርጉም ሲሰጥ አንመለከትም።)

**የምሳሌው ዋና ነጥብ:**
**ስለ እግዚአብሔር የተሰጠ ትምህርት:**
**ስለ ሰው የተሰጠ ትምህርት:**
**እኔ እንዴት መኖር አለብኝ:**
**ራስህን ለመስጠት ፀልይ:**

## ትምህርት-4

**መግቢያውን አንብብ፡-** ኢየሱስ ስለ ጽዋ አጠር ያለ ምሳሌ ለፈሪሳዊያን እየተናገረ ነበር። ፈሪሳዊያን የሃይማኖት መሪዎች ሲሆኑ ሁሉንም የእግዚአብሔር ሕግጋት ለመታዘዝ የሚሞክሩ ሰዎች ነበሩ። ኢየሱስ ዛሬ ለፈሪሳዊያን ብዙ ማስጠንቀቂያዎችን ይናገራል። በመጀመሪያ ምሳሌውን ተወያዩና በቁ.42-53 የተሰጠውን ማስጠንቀቂያ አንብቡ፡

በቁ.37-41 ያለውን ታሪክ በቃል ተናገር።
በቁ.37-54 ያለውን ታሪክ አንብብ።

የምሳሌው ዋና ነጥብ ምንድነው?
የፈሪሳዊያን ምላሽ ምንድነው?
ፈሪሳዊያንና የሕግ አስማሪዎች የሚያደርጓቸውን ስህተቶች ዘርዝር።
እግዚአብሔር ዛሬ አንተን የሚያስተምርህ?

## ትምህርት-5

**መግቢያውን አንብብ፡-** ፈሪሳዊያን ግብዝነታቸውን እንዲተው ኢየሱስ ማስጠንቀቂያ መስጠቱን ቀጠለ፡፡ ደቀመዛሙርቱ ከሰው ይልቅ እግዚአብሔርን እንዲፈሩ ይናገራቸው ነበር፡፡ ይሁን እንጂ ከሕዝቡ መካከል አንድ ሰው ከመንግሥተ ሰማይ ይልቅ የገንዘብ ጉዳይ ያስጨንቀው ነበር፡፡ እርሱ ኢየሱስን ሲጠራ ኢየሱስ በብዙ ምሳሌ መለሰለት፡፡ እኛም የእግዚአብሔርን መንግሥት እንድንፈልግ እነዚህ ምሳሌዎች ያበራታቱናል፡፡

በሉቃ፡12፡16-21 ያለውን ምሳሌ በቃል ተናገር፡፡
ታሪኩን አንብብ፡፡

<u>የምሳሌ መልመጃ</u>

**የመጽሐፉ ክፍልና የምሳሌው ስም-----------------------------------------------------**
**ምሳሌው የተነገረበት አውድ፡**

ምሳሌው የተነገረው በምን ወቅት ነው?
በምሳሌው ዙሪያ ያሉ ሌሎች ትምህርቶች ምንድናቸው?
ኢየሱስ የሚናገረው ለማን ነው?
በጊዜው የነበሩ ልማዶች ምንድናቸው?
ኢየሱስ ለምሳሌው የሰጠው ትርጉም ካለ (አብዛኛውን ጊዜ ኢየሱስ ለምሳሌው ትርጉም ሲሰጥ አንመለከትም፡፡)

**የምሳሌው ዋና ነጥብ:**
**ስለ እግዚአብሔር የተሰጠ ትምህርት:**
**ስለ ሰው የተሰጠ ትምህርት:**
**እኔ እንዴት መኖር አለብኝ:**
**ስለ እግዚአብሔር መንግሥት የምትማረው ምንድነው?**

## ትምህርት-6

**መግቢያውን አንብብ፡** እኛ ስላለን ሀብት ምን ዓይነት አመለካከት ሊኖረን እንደሚገባ ኢየሱስ ያስተምረናል፡፡ ቀጣዩ ምሳሌ ከባለፈው ሳምንት ስለ ባለጠጋው ሰውና ስለ እህሉ ከሚናገረው ምሳሌ ጋር የተያያዘ ነው፡፡ ከባለፈው ሳምንት ምሳሌ ዋና ሀሳብ ምን እንደሆነ ከልስ፡፡ ከዚያም ቀጣዩን ታሪክ ተናገር፡፡

በሉቃ፡12፡22-34 ያለውን ታሪክ ተናገር፡፡
ታሪኩን አንብብ፡፡

የውይይት ጥያቄዎች፡

1. የዚህ ክፍል ዋና ነጥብ ምንድነው?
2. በሕይወትህ በጣም የተጨክበትን ጊዜ ለቡድንህ አባላት አካፍል፡፡ ስለ ጭንቀት ኢየሱስ የሚያስተምርህ ምንድነው?
3. የልብህ መዝገብ ምንድነው? በሕይወትህ ንብረት ነው የምትለው ምንድነው? እነዚህ ጥያቄዎች አንተ በግልህ ለእግዚአብሔር የምትመልሳቸው ናቸው፡፡
4. እኛ ያለንን ሁሉ ሸጠን በድህነት እንድንኖር ነው ኢየሱስ የሚያስተምረን? ኢየሱስ በዚህ ክፍል ሊያስተምረን የፈለገው ዋናው ሀሳብ ምንድነው?
5. ለዚህ ክፍል የምትሰጠው ምላሽ ምንድነው?

***ማብራሪያ፡-*** ጭንቀትን እንዴት ማስወገድ እንችላለን እምነት ብቻ ነው ከዚህ ነፃ ሊያወጣን የሚችለው፡፡ እኛ ባለን ሀብት ላይ ትክክለኛ አመለካከት እንዲኖረን ኢየሱስ ይፈልጋል፡፡ እኛ ካለን ነገር ሁሉ ሕይወት ይበልጣል፡፡ በጣም አስፈላጊው ነገር እኛ ከእግዚአብሔር ጋር ያለን ግንኙነት ነው፡፡ ስለዚህ ስግብግብነትን አጥብቀን መቃወም አለብን፡፡ እኛ በምድራዊ ሀብት ሁሌ መደሰት እንደምንችል ዓለም ይነግረናል፡፡ ለዚህ የምትሰጠው ምላሽ ምንድነው?

## ትምህርት-7

***መግቢያውን አንብብ፡-*** ስለ እግዚአብሔር መንግሥት ኢየሱስ ሁለት ተጨማሪ ምሳሌዎችን ይናገራል፡፡ ይህ እኛ አስቀድመን የእግዚአብሔርን መንግሥትና ጽድቁን እንድንፈልግ ከሚለው የኢየሱስ ትምህርት ተከትሎ የሚመጣ ነው፡፡ በቁ.34 ላይ መዝገባችን ባለበት በዚያው ልባችን እንዳለ ይናገራል፡፡ እግዚአብሔር አምላካችን በምድራዊ መንገሥታችን ሳይሆን በሰማያዊ መንግሥት ላይ ትኩረት እንድናደርግ ይፈልጋል፡፡ እግዚአብሔር አባታችን መንግሥቱን ሊሰጠን ይፈልጋል፤ግን እኛ ለዚህ ተዘጋጅተን መጠበቅ አለብን፡፡

ጌታቸው ከሠርግ እስኪመለስ ስለሚጠብቁ ሰዎች በሉቃ፡12፡35-40 ያለውን ምሳሌ ተናገር፡፡ ለባሮቹ አንድ ሥራ ስለሰጠው ጠቢብ መሪ በሉቃ፡12፡42-48 ያለውን ምሳሌ ሌላ ሰው እንዲናገር አድርግ፡፡

ሉቃ፡12፡35-48 አንብብ፡፡

***<u>የምሳሌ መልመጃ</u>***

***የመጽሐፉ ክፍልና የምሳሌው ስም-------------------------------------------------------***
**ምሳሌው የተነገረበት አውድ፡**

ምሳሌው የተነገረው በምን ወቅት ነው?
በምሳሌው ዙሪያ ያሉ ሌሎች ትምህርቶች ምንድናቸው?
ኢየሱስ የሚናገረው ለማን ነው?
በጊዜው የነበሩ ልማዶች ምንድናቸው?
ኢየሱስ ለምሳሌው የሰጠው ትርጉም ካለ (አብዛኛውን ጊዜ ኢየሱስ

ለምሳሌው ትርጉም ሲሰጥ አንመለከትም።)

**የምሳሌው ዋና ነጥብ:**
**ስለ እግዚአብሔር የተሰጠ ትምህርት:**
**ስለ ሰው የተሰጠ ትምህርት:**
**እኔ እንዴት መኖር አለብኝ:**
**ራስህን ለመስጠት ፀልይ:**

***ማብራሪያ***፦ ጌታና ባሪያ የሚሉ ቃላት በእነዚህ ምሳሌዎች ስንት ጊዜ እንደተጠቀሱ ልብ በል። ስለ ኢየሱስ ስንናገር ኢየሱስ ጌታ ነው እንላለን፤ነገር ግን ኢየሱስን በእውነት ማገልገል አለማገልገላችንን ራሳችንን ልንጠይቅ ይገባል። ልብ አድርግ፦ ታማኝ ያልሆነው ባሪያ ምሳሌ ለዘላለም ስለማያምኑ ሰዎች ምሳሌ ነው። የእግዚአብሔርን መንግሥት መፈለግ ማለት ኢየሱስ የሕይወትህን ክፍሎች ማለትም፦ ሥራህን፣ ጨዋታህን፣ቤተሰብህንና ከሌሎች ጋር ያለህን ግንኙነት ሙሉ በሙሉ ተቆጣጥሯል ማለት ነው። በሕይወትህ እግዚአብሔር እንዳይቆጣጠር የምትደብቀው ቦታ አለ?

## ትምህርት-8

***መግቢያውን አንብብ፦*** ኢየሱስ ዳግመኛ እስኪመጣ ድረስ እንዴት መኖር እንዳለብን በምሳሌ ያስተምረናል። እኛ በእርሱ ስንኖር ሊገጥመን ስለሚችለው ነገር ያስጠነቅቀናል። እነዚህ ምሳሌዎች ሳይሆኑ ምሳሌዎቹን ለማይሰሙ ሰዎች የተሰጠ ጠንካራ ማስጠንቀቂያ ነው።

ሉቃ፡12፡49-59 አንብብ።
ክፍሉን እንደገና አንብብ። በዚህ ጊዜ ‹‹እሳት፣መለያየት፣ፍርድ›› በሚሉ ቁልፍ ቃላት ላይ ትኩረት አድርግ።

**የውይይት ጥያቄዎች:**

1. የኢየሱስ መምጣት በሰዎች መካከል ግጭትን የፈጠረው ለምንድነው?
2. የዘላለምን ሕይወት ለማግኘት ስትወስን በቤተሰብህ በኩል ሊደርስ የሚችለውን ተቃውሞ ለመቀበል ዝግጁ ነህ? (ይህ ‹‹ላይፍ አፐልኬሽን›› ከተባለ መጽሐፍ ቅዱስ የተወሰደ ነው።)
3. የአሁኑን ዘመን እንዴት እንድንመረምር ነው ኢየሱስ የሚናገረን? (ቁ.56)
4. የእግዚአብሔር መንግሥት እንደቀረበችና ሕዝቡም እንዲዘጋጁ ኢየሱስ ይናራል:: ሕዝቡ ቶሎ ብለው ማድረግ ያለባቸው ነገር ምንድነው? (ቁ.58-59)
5. ኢየሱስ ተመልሶ እንደሚመጣና ሕዝቡም ተዘጋጅተው እንዲጠብቁ እያስጠነቀቃቸው እንደሆነ ልብ በል። ይህ የመጨመረሻው ክፍል ‹ለማያምኑ ሰዎች የተሰጠ ማስጠንቀቂያ ነው› የሚል ትርጉም ለክፍሉ እንድትሰጥ ይረዳሃል። ኢየሱስ ዛሬ አማኞች ለሆንን ለእኛም መልዕክት አለው።
6. እንዴት መኖር እንዳለብህ ከዚህ ክፍል የተማርከው ምንድነው?
7. በዚህ ክፍል ያለው ቃል እንደሚለው ለመመላለስ በዚህ ሳምንት ምን ታደርጋለህ?

## ትምህርት-9

**መግቢያውን አንብብ፡-** ኢየሱስ ሰዎች ለመንግሥቱ ራሳቸውን እንዲያዘጋጁ ሲያስተምር ቆይቷል፡፡ ከሕዝቡ መካከል አንዳንዶቹ ስለሞቱ አይሁድ በመናገር ምላሽ ይሰጡት ነበር፡ ፡ ጲላጦስ የሮም አገረ ገዥ ነበር፡፡ እነዚህ ሰዎች በመንግሥቱ ላይ ስላመጹ እርሱ በገሊላ ሳያስገድላቸው አይቀርም፡፡ እነርሱ ስለራሳቸው የፍርድ ቀን እንድመለከቱ ኢየሱስ ያሳስባቸዋል፡፡

በሉቃ፡13፡1-8 ያለውን ታሪክ በቃል ተናገር፡፡
ታሪኩን አንብብ፡፡

በቁ.1-5 ባለው ክፍል ያለው ዋና ሀሳብ ምንድነው?
ሁሉም ሰው አንድ ቀን መሞቱ አይቀርም፡፡ ለዘላለም ሕይወት ቁልፍ የሆነው ጉዳይ ምንድነው?

<u>የምሳሌ መልመጃ</u>

**የመጽሐፉ ክፍልና የምሳሌው ስም**------------------------------------------------------
**ምሳሌው የተነገረበት አውድ፡**

ምሳሌው የተነገረው በምን ወቅት ነው?
በምሳሌው ዙሪያ ያሉ ሌሎች ትምህርቶች ምንድናቸው?
ኢየሱስ የሚናገረው ለማን ነው?
በጊዜው የነበሩ ልማዶች ምንድናቸው?
ኢየሱስ ለምሳሌው የሰጠው ትርጉም ካለ (አብዛኛውን ጊዜ ኢየሱስ ለምሳሌው ትርጉም ሲሰጥ አንመለከትም፡፡)

**የምሳሌው ዋና ነጥብ**: ፍሬ በማያፈራ ሰው ሕይወት የሚሆነው ምንድነው?
**ስለ እግዚአብሔር የተሰጠ ትምህርት**:
**ስለ ሰው የተሰጠ ትምህርት**:
**እኔ እንዴት መኖር አለብኝ**: እግዚአብሔር ለሰጠህ በረከት ምንም ምላሽ ሳትሰጥ በረከቱን እየበላህ ነህ?
**ራስህን ለመስጠት ፀልይ**:

## ትምህርት-10

**መግቢያውን አንብብ፡-** አይሁድ ራሳቸውን ከሮም መንግሥት ጭቆና ነፃ የሚያወጣቸው አንድ ታላቅ መስሕ ይመጣል ብለው ይጠብቁ ነበር፡፡ ነገር ግን ኢየሱስ በእነዚህ ሁለቱ ምሳሌዎች ስለ መንግሥቱ ሌላ ነገር ያስተምራቸዋል፡፡ በእግዚአብሔር መንግሥት አስገራሚ ነገሮች ይፈጠራሉ፡፡ ታሪኩን በቃል ተናገሩና አንብቡት፡፡

በሉቃ፡13፡18-30 ያሉትን ምሳሌዎች በቃል ተናገር።
ምሳሌዎቹ የተፃፉበትን አውድ ለመረዳት በሉቃ፡13፡10-35 ያለውን ክፍል እንደገና አንብብ።

የውይይት ጥያቄዎች፡-

1. በሰንበት ቀን የታመሙትን መፈወስ ሥራ እንደመሥራት ተደርጎ የሚወሰደው ለምን ነበር? ለሰንበት ቀን ብሎ ሕግን ከመታዘዝና ለሰዎች የሚያስፈልጋቸውን ነገሮች ከማድረግ አንገብጋቢ የሚሆነው የትኛው ነው?
2. ኢየሱስ የታመመውን ሰው ከፈወሰ በኋላ ስለ እግዚአብሔር መንግሥት ሁለት ምሳሌዎችን ነገራቸው። በመንግሥቱ ውስጥ የሚመጡ አዲስ ሰዎች የኢየሱስ ልብ እንደሚኖራቸው ያሳያቸዋል።

<u>**የምሳሌ መልመጃ**</u>

**የመጽሐፉ ክፍልና የምሳሌው ስም**-------------------------------------------------------
**ምሳሌው የተነገረበት አውድ፡**

ኢየሱስ የሚናገረው ለማን ነው?
ኢየሱስ ለምሳሌው የሰጠው ትርጉም ካለ (አብዛኛውን ጊዜ ኢየሱስ ለምሳሌው ትርጉም ሲሰጥ አንመለከትም።)

**የምሳሌው ዋና ነጥብ**: የእግዚአብሔር መንግሥት ምን ትመስላለች የሚድኑት የትኞቹ ናቸው
**ስለ ሰው የተሰጠ ትምህርት**:
**እኔ እንዴት መኖር አለብኝ**: እግዚአብሔርን ለመከተል አሁኑኑ ላለመወሰን ኢየሱስ የሰጠው ማስጠንቀቂያ ምንድነው? (ቁ.25)
**ራስህን ለመስጠት ፀልይ**:

ከቁ.31-35 ባለው ክፍል ኢየሱስ በኢየሩሳሌም ላይ ትኩረት ያደረገው ለምንድነው? ከመንግሥቱ ውጭ ላሉ ኢየሱስ ምን ተሰማው?

## ትምህርት-11

**መግቢያውን አንብብ፡-** አንድ ቀን በሰንበት ኢየሱስ ወደ አንድ ትልቅ ሰው ቤት እራት ሊበላ ገባ። በመጀመሪያውን የሰውዬውን በሽታ ፈወሰ። ከዛ በኋላ ሰዎች በተመረጠ ቦታ ለመቀመጥ ሲሽቀዳደሙ ኢየሱስ ይመለከት ነበር፤ምክንያቱም በዚያ ባህል ሰዎች ትልቅ በሚባል ሰው አጠገብ መቀመጥን እንደ ክብር ይቆጥሩ ነበር። ይህ ኢየሱስ እንዲያስተምርና ምሳሌዎችን እንዲናገር መራው።

በሉቃ፡ 14፡15-24 ያለውን ታሪክ በቃል ተናገር።
ሉቃ፡14፡1-24 ያለውን ክፍል በሙሉ አንብብ።

በቁ.7-14 ባለው ክፍል ውይይት አድርጉ::

1. ኢየሱስ እንግዶቹን ያስተማረው ምንድነው?
2. እንግዳ ተቀባዩን ኢየሱስ ያስተማረው ምንድነው?
3. ራሳችንን እንዴት ማዋረድ እንችላለን?

በዚህ ቦታ ኢየሱስ ያስተማረው ትምህርት በታላቁ ግብዣ ጊዜ በተነገሩ ምሳሌዎች ላይ በትኩረት ተገልጾአል፡፡

***<u>የምሳሌ መልመጃ</u>***

***የመጽሐፉ ክፍልና የምሳሌው ስም***-------------------------------------------------------

**ምሳሌው የተነገረበት አውድ፡**

ምሳሌው የተነገረው በምን ወቅት ነው?
በምሳሌው ዙሪያ ያሉ ሌሎች ትምህርቶች ምንድናቸው?
ኢየሱስ የሚናገረው ለማን ነው?
በጊዜው የነበሩ ልማዶች ምንድናቸው? በዚህ ጊዜ ሁለት ጥሪዎችን መላክ የተለመደ ነበር፡፡ አንደኛው፡- በወቅቱ ስለሆነው ነገር መናገር ሲሆን ሁለተኛው፡- አሁን ሁሉም ነገር ስለተዘጋጀ የእንግዶች መምጫ ጊዜ ነው ብሎ መናገር ናቸው፡፡
ኢየሱስ ለምሳሌው የሰጠው ትርጉም ካለ (አብዛኛውን ጊዜ ኢየሱስ ለምሳሌው ትርጉም ሲሰጥ አንመለከትም፡፡)

**የምሳሌው ዋና ነጥብ**: ፍሬ በማያፈራ ሰው ሕይወት የሚሆነው ምንድነው?
**ስለ እግዚአብሔር የተሰጠ ትምህርት**:

**ስለ ሰው የተሰጠ ትምህርት**:

**እኔ እንዴት መኖር አለብኝ**:

**ራስህን ለመስጠት ፀልይ**:

***ማብራሪያ***፡- *የአይሁድ ሰዎች የእግዚአብሔር ልጆች ለመሆን የመጀመሪያውን ጥሪ ተቀበሉ፡፡ ይሁን እንጂ ኢየሱስን እንዲቀበሉና በእርሱ እንዲያምኑ የተደረገላቸውን ጥሪ ቸል አሉ፡፡ በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ አንዱ በጣም መሥራት፣መከራን መቀበል እና አሁን መዋረድ ነው፤ ነገር ግን ተስፋችን ከጌታ ጋር ልንበላ ያለውን የመጨረሻውን ታላቁን ግብዣ መጠበቅ ነው፡፡ ራዕ፡19፡6-9፡- እግዚአብሔርና ቤተክርስቲያን ሊያከብሩ ስላሉት ስለበጉ የሠርግ ግብዣ ይናገራል፡፡ ምክንያቶችን በመደርደር የእግዚአብሔርን መንግሥት እንዳታጣ!!*

## ትምህርት-12

***መግቢያውን አንብብ፡-*** *ሕዝቡ ስለ ኢየሱስ ሲሰሙ ትልቅ መነሳሳት ነበራቸው፡፡ ነገር ግን ኢየሱስ ራሳቸውን እንዲሰጡ ፈለገ፡፡ የዛሬው ትምህርት ደቀመዝሙር መሆን*

የሚያስከፍለውን ዋጋ ይናገራል። ደቀመዝሙር ማለት ራሱን ክዶ ኢየሱስን የሕይወቱ ጌታ አድርጎ ለመከተል የወሰነ፣ እግዚአብሔር እንዲለውጠው ራሱን የሰጠና ክርስቶስን ለሌሎች ለመመስከር የቆረጠ ሰው ነው።
በሉቃ፡14፡25-35 ያለውን ክፍል አንብብ።
በጎንህ ያለውን ሰው ‹‹የሚሰማ ጆሮ አለህ?›› በለው። (እንደዚህ ማለት እንደ ትልቅ ላይመስል ይችላል።) አሁን ታሪኩን እንደገና አንብብና ኢየሱስ ደቀመዛሙርቱን ሊያስተምር የፈለገውን ስማ።

**የውይይት ጥያቄዎች፡-**

1. አንድ ቤት ሠሪ ለግንባታው የሚያስፈልገውን ውጪ በትክክል ባይገምት ሊፈጠር የሚችለው ምንድነው?
2. ኢየሱስን መከተል ማለት ከችግር መላቀቅ ማለት አይደለም። ኢየሱስ ለመከተል የሚያስከፍለው ዋጋ ምንድነው?
3. ጨው ጣዕሙን ሊያጣ ይችላል። አንድ ክርስቲያን ‹‹የጨውነት›› ሕይወት ሊያጣ የሚችለው እንዴት ነው?
4. ዛሬ የተማርከው ምንድነው?

**ለመሪው**፡- ለሚቀጥለው ሳምንት ታሪኩን የሚናገሩ ሶስት ሰዎችን ወክል።

## ትምህርት-13

***መግቢያውን አንብብ፡-*** *አንድ በጣም ጠቃሚ ነው የምትለው ዕቃ ጠፍቶብህ ያውቃል? ያንን ዕቃ ለማግኘት ያደረከው ነገር ምንድነው? ፈልገህ አገኘኸው? ዕቃው ሲጠፋብህ ምን ተሰማህ? ካገኘኸው በኋላስ ምን ተሰማህ?*

ልብ በል፡- በየሳምንቱ ታሪኩን አንብብና ለቡድንህ አባላት በቃል ተናገር። እያንዳንዱ የቡድን አባል ተራ በተራ ታሪኩን ይናገር። በዚህ ሳምንት ሶስት ሰዎች ታሪኩን እንዲናገሩ አድርግ።
የጠፋውን በግ ታሪክ ተናገር። (ሉቃ፡15፡1-17)
የጠፋውን ድሪም (ሳንቲም) ታሪክ ተናገር። (ሉቃ፡15፡8-10)
የጠፋውን ልጅ ታሪክ ተናገር። (ሉቃ፡15፡11-32)

ታሪኩን አንብብ።

<u>የምሳሌ መልመጃ</u>

**የመጽሐፉ ክፍልና የምሳሌው ስም፡-** ሉቃ፡15፡ ሶስቱ ታሪኮች፡ ስለጠፋው በግ፣ ስለጠፋው ሳንቲምና ስለጠፋው ልጅ ታሪክ።
**ምሳሌው የተነገረበት አውድ፡**
*ምሳሌው የተነገረው በምን ወቅት ነው?*

*በምሳሌው ዙሪያ ያሉ ሌሎች ትምህርቶች ምንድናቸው?* እነዚህ ሶስቱ ምሳሌዎች እርስ በራሳቸው የተያያዙ ናቸው፡፡ ይህ ለምን ሆነ? ርዕስ ጉዳዩ አንድ ሆኖ ሳለ ኢየሱስ ሶስት ታሪኮችን ለምን ተናገረ?
*ኢየሱስ የሚናገረው ለማን ነው?* ቁ.1-2 በሐጢአተኞች ላይ የነበራቸው አመለካከት ምንድነው?
*በጊዜው የነበሩ ልማዶች ምንድናቸው?* አንዲት ሴት ባል ስታገባ ለሚመጣው ጊዜ ብላ የቆጠበችው ሳንቲም አላት፡፡ አንድ አባት በሕይወት እያለ ለልጆቹ ንብረቱን ለማካፈል አይገደድም:: አብዛኛውን ጊዜ የንብረት ክፍፍል የሚደረገው አባት ሲሞት ነው፡፡
*ኢየሱስ ለምሳሌው የሰጠው ትርጉም ካለ* (አብዛኛውን ጊዜ ኢየሱስ ለምሳሌው ትርጉም ሲሰጥ አንመለከትም፡፡) ቁ. 7 እና 19 ተመልከት፡፡

**የምሳሌው ዋና ነጥብ**:
**ስለ እግዚአብሔር የተሰጠ ትምህርት**:
**ስለ ሰው የተሰጠ ትምህርት**:
**እኔ እንዴት መኖር አለብኝ**: *ፈሪሳዊያንና የሕግ አስተማሪዎች በታሪኩ ውስጥ ማንን ይመስላሉ? አንተስ ማንን ትመስላለህ?* (አባቱን? የጠፋውን ልጅ? ወይስ ታላቁን ልጅ?) *ለምን?*
***ራስህን ለመስጠት ፀልይ***: ልብ በል፡- *እያንዳንዱ የቡድን አባል የዛሬውን ታሪክ ከሕይወቱ ጋር ለማዛመድ በግሉ ይፀልያል፡፡*

## ትምህርት-14

***መግቢያውን አንብብ፡-*** አብዛኞቹ ምሳሌዎች ስለ ክርስቶስ ጌትነት ይናገራሉ፡፡ *ክርስቶስ ጌታችን ስለሆነ ልባችንን ለእርሱ እንድንሰጥ ይፈልጋል የገንዘብ አጠቃቀማችን አንዱ* ክርስቶስ ልባችንን የሚፈትንበት ነገር ነው፡፡ *ፈሪሳዊያን የሃይማኖት መሪዎች ሲሆን* ገንዘብን ይወዱ ነበር፡፡ በእነርሱ አስተሳሰብ ሀብት ማካበት ፃድቅ ለመሆን እንደ *ማረጋገጫ ተደርጎ* ይወሰድ ነበር፡፡ በሌላ *አነጋገር* ሀብት ያካበተ ሰው ፃድቅ ነው ማለት ነው፡፡ እነርሱም ሆነ እኛ ገንዘብን በጥበብ እንድንጠቀም ኢየሱስ አስተምሮአል፡፡

በሉቃ፡16፡1-18 *ያለውን ታሪክ* ተናገር፡፡
*ታሪኩን* አንብብ፡፡

<u>**የምሳሌ መልመጃ**</u>

**የመጽሐፉ ክፍልና የምሳሌው ስም፡**
**ምሳሌው የተነገረበት አውድ፡**
*ምሳሌው የተነገረው በምን ወቅት ነው?*
*በምሳሌው ዙሪያ ያሉ ሌሎች ትምህርቶች ምንድናቸው?* ስለ ሕግና ስለ *መፋታት* ትምህርት ምሳሌውን ተከትሎ ይመጣል፡፡ ኢየሱስ *ፈሪሳዊያን* በገንዘብ ላይ ስለነበራቸው አመለካከት ይነግራቸዋል፡፡

*ኢየሱስ የሚናገረው ለማን ነው?* ቁ.1

*በጊዜው የነበሩ ልማዶች ምንድናቸው?* በኢየሱስ ጊዜ የነበሩ የሀይማኖት መሪዎች ወንዶች በማንኛውም ምክንያት ሚስቶቻቸውን እንዲፈቱ ይፈቅዳሉ፡፡ የኢየሱስ ትምህርት ብዙዎችን አስገረማቸው፡፡

*ኢየሱስ ለምሳሌው የሰጠው ትርጉም ካለ* (አብዛኛውን ጊዜ ኢየሱስ ለምሳሌው ትርጉም ሲሰጥ አንመለከትም፡፡)

**የምሳሌው ዋና ነጥብ**:

**ስለ እግዚአብሔር የተሰጠ ትምህርት**:

**ስለ ሰው የተሰጠ ትምህርት**: በቁ.14 ላይ *ፈሪሳዊያን* በኢየሱስ ትምህርት ሳቁ፡፡ *ገንዘብን* በጣም ይወዱ ነበር፡፡ አንተስ ለገንዘብ ትገዛለህ? ለገንዘብ ብዙ ጊዜ ትጨነቃለህ? *ዕዳ* አለብህ? በገንዘብህ ሌሎችን ለመርዳት ትቸገራለህ?

**እኔ እንዴት መኖር አለብኝ?**: *ያለህን ነገር* በአግባቡ ትጠቀማለህ

***ራስህን ለመስጠት ፀልይ***:

## ትምህርት-15

***መግቢያውን አንብብ፡-*** *የሀይማኖት መሪዎች ሀብታቸው ፃድቅ ለመሆናቸው ማረጋገጫ* እንደሆነ *ያምኑ* ነበር፡፡ እነርሱ *መልካም* ስለሆኑ እግዚአብሔር በገንዘብ እንደባረካቸው *ያምናሉ*፡፡ ኢየሱስ አንድ በጣም *ያስገረማቸውን* ምሳሌ *ነገራቸው*፡፡ ይህ ምሳሌ ባለፈው *ሳምንት* ስለ *ገንዘብና* ስለ *መልካም ገንዘብ አያያዝ* የተነገረውን ምሳሌ ተከትሎ *ይመጣል*፡፡

በሉ*ቃ*፡16፡19-31 *ያለውን ታሪክ* ተናገር፡፡
ምሳሌውን አንብብ፡፡

<u>*የምሳሌ መልመጃ*</u>

**የመጽሐፉ ክፍልና የምሳሌው ስም**-----------------------------------------------------

**ምሳሌው የተነገረበት አውድ፡**

ምሳሌው የተነገረው በምን ወቅት ነው?
በምሳሌው ዙሪያ ያሉ ሌሎች ትምህርቶች ምንድናቸው?
ኢየሱስ የሚናገረው ለማን ነው?
በጊዜው የነበሩ ልማዶች ምንድናቸው?
ኢየሱስ ለምሳሌው የሰጠው ትርጉም ካለ (አብዛኛውን ጊዜ ኢየሱስ ለምሳሌው ትርጉም ሲሰጥ አንመለከትም፡፡)

**የምሳሌው ዋና ነጥብ**:

**ስለ እግዚአብሔር የተሰጠ ትምህርት**:

**ስለ ሰው የተሰጠ ትምህርት**: ባለጠ*ጋው* ሰው ወደ *ገሃነም* የሄደው *ለምንድነው*

**እኔ እንዴት መኖር አለብኝ**: በንብረትህና በገንዘብህ ላይ *ያለህ* አመለካከት ምንድነው

**ራስህን ለመስጠት ፀልይ:**

**አስተያየት**፡- ባለጠጋው ሰው ራስ ወዳድና ለድሆች የሚራራ አልነበረም፡፡ እኛ ማየት ያለብን ያለንን የገንዘብ መጠን ሳይሆን ያለን ገንዘብ ጥቂትም ይሁን ብዙ እንዴት በአግባቡ እንደምንጠቀም ነው፡፡

## ትምህርት-16

**መግቢያውን አንብብ፡-** ኢየሱስ ስለ ይቅርታ፣ስለ እምነትና እንደ አገልጋይ ስለምንጫወተው ሚና ያስተምር ነበር፡፡ እነዚህ ሶስቱ ታሪኮች አብረው ይሄዳሉ፡፡ እነዚህ ክፍሎች እንዴት አብረው እንደተያያዙ መረዳት እንድትችል እግዚአብሔር አዲስ ማስተዋል እንዲሰጥህ ፀልይ፡፡

በሉቃ፡17፡1-10 ያለውን ታሪክ በቃል ተናገር፡፡
ታሪኩን አንብብ፡፡
**የውይይት ጥያቄዎች:**

1. በቁ.1 ኢየሱስ ስለ ሐጢአት ማስጠንቀቂያ ይሰጣል፡፡ ይህ ማስጠንቀቂያ ምንድነው?
2. እኛ ሰዎችን የምናሰናክለው እንዴት ነው?
3. ደቀመዛሙርቱ ራሳቸውን እንዲያዩ ኢየሱስ ይነግራቸዋል፡፡ ደቀመዛሙርቱ ሌሎችን የማስተማር ሃላፊነት አለባቸው፡፡ አስተማሪዎች ሌሎችን እንዴት ሊያሰናክሉ ይችላሉ?
4. ሌሎችን መገሰጽ ማለት በሌሎች ላይ የምናየውን ሐጢአት ሁሉ መናገር አይደለም፡፡ በጣም አስፈላጊው ነገር ሌሎችን ወደ እግዚአብሔር ማቅረብ ነው፡፡ አንድ ሐጢአት የሠራውን ሰው ከመቅረባችን በፊት ስለዛ ሰው ያለን አመለካከት ምን መሆን አለበት?
5. ለአንድ ሰው ደግሞ ደጋግሞ ይቅርታ ማድረግ ምን ያህል አስቸጋሪ ነገር እንደሆነ ደቀመዛሙርቱ ገብቶአቸዋል፡፡ ይህንን ታላቅ ይቅርታ እንዲያደርጉ ኢየሱስ እምነት እንዲሰጣቸው ጠይቀዋል፡፡ እምነት ምንድነው?
6. የሰናፍጭ ቅንጣት (ዘር) በባህሪው በጣም ትንሽ ነው፤ ነገር ግን ሕይወት ያለውና የሚያድግ ነገር ነው፡፡ ኢየሱስ በዚህ ቦታ የሚያስተምረው ያላቸውን የእምነት መጠን ሳይሆን እምነታቸው እውተኛና የሚያድግ እንዲሆን ነው፡፡ ይህ የኢየሱስ ትምህርት በቁ.7-10 ካለው ሀሳብ ጋር እንዴት ይያያዛል?
7. በቁ.7-10 ኢየሱስ ሊያስተምር የፈለገው ዋናው ሀሳብ ምንድነው?
8. እግዚአብሔርን ስለምታገለግል ተጨማሪ በረከት ይገባኛል የሚል ስሜት አንዳንዴ ይሰማሃል? መታዘዝ ግዴታችን ነው ወይስ በፍላጎት የምናደርገው ነገር ነው?
9. ይቅርታ ስለማድረግና የእግዚአብሔር አገልጋይ ስለመሆን ዛሬ የተማርከው ምንድነው?

## ትምህርት-17፡ የፀሎትና የምስጋና ጊዜ

***መግቢያውን አንብብ፡-*** ኢየሱስ ወደ ኢየሩሳሌም ሲሄድ ሳለ በመጀመሪያ ከበሽታቸው የተነሣ ከማህበረሰቡ የተገለሉትን ለምፃሞች አገኘ፡፡ አንድ ለምፃም ከለምጹ ቢፈወስ አስቀድሞ ወደ ካህኑ ሄዶ ሲያሳየው ካህኑ ሰውየው ከለምጹ መፈወሱን ያውጅለታል፡፡ በሉቃ፡17፡11-17 ያለውን ታሪክ በቃል ተናገር፡፡
ታሪኩን አንብብ፡፡

**የውይይት ጥያቄዎች፡**

1. ለምፃሞቹ ፈውስ ከማግኘታቸው በፊት ኢየሱስ ወደ ካህኑ ላካቸው፡፡ ስለ እምነታቸው የምንማረው ምንድነው?
2. አንተስ? አንድ ነገር እንዴት እንደሚሠራ ከማየትህ በፊት እግዚአብሔር የሚልህን ታደርጋለህ?
3. ከለምፃሞቹ አንዱ ብቻ ነው ለምስጋና የተመለሰው፡፡ ይህ ለምፃም አብዛኞቹ አይሁድ ይጠሉት የነበሩት ሳምራዊ ነው፡፡ ከእግዚአብሔር በረከትን ተቀብለን አለማመስገን ይቻላል?
4. አመስጋኙ ሰው ስለፈውሱ የተማረው ነገር ምንድነው? ቁ.9
5. በሕይወትህ እግዚአብሔር ስላበዛው በረከት ጊዜ ወስደህ እግዚአብሔርን አመስግን፡፡

## ትምህርት-18

***መግቢያውን አንብብ፡-*** ስለ እግዚአብሔር መንግሥት ብዙ ማወቅ ትፈልጋለህ? የአይሁድ ሰዎች ስለሚታየው የምድሩ መንግሥት ነበር ያስቡ የነበረው፡፡ ነገር ግን እግዚአብሔር የተሻለ ነገር ነበረው፡፡ ይህም፡- የሰዎችን ሕይወት የሚቀይረው መንፈሳዊው መንግሥት ነው፡፡ የዛሬውን ትምህርት ስትማር እግዚአብሔር በሰዎች ሕይወት በተለይም ባንተ ሕይወት የሚሠራውን ሥራ አስብ፡፡

በሉቃ፡17፡20-37 ያለውን ታሪክ በቃል ተናገር፡፡

**የውይይት ጥያቄዎች፡**

1. ቁ.21 እንደገና አንብብ፡፡ የእግዚአብሔር መንግሥት በአንተ ውስጥ እንዳለች ኢየሱስ ይናገራል፡፡ ይህ ለአንተ የሚሰጠው ትርጉም ምንድነው?
2. አንድ መንግሥት የራሱ ንጉሥ አለው፡፡ በእነዚህ ቁጥሮች ስለ ንጉሡ የምትማረው ምንድነው?
3. ወደ ፊት ንጉሡ የሚመጣው እንዴት ባለ ሁኔታ ነው?
4. ንጉሡ ተመልሶ ሲመጣ አብዛኞቹ ሰዎች ምን ሲሠሩ ይገኛሉ?
5. ክርስቶስ ዳግም ሲመጣ እኛ እንዴት ሆነን መጠበቅ አለብን?

6. ቁ. 37 ምሳሌ ነው። ብዙ ጥንብ አንሳዎች በአንድ ቦታ ቢሰበሰቡ አንድ የሞተ ነገር በቅርብ አለ ማለት ነው። እንደዚሁም ብዙ የምጽአቱን ምልክቶች ብታዩ ጊዜው ቅርብ እንደሆነ ኢየሱስ ይናገራል።
7. ዛሬ የተማርከው ምንድነው?

## ትምህርት-19

***መግቢያውን አንብብ፡-*** ዛሬ ሁለት ምሳሌዎች ስለ ፀሎት ይናገራሉ። ከእግዚአብሔር ሰዎች መካከል መበለቶች ትልቅ ድጋፍ የሚሹ ናቸው። ለእነርሱ ጥንቃቄ እንዲደረግላቸው እግዚአብሔር ይፈልጋል። ፀሎታችንን እንዴት ወደ እግዚአብሔር ማቅረብ እንዳለብን እግዚአብሔር ይፈልጋል።

በሉቃ፡18፡1-14 ያሉትን ምሳሌዎች በቃል ተናገር።
ምሳሌዎቹን አንብብ።

1. ኢየሱስ ምሳሌዎቹን የተናገረው ለምንድነው? ቁ.1 እና 9
2. ኢየሱስ የሚናገረው ለማነው?
3. የእያንዳንዱ ምሳሌ ዋና ነጥብ ምንድነው?
4. እኛ ብዙውን ጊዜ የግድ ረጅም ፀሎት ስለፀለይን እግዚአብሔር መልስ ይሰጣል ብለን እናምናለን። ይህ ምሳሌ ይህን አያስተምርም። ታዲያ ሳይታክቱ ዘወትር መፀለይ ማለት ምን ማለት ነው?
5. ስለ እግዚአብሔርና ለፀሎትህ እርሱ ስለሚሰጠው ምላሽ የምትማረው ምንድነው?
6. በትህትና በመፀለይ ላይ ስላለው አመለካከት የምትማረው ምንድነው?
7. ትዕቢት ፀሎታችንን እንዴት ሊጎዳ ይችላል?

**አስተያየት**፡- ፀሎታችንን ወደ እግዚአብሔር ስናደርስ እግዚአብሔር መልስ እንደሚሰጥ ማመን አለብን። አንዳንድ ጊዜ ለፀሎታችን መልሱ ሊዘገይ ይችላል፤ነገር ግን ራሳችንን በመስጠት በእምነት ሳናቋርጥ መፀለይ አለብን። ነገሮቻችንን ለእግዚአብሔር ማቅረብ በእግዚአብሔር ጋር ያለንን ግንኙነት ከማጠናከሩም አልፎ በእርሱ እንድንደገፍ ይረዳናል። ስለዚህ ስንጨነቅ እንፀልያለን። ልብ በል፡- እግዚአብሔር ፀሎትህን ስለሚሰማ በቀጥታ ከእርሱ ጋር በፀሎት መነጋገር ትችላለህ።

## ትምህርት-20

***መግቢያውን አንብብ፡-*** አንዲት እና ልጆቿን ለበረከት ወደ አንድ የታወቀ ሰው ይዛ መምጣት በዚያ ባህል የተለመደ ነገር ነው። ኢየሱስ ሕፃናት ወደ እርሱ እንዲመጡ ፈቀደ፤ደቀመዛሙርቱንም በዚህ አንድ ትምህርት አስተማራቸው። ይህ ትምህርት ከሚቀጥለው ታሪክ ጋር የተያያዘ ነው።

በሉቃ፡18፡18-30 ስለ ባለጠጋው ወጣት የሚያወራውን ታሪክ በቃል ተናገር።
ሉቃ፡18፡15-30 አንብብ።

**የውይይት ጥያቄዎች፡**

1. በቁ.16 እና 17 ኢየሱስ የሚያስተምረው ትምህርት ምንድነው?
2. ወጣቱ ባለጠጋው ሰው ኢየሱስን የጠየቀው ምንድነው? ለምን? ስለዚህ ሰው የምንማረው ምንድነው?
3. ኢየሱስ መልሶ፡-‹‹ስለ ምን ቸር ትለኛለህ? ከአንዱ ከእግዚአብሔር በቀር ቸር የለም።›› ይህ ሰው እንዲያውቅ ኢየሱስ የፈለገው ምንድነው?
4. ይህ ባለጠጋ ኢየሱስን መከተል ያስፈለገው ለምንድነው? እንደ ሕፃን ሆኖ እንዴት ወደ እግዚአብሔር መንግሥት መግባት ይችላል?
5. ለባለጠጋ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት መግባት ከባድ የሚሆነው ለምንድነው?
6. ማን መዳን እንደሚችል የተማርከው ምንድነው?
7. ኢየሱስን በመከተል የሚመጡ ጥቅሞችና ተግዳሮቶች ምንድናቸው?
8. በዚህ ሳምንት ኢየሱስን መከተልህን ለማሳየትና ለሚያስፈልግህ ነገር ሁሉ በእርሱ መታመንህን ለመግለጽ ልታደርገው ያለኸውን ነገር አስብና ለቡድንህ አባላት አካፍል።

## ትምህርት-21

**መግቢያውን አንብብ፡-** ኢየሱስ የሚሞትበት ጊዜ ስለ ተቃረበ ወደ ኢየሩሳሌም ይወጣል። ቀጣዩን የሉቃስ ወንጌል ስታጠና የኢየሱስን የመጨረሻ ግብ አስብ። እነዚህ የኢየሱስ የመጨረሻ ቀኖች ስለሆኑ ደቀመዛሙርቱን እያዘጋጀ ነው። ሌሎችን መርዳቱንና ማስተማሩን ቀጠለ።

በሉቃ፡18፡31-34 ያለውን ታሪክ አንብብ።
በኢየሱስ ሕይወት ምን እንደሚሆን የምትማረው ምንድነው?
ለደቀመዛሙርቱ ይህ የማይገባቸው ለምንድነው?

በሉቃ፡18፡35-43 ያለውን ታሪክ በቃል ተናገር።
ክፍሉን አንብብ።

የውይይት ጥያቄዎች

1. ስለ ኢየሱስ የምትማረው ምንድነው?
2. ከዕውሩ ሰው የምትማረው ምንድነው?
3. ዕውሩ ሰው ስለ ኢየሱስ የተረዳው ምንድነው?
4. እግዚአብሔር ዛሬ የሚናገርህ ምንድነው? እግዚአብሔር መረዳትን እንዲሰጥህና እርሱን መታዘዝ እንድትችል እንዲረዳህ ፀልይ።

## ትምህርት-22

***መግቢያውን አንብብ፡-*** *አይሁድ ለሮም መንግሥት ግብር ይከፍሉ ነበር፡፡ ይህን ድርጊት አልወደዱትም፤ምክንያቱም ሮማዊያን ለባእድ አምልኮ የተገዙ ነበሩና ተገድደው ይከፍሉ ነበር፡፡ ቀረጥ ሰብሳቢዎች አይሁድ ነበሩና ከሚገባው በላይ ይሰበስቡ ነበርና ባለጠጎች ሆኑ፡፡ በእያንዳንዱ አገር በእውነቱ መጥፎ የሚባሉ ሰዎች አሉ፤ነገር ግን እኛ የኢየሱስን ፈለግ መከተልና ለእነዚህ ሰዎች ወንጌልን መመስከር አለብን፡፡*

በሉቃ፡19፡1-10 ያለውን ታሪክ በቃል ተናገር፡፡
እያንዳንዱ የቡድኑ አባል ታሪኩን ተራ በተራ ይናገራል፡፡ ብዙ ሰው ይህንን ታሪክ በፊት ሰምቶ ሊሆን ይችላል፡፡
ታሪኩን አንብባ፡፡
የውይይት ጥያቄዎች፡

1. ስለ ዘኬዎስ የምትማረው ምንድነው?
2. ስለ ኢየሱስ የምትማረው ምንድነው?
3. በሥፍራው ስለተሰበሰበው ሕዝብ የምትማረው ምንድነው?
4. በቁ.9 ላይ ኢየሱስ ዘኬዎስን የአብርሃም ልጅ በማለቱ የምትማረው ምንድነው? አንተ በክርስቲያን ቤተሰብ በመወለድህ ደህንነትን ማግኘት ትችላለህ?
5. ዘኬዎስ በውስጡ መለወጡን ለማሳየት ያደረገው ነገር ምንድነው?
6. እምነትህን በተግባር ትገልፃለህ?
7. በውስጥህ የተፈጠረልህን እምነት ለማሳየት በዚህ ሳምንት የምታደርገው ምንድነው?

## ትምህርት-23

***መግቢያውን አንብብ፡-*** *ኢየሱስ ለዘኬዎስ ቤት መዳን እንደሆነ ለአይሁድ ነገራቸው፡፡ ዘኬዎስም ድሆችን በመርዳት መዳኑን በተግባር ገለፀ፡፡ ሰዎችን ማጭበርበሩን ተወ፡፡ አሁን ኢየሱስ ተከታዮቹ ስለ መንግሥቱ ዳግም ምጽአትን ሲጠብቁ ሳሉ <u>ታማኞች እንዲሆኑና ፍሬአማ ሕይወት እንዲኖሩ</u> ለማበረታታት አንድ ምሳሌ ነገራቸው፡፡ ታሪኩ ከሉቃ፡19 እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡*

በሉቃ፡19፡11-27 ያለውን ታሪክ በቃል ተናገር፡፡
ምሳሌውን አንብብ፡፡

***ርዕስ፡- አሥር የንጉሡ አገልጋዮች***

**ምሳሌው የተነገረበት አውድ፡**

ምሳሌው የተነገረው በምን ወቅት፡- ስለ እግዚአብሔር መንግሥት ሰዎች ያስቡ የነበረው ምንድነው?

በምሳሌው ዙሪያ ያሉ ሌሎች ትምህርቶች፡- ዘኬዎስ ለሌሎች ምሳሌ ሊሆን የሚችለው እንዴት ነው?

ኢየሱስ የሚናገረው ለማን ነው?

በጊዜው የነበሩ ልማዶች፡- ሕዝቡ ከሮም አገዛዝ ነጻ የሚያወጣቸውን አንድ የፖለቲካ መሪ ተስፋ ያደርጉ ነበር። ‹‹ምናን›› ማለት ለሦስት ሥራ የሚሰጥ ክፍያ ነው።

ኢየሱስ ለምሳሌው የሰጠው ትርጉም ካለ (አብዛኛውን ጊዜ ኢየሱስ ለምሳሌው ትርጉም ሲሰጥ አንመለከትም።)

**የምሳሌው ዋና ነጥብ**: የኢየሱስን ዳግም ምጽአት ስንጠብቅ እንዴት ሆነን መጠበቅ አለብን?

**ስለ እግዚአብሔር የተሰጠ ትምህርት**: እግዚአብሔር ለአንተ የሰጠው ምንድነው? ለመንግሥቱ ምን እንድታደርጉ ነው እግዚአብሔር ከአንተ የሚጠብቀው?

**ስለ ሰው የተሰጠ ትምህርት**: ገንዘቡን ወስዶ የደበቀው ሰው ስለ ራሱ ብቻ ያስብ ነበር። ለመንግሥቱ የሚያስፈልገውን አድርጎ ነበር?

**እኔ እንዴት መኖር አለብኝ?** የእግዚአብሔር መንግሥት እንዲስፋ ትፈልጋለህ? የሌሎች ጉዳይ ያሳስብሃል? እግዚአብሔር ዛሬ የሚያስተምርህ ምንድነው?

***ራስን ለመስጠት የሚደረግ ፀሎት፡-*** *ታማኝ አገልጋይ ሆነህ የተሰጠህን ፀጋ ለመንግሥቱ እንድትጠቀም እግዚአብሔር እንዲረዳህ ፀልይ።*

## ትምህርት-24

***መግቢያውን አንብብ፡-*** ኢየሱስ በአህያ ውርንጫ ተቀምጦ ወደ ኢየሩሳሌ እየሄደ ነው። ይህ ከመሞቱ በፊት የመጨረሻው ሳምንት ነበር። ኢየሱስ በዓለም የታወቀ ነው። ብዙ ሕዝብም የኢየሱስ ዝና ስለገረማቸው የፋሲካ በዓልን ለማክበር ወደ ኢየሩሳሌም ይመጡ ነበር። ይህንን ታሪክ በቃል ተናገርና ሕዝቡ እግዚአብሔርን እንዲያመሰግኑ ያደረጋቸውን ምክንያት አስብ። ስለ ኢየሱስ የተሳሳተ ሀሳብ ነበራቸው?

በሉቃ፡19፡28-48 በቃል ተናገር።
ክፍሉን አንብብ።

የውይይት ጥያቄዎች፡

1. ት/ዘካ፡9፡9 አንብብ። ኢየሱስ ይህንን ትንቢት ፈጽሞታል። ኢየሱስ ለሕዝቡ የተናገረው ምንድነው የሕዝቡ ምላሽ ምንድነው?
2. መስሑ ምን እንዲያደርግላቸው ነው ሕዝቡ ሲጠብቁ የነበረው? (የሕዝቡን ክብር እንደሚመልስ ነበር ሲጠብቁ የነበረው።)
3. የሃይማኖት መሪዎች (ፈሪሳዊያን) ኢየሱስ ሕዝቡን እንዲገስጽ ለምን ነገሩት? ቁ.39
4. ኢየሱስ ለከተማይቱ ያለቀሰው ለምንድነው? ከዚህ ስለ እግዚአብሔር የምትማረው ምንድነው?

5. በቁ.43 እና 44 ያለው ቃል ከ40 ዓመት በኂላ ተፈጸመ፡፡ ሮማዊያን ኢየሩሳሌምን ደመሰሱ፡፡ 600.000 የሚሆኑ አይሁድ ተገደሉ፡፡ ከዚህ የምትማረው ምንድነው?
6. ኢየሱስ ቤተመቅደሱን ያጠራው ለምንድነው?
7. የሃይማኖት መሪዎች ኢየሱስን ለመግደል የፈለጉት ለምንድነው?
8. እኛስ ዛሬ ሕይወታችን ምን ይመስላል? እግዚአብሔር ሲያሳዝነን ከእርሱ እንሸሻለን? በእግዚአብሔር ላይ ያዘንክበት ጊዜ ካለ ለቡድንህ አባላት አካፍል፡፡
9. ዛሬ ለሕይወትህ የተማርከው ምንድነው?

## ትምህርት-25

***መግቢያውን አንብብ፡-*** *የሃይማኖት መሪዎች ኢየሱስን ሊያጠፉ ስለ ፈለጉ በሉቃ፡20 ብዙ ጥያቄዎችን ይጠይቁት ነበር፡፡ የመጀመሪያው ጥያቄ ስለ ስልጣኑ ነበር፡፡ እነርሱ ሊገድሉት እንደሚፈልጉ ማወቁን ለማሳየት ኢየሱስ አንድ ምሳሌ ነገራቸው፡፡*

በሉቃ፡20፡9-19 ያለውን ምሳሌ በቃል ተናገር፡፡ የክፉ አከራዮች ምሳሌ፡፡
በሉቃ፡20፡1-8 ያለውን ሀሳብ አንብብ፡፡ ክፍሉን እንደገና አንብብ፡፡ የክፍሉ ዋና ሀሳብ ምንድነው?

**ምሳሌው የተነገረበት አውድ፡**

ምሳሌው የተነገረው በምን ወቅት ነው?
በምሳሌው ዙሪያ ያሉ ሌሎች ትምህርቶች፡ ቁ.1-8
ኢየሱስ የሚናገረው ለማን ነው?
በጊዜው የነበሩ ልማዶች፡
ኢየሱስ ለምሳሌው የሰጠው ትርጉም ካለ (ቁ.17 ኢየሱስ መዝ፡118፡22 ላይ ያለውን ትንቢት ጠቅሶ ተናገረ፡፡)

**የምሳሌው ዋና ነጥብ**: ስለ ኢየሱስ ስልጣን የምትማረው ምንድነው?
**ስለ እግዚአብሔር የተሰጠ ትምህርት**:

**ስለ ሰው የተሰጠ ትምህርት**: በቁ.16 ላይ ስላለው ምሳሌ ሕዝቡ ምላሽ የሰጡት እንዴት ነበር? የሕግ መምህራን ምላሽ የሰጡት እንዴት ነበር? ለምን? ቁ.19

**እኔ እንዴት መኖር አለብኝ?**

***ራስን ለመስጠት የሚደረግ ፀሎት፡***
*ለመሪው፡- በቀጣዩ ትምህርት ላይ ሁለት ታሪኮች አሉ፡፡ በሉቃ፡20፡20-26 እና ሉቃ፡20፡ 27-39 ያለውን ሀሳብ ሁለት ሰዎች ተራ በተራ እንዲናገሩ አድርግ፡፡*

## ትምህርት-26

***መግቢያውን አንብብ፡-*** *የሃይማኖት መሪዎች ሁለት ተጨማሪ ጥያቄዎችን ጠየቁ፡፡ አንዱ ስለ ግብር መክፈል ሲሆን ሌላው ስለ ትንሣኤ ነበር፡፡ አሁንም ኢየሱስ በሚመልሰው መልስ ልይዙት ምክንያት ይፈልጉ ነበር፡፡ ይህንን ታሪክ ተናገር፤ክፍሉን አንብብ፤ለሃይማኖት መሪዎችም የተሰጠውን ማስጠንቀቂያ በጥንቃቄ አድምጥ፡፡*

በሉቃ፡20፡20-26 እና ሉቃ፡20፡27-39 ያሉትን ታሪኮች በቃል ተናገር፡፡
<u>በሉቃ፡20፡20-47 ያለውን ክፍል አንብብ፡፡ ይህ የምዕራፉ መጨረሻ ክፍል ድረስ ነው፡፡</u>

**የውይይት ጥያቄዎች፡**

1. የሃይማኖት መሪዎች ለኢየሱስ ጥያቄዎችን ያቀርቡ የነበረው ለምንድነው?
2. ኢየሱስ ጠንካራ የሃይማኖት ጥያቄዎችን እንዴት ተወጣቸው? ሰዎች እኛን ከባድ ጥያቄዎችን ሲጠይቁን መወጣት እንድንችል ከኢየሱስ ሕይወት የምንማረው ምንድነው?
3. በቁ.46-47 ላይ ያሉ የሃይማኖት መሪዎች ምን እንደሚመስሉ ግለጽ፡፡
4. እነርሱ የከፋ ቅጣት የሚጠብቃቸው ለምንድነው? እግዚአብሔር የሃይማኖት መሪዎችን መቅጣቱ ያስገርምሃል?
5. ዛሬ ስለራስህ ሕይወት የተማርከው ምንድነው?

**አስተያየት**፡- ሰዎች ከባድ የሃይማኖት ጥያቄዎችን ሲጠይቁ ለጥያቄአቸው በቂ መልስ ይሻሉ፡፡ እንዲህ ዓይነት ሁኔታ ሲያጋጥመን ትዕግስት ሊኖረን ይገባል፤ሌሎችንም ማክበር አለብን፡፡ አንዳንድ ጊዜ ዝም ብሎ ሊከራከሩ ይችላሉ፡፡ ኢየሱስ የሚያስተምራቸው እንደነዚህ ያሉ ሰዎችን ነበር፡፡ ነገር ግን መሪዎቹ ራስ ወዳድ፣ ለሌላው የማይጠነቀቁና ትዕቢተኞች እንዳይሆኑ አስጠነቀቃቸው፡፡

## ትምህርት-27 የሕብረትና የፀሎት ጊዜ

በሉቃ፡21፡1-4 ያለውን ክፍል አንብብ፡፡
ክፍሉን እንደገና አንብብ፡፡ በክፍሉ ዋና ሀሳብ ላይ ውይይት አድርግ፡፡
ዛሬ አንዱ ለሌላው ለመፀለይ ጊዜ ውሰዱ፡

1. ገንዘብህን በአግባቡ ለመጠቀም እንድትችል ፀልይ፡፡
2. ገንዘብህን ለምን ማውጣት እንደምትችል እግዚብሔር ጥበብ እንዲሰጥህ ፀልይ፡፡
3. በገንዘብህ፣በጊዜህና በችሎታህ በእግዚአብሔር ላይ ታመን፡፡

## ትምህርት-28

**መግቢያውን አንብብ፡-** ኢየሱስ በኢየሩሳሌም በቤተመቅደስ ውስጥ ሆኖ ወደፊት ሊሆን ስላለው ነገር በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ ያስተምር ነበር። ስለ ደቀመዛሙርቱ ወደ ፊት፣ ስለ ኢየሩሳሌም ወደ ፊትና በዘመን መጨረሻ ሊመጣ ስላለው ኢየሱስ ይናገር ነበር። ብዙውን ጊዜ በትንቢት የሚሆኑ ነገሮች ‹‹በመጀመሪያ ይህ ይሆናል፤ ቀጥሎ ይህ ይሆናል›› በሚል ቅደም ተከተል አይሆኑም። ስለዚህ የውይይት ጥያቄዎችን በጥንቃቄ አንብብና የትኞቹ ጥቅሶች ስለተለያዩ የትንቢት ጊዜያት ምላሽ እንደሚሰጡ ለመረዳት ሞክር።

በሉቃ፡21፡5-24 ያለውን ክፍል አንብብ።

**የውይይት ጥያቄዎች፡**

1. ቁ.5-9 እንደገና አንብብ። ቤተመቅደሱን በተመለከተ ኢየሱስ የሰጠው ትንቢት ምንድነው? እነዚህ አይሁድ ስለዚህ ትንቢት ምን ዓይነት ስሜት ተሰማቸው ብለህ ታስባለህ?
2. ደቀመዛሙርቱ በቁ.7 ላይ ስለ ቤተመቅደሱ ኢየሱስን አንድ ጥያቄ ጠየቁ። ኢየሱስ በቁ.20-24 ለዚህ ምላሽ ይሰጣል። ስለ ኢየሩሳሌም መደምሰስ ኢየሱስ ለደቀመዛሙርቱ ምን አላቸው? ይህ ኢየሱስ ከተወለደ ከ70 ዓመት በኋላ ሆነ።
3. ደግሞ ኢየሱስ በመጨረሻ ዘመን ስለሚሆኑ ምልክቶችና ስለ ሰው ልጅ ዳግም ምጽአት ተናገራቸው። ቁ.8-11 እና 25-28 አንብብ። በእነዚህ ክፍሎች የሚሆኑ ምልክቶችን ጥቀስ። ከዚህ የምትማረው ምንድነው?
4. ቁ.12-19 አንብብ። ስለስደት የምትማረው ምንድነው? ይህ ስደት በደቀመዛሙርት ላይ ብቻ የሚደርስ ሳይሆን በሁሉም አማኞች ሕይወት የሚደርስ ነው።

## ትምህርት-29

**መግቢያውን አንብብ**፡- በባለፈው ሳምንት ትምህርት ላይ የተማርከውን ትንቢት ከልስ። በትንቢቱ ላይ ስለተዘረዘሩ ምልክቶች ተምረህ ነበር። ኢየሱስ አሁን ምሳሌ በመናገር ደቀመዛሙርቱ ምን ማድረግ እንዳለባቸው መመሪያ ሰጣቸው። ምሳሌው ከዚህ በታች ቀርቧል፡

በሉቃ፡21፡29-33 ያለውን ክፍል በቃል ተናገር።
ክፍሉን አንብብ።

የምሳሌውን መልመጃ በመጠቀም ስለ ምሳሌው ውይይት አድርግና ክፍሉን እስከ መጨረሻ አንብብ።

የምሳሌው ስም-----------------------------------------------------------------------------

**ምሳሌው የተነገረበት አውድ፡**

ምሳሌው የተነገረው በምን ወቅት ነው?
በምሳሌው ዙሪያ ያሉ ሌሎች ትምህርቶች፡
ኢየሱስ የሚናገረው ለማን ነው?
በጊዜው የነበሩ ልማዶች፡
ኢየሱስ ለምሳሌው የሰጠው ትርጉም ካለ (ብዙ ኢየሱስ ትርጉም ሲሰጥ አንመለከትም፡፡)

**የምሳሌው ዋና ነጥብ:**
**ስለ እግዚአብሔር የተሰጠ ትምህርት:**

**ስለ ሰው የተሰጠ ትምህርት:**

ሉቃ፡21፡34-38
እኛ ራሳችንን እንድንመለከት ኢየሱስ ያስጠነቅቀናል፡፡

**እኔ እንዴት መኖር አለብኝ?**

**ራስን ለመስጠት የሚደረግ ፀሎት፡**

**ለመሪው**፡- በሉቃ፡22፡1-6 እና ሉቃ፡22፡7-13 እና ሉቃ፡22፡14-23 ያሉትን ክፍሎች ከቡድንህ አባላት ሦስት ሰዎች በሚቀጥለው ሳምንት ለመናገር እንዲዘጋጁ ንገራቸው፡፡

## ትምህርት-30

**መግቢያውን አንብብ፡-** የሚቀጥሉ ትምህርቶች የኢየሱስን የመጨረሻ የምድር ቆይታ ጊዜ ይናገራሉ፡፡ ይህንን ክፍል በፊት ልታውቅ ትችላለህ፤ነገር ግን እግዚአብሔር አዲስ ማስተዋል እንዲሰጥህ ፀልይ፡፡

በሉቃ፡22፡1-6 ያለውን ክፍል በቃል ተናገር፡፡
ሉቃ፡22፡7-13 ያለውን ታሪክ በቃል ተናገር፡፡

አሁን ሁሉንም ክፍሎች አንብብ፡፡
**የውይይት ጥያቄዎች፡**
1. ሊቀ ካህናትና የሃይማኖት መሪዎች ሊያደርጉ የፈለጉት ምንድነው? ለምን?
2. ስለ አስቆሮቱ ይሁዳ የምትማረው ምንድነው?
3. ከፋሲካው ራት የምትማረው ምንድነው?
4. በዚህ ባህል አንድ ወንድ ውሃ በእንሥራ መሸከም ያልተለመደ ተግባር ነው፡፡ ውሃ መሸከም የሴቶች ተግባር ነው፡፡ ከዚህ የምትማረው ምንድነው?

በሉቃ፡22፡14-23 የመጨረሻውን ራት ታሪክ በቃል ተናገር፡፡
ታሪኩን አንብብ፡፡

**የውይይት ጥያቄዎች፡**

1. ኢየሱስ ይህን ራት ከሐዋሪያቱ ጋር ሊበላ የወሰነው ለምንድነው?
2. የአዲሱ ኪዳን ሥርዓት (ቅዱስ ቁርባን) ምን እንደሚመስል ግለጽ፡፡ እኛ ለመታሰቢያ የምናደርገው ምንድነው?
3. ቅዱስ ቁርባን ለአንተ የሚሰጠው ትርጉም ምንድነው?
4. ዛሬ የተማርከው አዲስ ነገር አለ?

## ትምህርት-31

***መግቢያውን አንብብ፡-*** ኢየሱስ ስለሞቱና አሳልፎ የሚሰጠው ማን እንደሆነ ተናግሮ ነበር፤ነገር ግን ሐዋሪያቱ ‹‹ከእኛ መካከል ታላቅ የሚሆን ማነው?›› የሚል ጥያቄ ኢየሱስን ጠየቁት፡፡ አንዳንድ ጊዜ ስለ ኢየሱስና ስለ እግዚአብሔር መንግሥት ከማሰብ ይልቅ ስለራሳችን እናስባለን፡፡ ከዛሬው ታሪክ በእግዚአብሔር መንግሥት ስለ መሪነት መማር እንችላለን፡፡

በሉቃ፡22፡24-34 ያለውን ታሪክ በቃል ተናገር፡፡
ክፍሉን አንብብ፡፡

**የውይይት ጥያቄዎች፡**

1. ስለ አለማዊ መሪዎች የምትማረው ምንድነው?
2. እግዚአብሔር የሚፈልገው ምን ዓይነት መሪ ነው?
3. ኢየሱስ ለሐዋሪያቱ የገባው ተስፋ ቃል ምንድነው? በሉቃ፡21፡12-19 የተማርከውን ታሪክ አትዘንጋ፡፡
4. ስለ ጴጥሮስ ኢየሱስ የሰጠው ትንቢት ምንድነው?
5. ከጴጥሮስ ታሪክ መማር የምንችለው ምንድነው?
6. እግዚአብሔር ዛሬ አንተን የሚያስተምርህ ምንድነው?

## ትምህርት-32

***መግቢያውን አንብብ፡-*** ዛሬ የኢየሱስን ሞት ታሪክ እናነባለን፡፡ ከመጀመሪያው እስከ መጨረሻው ታነበዋለህ፡፡ ጊዜ ካለህ ሁለት ጊዜ አንብበው፡፡ ኢየሱስ ሕይወቱን ለአንተ መስዋዕት አድርጎ ሰጥቷል፡፡ እግዚአብሔር በዚህ እውነት ልብህን እንዲነካው ፀልይ፡፡

በሉቃ፡22፡35-23፡56 ያለውን ክፍል አንብብ፡፡
በዚህ ክፍል የሆኑት ታላላቅ ክስተቶች ተገልጸዋል፡፡ እነዚህን ክስተቶች የሚናገሩትን ቁጥሮች ፈልገህ አግኝ፡፡ የመጀመሪያው ምሳሌ ተሰርቶልሃል፡፡

1. በቅዱሳት መጽሐፍት የተጻፉትን ኢየሱስ ፈጽሟቸዋል፡፡ ሉቃ፡22፡35-38
2. ኢየሱስ ወደ ደብረ ዘይት ተራራ ሄዶ ፀለየ፡፡
3. የኢየሱስ አልፎ መሰጠትና በወታደሮች መያዝ፡፡
4. ጴጥሮስ ኢየሱስን ካደው፡፡

5. በኢየሱስ ላይ አፈዙበት።
6. ኢየሱስ በሸንጎ ፊት ቀረበ።
7. ኢየሱስ በጲላጦስ ፊት ቀረበ።
8. ኢየሱስ በሄሮድስ ፊት ቀረበ።
9. ጲላጦስ ኢየሱስ እንዲሰቀል ለሕዝቡ አሳልፎ ሰጠው።
10. ስቅለት።
11. የኢየሱስ ሞት።
12. ኢየሱስ ተቀበረ።

ዛሬ የተማርከውን ለቡድንህ አባላት አካፍል።

## ትምህርት-33

***መግቢያውን አንብብ፡-*** እግዚአብሔርን አመስግኑ። ኢየሱስ ከሞት ተነሥቷል። ዛሬ ስለ ትንሣኤው ታሪክ አንብብ። ሁለት ጊዜ አንብበው። ከትንሣኤው ታሪክ የተነሣ እግዚአብሔር በቃሉ ልብህን እንዲነካው ፀልይ።

በሉቃ፡24፡1-35 ያለውን ታሪክ አንብብ።
ክፍሉን እንደገና አንብብ።
ከዚህ የምትማረው ምንድነው?

## ትምህርት-34

***መግቢያውን አንብብ፡-*** ዛሬ የሉቃስን ወንጌል የመጨረሻውን ክፍል እናነባለን። ከሞት ከተነሣ በኋላ ኢየሱስ ለደመዛሙርቱ ታይቶ ወደ ሰማይ ዐረገ።

የሉቃስ ወንጌል ብዙ ታሪካዊ ክስተቶችን ተናግሮናል። እግዚአብሔር ራሱንና ፈቃዱን በዚህ መጽሐፍ ገልጧል። እግዚአብሔር በዚህ መጽሐፍ ለየዕለት ኑሮህ የሚያስፈልጉህን መመሪያዎች በቃሉ እንዳስተማረህ በጥንቃቄ እንደተረዳህ ተስፋ አደርጋለሁ። እንደዚሁም ታሪኮችና ምሳሌዎች እንዴት እንደሚጠኑ ዘዴው እንደገባህ ተስፋ አደርጋለሁ።

ይህ የመጨረሻው የሉቃስ ወንጌል ታሪክ ነው።
በሉቃ፡24፡36-49 ያለውን ታሪክ በቃል ተናገር።
ሉቃ፡24፡36-53 አንብብ።

**የውይይት ጥያቄዎች፡**

1. በዚህ ታሪክ ስላሉ ሰዎችና ክስተቶች የምትመለከተው ምንድነው?
2. ኢየሱስ በትንቢቶች መፈጸም ላይ ትኩረት የሚያደርገው ለምንድነው? ቁ.44-47

3. ኢየሱስ በእጆቹ፣በእግሮቹና ምግብ ለመብላት እንደሚችል ትኩረት አድርጎ የሚያደርገው ለምንድነው?
4. ኢየሱስ ለደቀመዛሙርቱ የሰጠው ተስፋ ምንድነው? ቁ.49
5. ዛሬ የተማርከው ምንድነው?

ወንጌላዊው ሉቃስ የቀረውን ታሪኩን በሐዋሪያት ሥራ መጽሐፍ ይቀጥላል። ምናልባት በሚቀጥለው የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት የሐዋሪያት ሥራን መጽሐፍ ልናጠና እንችላለን።

## ትምህርት-35 የሕብረትና የፀሎት ጊዜ

ሁሉም ሰው ለየራሱ የሚከተለው ሰው ይኖረዋል። ምናልባት የአስተማሪህን ወይም የጓደኛህን ፈለግ ልትከተል ትችላለህ። ሁል ጊዜ እንደ እርሱ መሆን የምንፈልገውን ሰው ፈለግ እንከተላለን። ኢየሱስ ወንዶችንና ሴቶችን እርሱን እንዲከተሉት በታላቅ አጠራር ጠራቸው። እርሱ ወደ ሰማይ ሲሄድ የእግዚአብሔርን መንግሥት እንዲያስፋፉ ደቀመዛሙርቱን ፈለገ። ይህ የሉቃስ ወንጌል ኢየሱስን መከተል ማለት ምን ማለት እንደሆነ በቂ ግንዛቤ እንደሰጠህ ተስፋ አደርጋለሁ።

***በሉቃስ ወንጌል እስካሁን ድረስ የተማርከውን ከልስ።***

***ይህን የወንጌል መጽሐፍ ስለተማርክ ሕይወትህ ምን ያህል ተለውጧል ትላለህ እንደመጀመሪያዎቹ ደቀመዛሙርት ኢየሱስን መከተል እንድትችል እግዚአብሔር እንዲረዳህ ፀልይ።***